# የሽብር ራእይ!

የኢሕአዴግ መንግሥት አንዱ ከፋቱ ዜጎችን በሽብር ራእይ ዘፍቆ አሸማቆና አስጨንቆ መግዛት ነው:: ለመሆኑ ሽብር ምንድን ነው?

ሽብር የከፋ ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ምጥ ማለት ነው:: አሸባሪዎች ደግሞ ህፃናት የሚማሩበትን ት/ቤት በቁጥጥራቸው ስር በማድረግ፣ አይሮፕላን በመጥለፍ መንገደኞችን አግተው ፖለቲካዊ ጥቅምን ለማስከበር ሲሉ እንዲፈፀምላቸው የሚፈልጉትን ጥያቄ በማቅረብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይደራደራሉ:: ለጠየቁት ጥያቄ በቂ የሆነ መልስ ካላገኙ አሠቃቂ የሆነ ርምጃ እንደሚወስዱ ይዝታሉ:: በዚህ ወቅት በታጋቾቹና ብቤተሰቦቻቸው ላይ ሊፈጠር የሚችለውን ጭንቀትና ምጥ በቃላት ለመግለጽ ይከብዳል::

እንግዲህ ከዚህ መሠረታዊ ሀቅ ስንነሳ እውነት ባገራችን ይህንን ዓይነት ሽብር የሚፈፅሙ ሽብርተኞች አሉ ወይ? ብለን ብንጠይቅ መልሱ እንቆቅልሽ ነው የሚሆንብን::

በርግጥ ኢሕአዴግ ሥልጣን እንደያዘ በተፈጠረው የመንግሥት አስተዳደር ክፍተት በመጠቀም ግለሰቦች አይሮፕላን በመጥለፍ ወደ ውጭ አገር ለመኮብለል እንደ ፋሽን ተዘውትሮ ነበር:: ጋምቤላ፣ ባሕርዳር፣ ድሬደዋ፣ ከዚሁ አዲስ አበባ ተሞክሯል:: እነዚህ ጠላፊዎችም አገራቸውን ለኢሕአዴጋውያን ጥለው ለመሰደድ ከማሰብ በስተቀር አንድም የፖለቲካ ጥቅም ለማስከበር የሚል ጥያቄ በወቅቱ ለመንግሥት ስለማቅረባቸው መረጃ የለም:: አብዛኞቹም በቁጥጥር ሥር ውለው ቃላቸውን ሠጥተው እሥር ተፈርዶባቸው የእሥር ጊዜያቸውን ጨርሰው ወጥተው የመንግሥት ተቀጣሪም የሆኑ አሉ:: ለምሳሌ ያምቦዋ ወጣት ሙኒት ተጠቃሽ ናት:: ሙኒት ኡጋንዳ በኢትዮጵያ ኤምባሲ ውስጥ ተመድባ በመሥራት ላይ ነች::

ሌላው በዘመነ ደርግ "ከኔ ወዲያ አብዮተኛ ላሣር ነው!" በሚል በኢሕአፓና በመንግሥት መካከል በተፈጠረ ሥልጣን ለኔ ይገባኛል ግብግብ ምክንያት በነጭ ሽብርና ቀይ ሽብር ከወዲህም ሆነ ከወዲያ ያንዲት እናት ልጆች በሚያሣዝን ሁኔታ ተራርደዋል:: ይህ የታሪክ ጠባሣም ዘግናኝ ከመሆኑ በስተቀር የፀረ-ሽብር ሕግ አልወጣለትም ነበር:: ለሥልጣን ቅርምት ወንድማማቾች የተጋደሉበት በመሆኑ በሁለቱም በኩል እናቶች ከል ለብሰዋል። የሚያሣዝነው ይልቅ እናቶች ዛሬም ቢሆን ከላቸውን በነጭ ሸማ





አለመቀየራቸው ነው:: በተረፈ ዛሬ ኢሕአዴግ እንደሚጮኸው የውጭ ጫና ወይንም ያከራሪዎች እጅ አልነበረበትም:: ይህ ከሆነ ታዲያ የዛሬው የኢሕአዴግ ሥጋት ከምን የመጣ ነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው::

እንደሚታወቀው ኢሕአዴግ ያሜሪካን ሣተላይት (ተወርዋሪ ጦር) በመሆን በጎረቤት አገሮች ላይ በሰላም አስከባሪነት ስም የሚያደርገው ጣልቃገብነት በራሱ እንዲሸበርና ሰላም እንዲያጣ አድርጎታል:: የራሱ ጥላ ባሰበረገገው ቁጥር የራሱን ተግባር ነው አንዳንድ ጊዜ ገልብጦ የሚያነብልን::

በርግጥ ባንድ ወቅት ልክ እንደ አይሮፕላን ጠለፋው በኦነግ እየተሳበበ አዲስ አበባና ድሬደዋ በትላልቅ ሆቴሎች ላይ ጊዜ ጠብቀው የሚፈነዱ በምቦች እየተጠመዱ በመፈንዳታቸው ዜጎች መሞታቸውና መቁሰላቸው እውነት ነው:: ለምሳሌ ፒያሣ ትግራይ ሆቴል የፈነዳው ፈንጂ በመዝናናት ላይ የነበሩትን ንፁሐን ዜጎችንና የሆቴሉን አስተናጋጆች ጨምሮ በርካታዎች የሞትና የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል:: ይህ ሁሉ ሆኖም ኢሕአዴግ በወቅቱ በኦነግ ከማሳበብ በሥተቀር አክራሪዎች ወይንም አልቃኢዳ አለዚያም ሽብርተኞች የሚል መግለጫም ሆነ የፀረ-ሽብር ሕግ አላወጣም ነበር:: እውነታው ይህ ከሆነ ታዲያ ያሁኑ የኢሕአዴግ ሥጋትና ፍርሃት ከምን የመጣ ነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል::

ዋናውና የኢሕአዴግ ተጨባጩ ሥጋት እያደገ የመጣውን የሕዝቡን የመብት ጥያቄ ለመመለስና ለማስተናገድ ከብዶታል:: በተለይም ከ97 ዓ.ም ወዲህ የሕዝቡን ጥያቄ ለመመለስ ካቅሙ ውጭ ሆኖበታል:: በመሆኑም ሌላ ተጨማሪ የማፈኛ ሕግ እንደሚያስፈልገው አምኗል:: ይህንንም ለመጫን መልካም አጋጣሚን ወይንም "የዴሞክራትነቱን" ጭምብል የማይገፍ መሆን እንደሚገባው ተገንዝቧል:: ይኸም ተሣክቶለታል::

መቸም ኢሕአዴግ የፖለቲካ ትርፍ ያስገኝልኛል ካለና ለሥልጣን ማቆያ ጊዜ የሚያገኝ ከሆነ የሌሎችን መጥፎ ማነቆ ሕግም ሆነ ሌላውን ነገር ከመኮረጅ ወደ ኋላ አይልም:: እናም ሽብርተኝነት በኢትዮጵያ እንዳለና በምሥራቅ አፍሪካ አደጋ እንደሚሆን አስቀድሞ ከማንም በፊት መጮህ የጀመረው ያሜሪካን መንታ ፎቆች በሽብርተኞች ከተደረመሱ በኋላና ዓለም አቀፍ ገፅታ ሲሰጣቸው ነበር:: ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም የፀረ-ሽብር ሕግ አውጥቶ ሥራ ላይ አዋለ:: በተለይም ጦሩን ሞቃዲሾ ድረስ ካዘለቀ በኋላ እንቅልፍ ሊተኛ አልቻለም:: ስለመብታቸው የሚሟገቱትን ሁሉ "ሽብርተኞች" እያለ እስር ቤት ማጎርን እስካሁንም እንደተያያዘው ነው::

# የፀረ-ሽብር ሕጉ

የፀረ-ሽብር ሕጉ ገና ከመግቢያው ላይ ዓላማውን ሲያስተዋውቅ እንዲህ ይላል:-

*"በሥራ ላይ ያሉት የሀገሪቱ ሕጎች በበቂ ሁኔታ ሽብርተኝነትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ባለመሆናቸው ጠንካራ የሕግ አቅም መፍጠር በማስፈለጉ . . ."* ይላል:: *(አዋጅ ቁጥር 652/2001 ዓ.ም)*

እንግዲህ የሕጉ ዓላማ ያገርን ደህንነት ከከፉ አጥቂዎች ወይንም አሸባሪዎች ለመጠበቅ ወይንም ለመከላከል ሣይሆን የዜጎች ሽምቀቅ መሆኑን ነው የምንረዳው:: ያ ባይሆንማ ኖሮ ነባሩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ከበቂ በላይ በቂ ነበር:: ሽብር በሌለበት አገር ሽብር ያለ በማስመሰል ኢሕአዴግ ለራሱ ተሽብሮ ዜጎችን በማሸበር ሥልጣን ላይ ለመቆየት የማገቻ ሕግ አውጥቶ ነፃ ሐሳብ ለማራመድ የሚሞክሩትን ሁሉ በሽብርተኝነት እያነቀ ወደ እስር ቤት መወርወርን የትንፋሽ ማገኛ ስልት አድርጎ እየተጠቀመበት ይገኛል::

ባስፈለገው ጊዜና ለሥልጣኔ ያሠጉኛል የሚላቸውን በሕግ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችን በደረቁ በመወንጀል ወይንም የፕሮፓጋንዳ ዶፍ በማውረድ ዜጎች ወደነሱ እንዳይጠጉና አባል እንዳይሆኑ የማስፈራሪያ አጥር ሲያጥር ሕጉ በክፍል2 እንዲህ ይላል:-

*"በሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ ስለመሣተፍ" በሚለው ርእስ ሥር ፩ ማንኛውም ሰው በሽብርተኛ ድርጅት ወይንም የሽብርተኝነት ድርጊቶችን ለመፈፀም ሰው የመለመለ ወይንም አባል የሆነ ወይንም ሥልጣና የወሰደ ወይንም በድርጅቱ በማንኛቸውም መልክ የተሳተፈ እንደሆነ እንደየ ተሳትፎ ደረጃው ከ5-10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል"* ይላል:: ይህ እንግዲህ ትልቅ ማሸማቀቂያና የፍርሃት ድባብን የሚፈጥር ነው::

ኢሕአዴግ ግለሰቦችን ለማነቅና ለማጥፋት ዒላማ አድርጎ ሲነሳም እነሱን በቁጥጥር ሥር ከማድረጉ በፊት ለመረጃ ይሆኑኛል የሚላቸውን ሰዎች አስቀድሞ ያዘጋጃል:: ባስፈለገ ጊዜም ከታዳኙ ጋር አብሮ በቁጥጥር ሥር ያውላቸዋል:: ከዚህ በኋላ በሱ ላይ እንዲመሠክሩ በርካታ ማባበያዎችን ያቀርብላቸዋል:: ፈቃደኛ ካልሆኑ ከሰውዬው ጋር ተባባሪዎች ናችሁ ተብለው እድሜ ልክ እስራት እንደሚጠብቃቸው ከዛቻ ጋር ይነገራቸዋል:: በሱ ላይ በመመስከራቸውም ምንም ነገር እንደማይደርስባቸው ልዩ ጥበቃና





እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው ሁሉ ቃል ይገባላቸዋል:: ከዚህ በኋላ የተጠየቁትን ለመፈፀም ይፈቅዳሉ:: አንዳንዶቹ ግን ቀድመው የተዘጋጁ ስለሚሆኑ የሚሰጣቸውን መመሪያ ከማጥናት ውጭ ምንም ዓይነት ችግር አይፈጥሩም:: ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ማንነታቸው ሁሉ እንዳይታወቅ የፀረ-ሽብር ሕጉ እንዲጠብቃቸው ሆኖ ተቀርጿል:: ክፍል7 እንዲህ ይላል:-

*"ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች"* በሚለው ሥር አንቀጽ 32 *"ለምስክሮች ጥበቃ ስለማድረግ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፍ/ቤት ማንኛውም የሽብርተኝነትን ጉዳይ በሚያይበት ጊዜ በራሱ አነሳሽነት ወይንም ባቃቤ ሕግ ወይንም በምስክሩ ጠያቂነት የምስክሩን ማንነትና አድራሻ በሚስጥር ለመጠበቅ አስፈላጊ ርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል. . ."* ይለንና የሚወስዳቸውንም ርምጃዎች እንደሚከተለው ያስቀምጣቸዋል:-

*ሀ/ ከሱ የሚሰማበትን ቦታ መወሰን (መደበቅ ሊሆን ይችላል) በቀንፍ ውስጥ ያለው ሐሳብ የኔ ነው::*

*ለ/ የምስክሮች ስሞችና አድራሻዎች በፍ/ቤት ትእዛዞች፣ ውሳኔዎችና መዝገቦች ላይ እንዳይገለፁ*

*ሐ/ የምስክሮች ማንነትና አድራሻ እንዳይገለጽ ትእዛዞችን መስጠት"* ይላል::

እንግዲህ የፀረ-ሽብር ሕጉ ለሚዘጋጁ ምስክሮች እስከዚህ ድረስ ዘልቆ እንክብካቤ እንደሚያደርግ ተቀርጾ ተቀምጧል:: የተፈረደበትን ሰው ለማንበርከክና ከጫማ ሥር ለመጣል ደግሞ የፀረ-ሽብር ሕጉ በክፍል7 ደግሞ እንዲህ ይላል:-

*"አንቀጽ 33 የፍርድ ሂደትን ስለመርዳት" በሚለው "ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተን ወንጀል በመፈፀሙ ባድራጎቱ የተፀፀተ እንደሆነና ስለ ወንጀሉ አፈፃፀም በዝርዝር ለማስረዳት የተባበረ እንደሆነ ወይንም ወንጀሉን በመፈፀሙ ከሱ ጋር የተሳተፉ ሰዎችን ያጋለጠ እንደሆነ ባቃቤ ሕግ ጥያቄ መነሻነት ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ሊያቀልለት ይችላል"* ይላል:: ይህንን አንቀጽ በተመለከተ ነፍሳቸውን ይማረውና ጠ/ሚንስትር መለስ ፓርላማ ላይ ባንድ ወቅት አንስተው "ወንጀል መፈፀማቸውን አምነው ከተፀፁቱና ይቅርታ ከጠየቁ ምህረትም ይደረግላቸዋል" በማለት ተናግረው ነበር::

የዚህ አንቀጽ ዓላማ ሁለት ሥለት ያለው ነው:: አንደኛው ስለት አንበርክኮ ከጫማ ሥር ከጣሉ በኋላ ዳግም እንዳይለምደው አንገቱን ደፍቶ

እንዲኖር ማድረግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ሥልት ደግሞ እድሜ ልክ ፍርድ ጭኖ ሁለት ሦስት ዓመታት አሥሮ መልሶ ይቅርታ አድርጎ በምሕረት በመልቀቅ ለወገን ሩህሩህና ተጨናቂ ስለሚያስመስል በተለይ የውጭ ዜጎችን ለማታለል ይጠቅማል:: ኢሕአዴግ ይህንን ሥልት አዘውትሮ ተጠቅሞበታል:: ዛሬም እየተጠቀመበት ነው:: የዚህ ምሳሌ የሚሆኑን የቅንጅት መሪዎችና በኋላ ደግሞ ብርቱካን ሚደቅሳ ነች:: ከዚህ ውጭ ኢሕአዴግ ለዜጎች የሚራራና የሚጨነቅ አንጀት የለውም::

እንግዲህ የፀረ-ሽብር ሕጉን ከፍ ብለን እንዳየነው ያገርንና የዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅ ተብሎ የወጣ ሣይሆን የኢሕአዴግን ደህንነትና ከሥልጣን ላይ ተጣብቆ እንዲቆይ በጥንቃቄ ተሰልቶ የወጣ ሕግ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሣይ ነው::

እንደ እውነቱ ከሆነ ደርግ ሕግን ይፈራል:: ፈርቶም ያከብራል:: ሕግ የያዘውን ነገር ባጠገቡ አይደርስም፤ ወይንም በፍ/ቤቶች ጉዳይ ላይ በድፍረት ጣልቃ አይገባም:: ወይንም እንዲህና እንዲያ ይደረግ ብሎ ጫና አያደርግም:: ሊያጠፋቸው፣ ሊረሽናቸው የሚፈልጋቸውን ግለሰቦች የሕግ ሽፋኑን ሳይሰጥ ወይንም ከሕግ ፊት ሳያቀርብ "የፍየል ወጠጤ ትከሻው ያበጠ..." እያለ በመሸለል ይረሽናቸዋል:: ባንፃሩ ኢሕአዴግ ሕግን ይንቃል፤ ንቆም በሕግ ሲቀልድ ይስተዋላል:: አንዲት ነገር ከሕግ ውጭ አይሠራም እንዲባል በሕግ ሽፋን ዜጎችን ያጉላላል፤ ያንገላታል፤ በትንሿ ጥፋት ሁሉ የፖለቲካና የሽብር ጥላሸት በመቀባት እድሜ ልክ፣ ዝቅ ሲልም 20 ዓመትና 18 ዓመት ያሸከማል::

በዘመነ ኢሕአዴግ ፍ/ቤቶች ከኢሕአዴጋውያን ነፃ ናቸው ብሎ አፍን ሞልቶ ለመናገር አያስችልም:: አንዳንድ ጊዜም የፍርዱ ሂደት በባለሥልጣናት ቀድሞ የሚያልቅበት አጋጣሚም እንዳለ ዜጎች በምሬት ሲገልፁ ዓመታትን አስቆጥረዋል:: በመሆኑም በነዚህ 21 ዓመታት ውስጥ ከሁሉም እየከፋና እየጎፈነነ የመጣው የፍትህ ድርቀት እየበረታ መምጣቱ ነው::

## የፀረ-ሽብር ሕጉ ለምን አስፈለገ?

> *"ሰላማዊ ትግል ውጤት እያመጣ መሆኑ የሚታወቀው በአምባገነኖች እስር ቤቶች ሰላማዊ ታጋዮች መታጎር ሲጀምሩ ነው!!" ማኅተማ ጋንዲ::*





## የድኩላና የነብር ኑሮ ለምን?

እንደሚታወቀው ሕወሓት ሥልጣን ላይ የወጣው መጠነ ሠፊ ደም አፍስሶና ያገር ንብረትን አውድሞ እንጂ በሕዝብ ይሁንታ በምርጫ ሥልጣን ላይ የተቀመጠ በመሆኑ አይደለም:: በጉልበትና በማምታታት ሥልጣን የጨበጠ ፓርቲ ደግሞ የሰላም እንቅልፍ አይተኛም፤ ዜጎችንም አያስተኛም:: እሱ በበረገገ ቁጥር ዜጎችንም እያስበረገገ በበረት ውስጥ መንጋውን እንደሚያምስ ከፉ ኮርማ ሕዝብን እያመሰ ለመብታቸው የሚሟገቱትን ንቁ ወጣቶች ወንጀል እየፈበረከ ያግታል፤ የበረገጉት ደግሞ አገር ጥለው እንዲሰደዱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያመቻቻል:: ቀሪዎቹ በፍርሃት ተሸማቀው የድኩላና የነብር ኑሮ እየኖሩ ኖርን ይላሉ:: ከነዚህ ጠንከር ያሉቱ ደግሞ ምክንያት ተፈልጎ ወይንም በዚያው መከረኛ ሽብርተኝነት ተሳቦ ወደ እስር ቤት ይወረወራሉ::

ሕወሓት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየፈፀመ ያለው ግፍ እንቅልፍ አያስተኛውም:: ሊተኛም አይችልም:: ፈንጅ ላይ የተቀመጠ ድርጅት ነው:: ሕዝብን በጎሳ ከፋፍሎ ትውልድን አገራዊ ራእይ አሣጥቶ የኢትዮጵያን መሠረት አናግቷል:: ኤርትራን ተዋግቶ አሥገንጥሏል፤ ያሰብን የባሕር በር አዘግቷል:: በዚህ ከፉና እኩይ ተግባሩ ከሕዝብ ጋር ሊያስማማው የሚችል አንዳችም በጎ ሥንቅ የለውም::

ታዋቂው ምሁር ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ኢሕአዴግ የሚያወጣቸው ሕጎች ለዜጎች ማጥቂያነትና ሕዝቦች በባርነት እንዲማቅቁ ሆነው መቀረጻቸውን እንዲህ ሲሉ ይተቻሉ:-

*"ሕግ የዜጎች ከለላ፣ የዜጎች አለኝታ በመሆን ፈንታ በተጣመመ መንገድ እየተተረጎመ የዜጎች ማጥቂያ መሣሪያ እየሆነ፣ በዚህ ሥልት ንፁሐን ዜጎች ሲወነጀሉ፣ ሲታሠሩ፣ አገር ጥለው ሲሰደዱ፣ እውነት ዜጎችን ነፃ የማታወጣበት እየሆነች ስትሄድ እያዩ ዝም ማለት የመንግሥት ባሪያ መሆን ነው" ሲሉ ምሁሩ ነቅፈዋል:: (ፍኖተ ነፃነት ቅፅ 2 ቁጥር 37 ማክሰኞ ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም)*

በመሠረቱ መንግሥት ሕግ ሲቀርጽም ሆነ ሲያወጣ ዜጎቹን የከፋ አደጋ እንዳይገጥማቸው የመከላከያና የመጠበቂያ ሕግ ያወጣል እንጂ ገና ለገና ለሥልጣኔ ያሠጉኛል፣ ይቀናቀኑኛል ብሎ የፍርሃት ሕግ አያወጣም:: መስሎት እንጂ ሕጎች ሁሉ የወንጀሎች ምንጮች ናቸው:: አፈናው እየከፋና እየጠበቀ በሄደ ቁጥር ካፋናው ለመላቀቅ የመውጫ ቀዳዳን መፈለግ የግድ

ይሆናል፡፡ ነፃነትን በመሥጠት ወይንም በመልቀቅ እንጂ የማፈኛ ሕግ በማውጣት በጭራሽ ሕዝብን መግዛት አይቻልም፡፡ በተለይም ስለመብታቸው የሚሟገቱትን በዚሁ የማፈኛ ሕግ ወንጀል እየፈበረኩ የእድሜ ልክ እሥራት መጫን ይሰቀጥጣል፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን አንዱዓለም አራጌ፣ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ ናትናኤል መኮንን <ሽብርተኞች> ተብለው ሲያዙ በተቀናበረና በተጠና ስልት የተያዙ ለመሆናቸው ሁለት ማስረጃዎችን ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

አንደኛው እንደተያዙ "ታላቁ መሪያችን" በተወካዮች ም/ቤት ባደረጉት ንግግር ርግጠኛ ሆነው በማስረጃ እንደተያዙ ነበር የተናገሩት፡፡ ይሁን እንጂ ዘግይቶም ቢሆን የፍርድ ሂደቱ ሲጀመር አቃቤ ሕግ በተደጋጋሚ 'የጊዜ ቀጠሮ እየጠየቀ ምስክርና ማስረጃ ፍለጋ ነበር የገባው፡፡




*አንዱዓለም አራጌ ከባለቤቱና ከሁለት ህፃናት ልጆቹ ጋር የዕድሜ ልክ እሥራት ከመሸከሙ በፊት*





ሁለተኛው ማስረጃ ሦስቱም ሲያዙ በያሉበት በተመሣሣይ ሰዓት በዘመቻ ነበር፡፡ እነዚህን የሰላም ታጋዮች በጭፍኑ ሽብርተኞች ናቸው ብለን ፍርድ ከመሥጠታችን በፊት ወይንም ንፁሆች ናቸው ብለን አስቀድመን ከመቆርቆር ትንሽ ስለ ሽብርተኞች ምንነት ወይንም በገሀዱ ዓለም ስላላቸው ሕይወት ማወቅ ተገቢ ይሆናል፡፡

እንደሚታወቀው ሽብርተኞች የራሳቸው የሆነ ኑሮ የላቸውም፡፡ ሌላው ቀርቶ የት እንደሚኖሩ እንኳን በቅጡ አይታወቁም፡፡ አንዳንድ ጊዜም በውኑ ዓለም ስለመኖራቸው የምንጠራጠር ጥቂቶች ዓይደለንም፡፡ ከሚወስዷቸው ዘግናኝና አሸማቃቂ የጭካኔ ርምጃዎች አንፃር እነሱነታቸውን በሰብዓዊ ሚዛን አስቀምጦ በቃላት ለመግለፅ እጅግ ከባድ ነው፡፡ እነሱን አድኖ ለመያዝና ማንነታቸውን ለይቶ ለማወቅ የሚጠይቀው የገንዘብ መጠንና የሰው ኃይል በራሱ ያንዲትን አገር ኢኮኖሚ የሚፈታተንና የሚያደቅ ነው፡፡ አሜሪካን ኦሳማ ቢንላድንን አድና ለመያዝ ወይንም ለማጥፋት ምን ያህል ጊዜ እንደ ደከመች ዓለም ያወቀው ሀቅ ነው፡፡



*የ18 ዓመት ፈርደኛ ናትናኤል መኮንን*



*አንዱዓለም አራጌ ከባለቤቱና ከሁለት ህፃናት ልጆቹ ጋር የዕድሜ ልክ እሥራት ከመሸከሙ በፊት*

አሜሪካን ኦሳማ ቢንላድንን አድና ለመያዝ ወይንም ለማጥፋት ምን
ጊዜ እንደ ደከመች ዓለም ያወቀው ሀቅ ነው።



*የ18 ዓመት ፈርደኛ ናትናዔል መኮንን*

ከዚህ እውነታ ስንነሳ እውነት እነ አንዱዓለም አራጌ ሽብርተኞች ነበሩ? ኑሯቸውስ ከላይ እንደተገለፁት ያሉ ናቸው? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ ሦስቱም ባለትዳሮችና የልጆች አባቶች ናቸው:: ታዲያ ሦስቱም ባለትዳሮችና የልጆች አባቶች ከሆኑ በሽብርተኝነት ተግባር ላይ ለምን ተሠማሩ? ብሎ መጠየቅም ተገቢ ነው::

የኢሕአዴግ የጎሣ ሥርዓት አፋኝ ከመሆኑ የተነሣ እንቅልፍ አያስተኛም:: ሰዎች ሆነን እንደ ሰዎች የምናስብ ከሆነ እንዴት ብለን ነው የራሳችንን ምቾት በመምረጥ ብቻ ተደላድለን መቀመጥ የምንችለው? የነዚህ የሰላም ታጋዮች ችግርም ወይንም በሽብርተኝነት ያስወነጀላቸው የነሱ ኑሮ ጎሎባቸው ያንን ለማሟላት ሣይሆን የዜጎች ስቃይና ሰቆቃ አርፈው የግል ኑሯቸውን በምቾት እንዲኖሩ አላስቻላቸውም:: በተለይም የዚች አገር የወደፊት እጣ ፈንታ በእጅጉ አስጨንቋቸዋል:: የሥርዓቱ አፋኝነት የጉረሮ አጥንት ሆኖባቸዋል:: እናም የሥርዓቱን በታኝነትና አፋኝነት አጥብቀው ተቃወሙ:: መቃወም ብቻም አይደል ለውጥም መምጣት እንዳለበት አመኑ:: ይኼ ነው እንግዲህ በሽብርተኝነት ያስወነጀላቸው::

አንድን አፋኝ ሥርዓት መቃወምና የፍትሕ ሥርዓት እንዲሰፍን መታገል በሽብርተኝነት የሚያስወነጅል ከሆነ እያንዳንዱ የዚች አገር ዜጋ የሞት ያህል አይቀሬውን "ሽብር" በጀርባው አዝሎ እንደሚዞር ማወቅ አለበት:: ባጭሩ የነአንዱዓለምና የነ እስክንድር ወንጀል አርፈው እየተረገጡ ለመገዛት አለመፍቀዳቸው ብቻ ነው:: ከዚህ ውጭ ከታላላቅ ሕንፃዎች ሥር ወይንም ሕዝብ በሚዝናናባቸው ትላልቅ ሆቴሎች ፈንጂ ሲያጠምዱ ወይንም ቦሌ አይሮፕላን ለመጥለፍ ሲሉ እጅ ከፍንጅ አልተያዙም::

በመሠረቱ የሥርዓቱን አፋኝነትና ዴሞክራሲ አልባነት አውቆም ይሁን ሣያውቅ ማስታወቂያ ሚንስቴር "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይና የደህንነት፣ ፖሊሲና ስትራቴጅ" ብሎ ባሳተመው መጽሐፉ የሚከተለውን ቁምነገር አስፍሯል:-

*"የዴሞክራሲ ሥርዓት ባገራችን እውን ካልሆነ በብሔርና በእምነት ተነጣጥለን፣ በመብት መረገጥ ተቃቅረን፣ መበጣበጣችንና ሰላም መጥፋቱና ልማት ቀርቶ ድህነት መስፋፋቱ ብሎም ለእልቂትና ለብተና መዳረጋችን አይቀርም. . .ልማትና መልካም አሥተዳደርን የማስፈን ጉዳይ ብቻ ሣይሆን እልቂትና ብተናንም የማስቀረት፣ ብሔራዊ ህልውናችንን የማረጋገጥ ጉዳይም ጭምር ነው . . ."* ይለናል:: *(ገጽ 2-3)*





ማስታወቂያ ሚንስቴር ሕሊናውን ቆጥቁጦት ወይንም አይቀሬውን የከፋት ቀውስ አስቀድሞ ተገንዝቦ ይህንን ሀቅ ሣይደብቅና ሣያድበሰብስ ማስቀመጡ ሊያስመሰግነው ይገባል:: ሌላም ማስረጃ መጨመር ተገቢ ነው::

እንደሚታወቀው ጠ/ሚንስትር መለስ <የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ ዓመት ታሪክ ነው፤ የፈጠሯትም አፄ ምኒልክ ናቸው> ብለው ነው የሚያምኑት:: ይሁን እንጂ በሌላ አጋጣሚ ከሳቸው አንደበት ይወጣል ተብሎ ሊታመን በማይችል መልኩ ሲናገሩ ደግሞ ግርምትን መፍጠሩ አይቀርም:: ካንገታቸው ነው ካንጀታቸው? ለሚለው ጥያቄ ዛሬ በሕይወት ስለሌሉ መልስ ማግኘት አንችልም:: ለማንኛውም እሳቸው የተናገሩትን እነሆ:-

*"የጠቅላይ ሚንስትር ሥጋት ምን ሊሆን ይችላል?"* ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ሲመልሱ *"ሁልጊዜም ከእንቅልፌ የሚያባንነኝ ሥጋት አለ:: ይች ታላቅ አገር፣ ይቺ ካንድ ሺ ዓመታት በፊት ታላቅ የነበረች አገር አስከፊ አዘቅት ውስጥ ገብታ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎቿ የተራቡባትና የሞቱባት አገር ምናልባትም በመፈረካከስ ላይ ትሆን? የሚል ፍርሃት ይቀሰቅሰኛል::" (መለስ ከልጅነት እስከ እውቀት ገጽ 128)*

ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ ሣይቀሩ ሀቁን ሣይደብቁ እየተናገሩ <ምናልባትም በመፈረካከስ ላይ ትሆን?> በማለት እየጠየቁ ታዲያ የነአንዱዓለም የሽብርተኝነት ወንጀል ከየት መጣ? እንዴትስ ተፈበረከ? ወገን ጠይቁ::

ማስታወቂያ ሚንስቴር ወዳሣተመው መጽሐፍ ስመልሳችሁ ደግሞ የሚከተለውን ሐቅ ታገኛላችሁ:- *". . .በጎረቤት አገራት* (ዐረቦቹ ለማለት ነው) *በግርድና መኖር እንደፀጋ በሚወሰድባት አገር የሚኖር ዜጋ ካላፈረ፣ ካልተሸማቀቀ፣ ውርደቱ ወገቡን ካልቆረጠው፣ ያገር ፍቅሩ የቱ ላይ እንደሆነ አስቸጋሪ ነው?. . .ያሁኑ ውርደታችን መሠረታዊ ምንጩ ድህነትና ኋላቀርነት ነው:: የዴሞክራሲና የመልካም አሥተዳደር እጦት ነው . . ."* (እንደላይኛው ገጽ 7-8)

እንግዲህ አሁን አገሪቱ ያለችበትን ተጨባጭ ሁኔታ ማስታወቂያ ሚንስቴር ያሣተመው መጽሐፍ አልደበቀም:: በተለይም የመራባችንና የመዋረዳችን ዋንኛ ምንጩ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር እጦት መሆኑን በሚገባ ገልፆታል:: በርግጥም የዐረቦች ገረድ ከመሆን ለዚች አገር ወጣቶች የከፋ ውርደት ሊኖር አይችልም::

ኢሕአዴግ ባንድ በኩል የዴሞክራሲ አፈናና የመልካም አሥተዳደር እጦት መኖሩን ያምናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንኑ የዴሞክራሲ አፈናንና የመልካም አሥተዳደርን እጦት በመቃወም ለውጥ እንዲመጣ የሚታገሉትን የሰላም ታጋዮች በሽብርተኝነት ስም እየወነጀለ እድሜ ልክ በመፍረድ እስር ቤት ይከታል፡፡ ይህ ነገር እንዴት ነው? ብለን ይህንኑ ጥያቄ ይዘን ራሱን ኢሕአዴግን ብንጠይቀው ያለጥርጥር የሚሠጠን መልስ፡-

"አዎን፤ ዴሞክራሲያችን ገና ጨቅላ ነው፤ አላደገም፤ በዚህ ምክንያትም የመልካም አሥተዳደር እጦት አለ፡፡ በተለይም ከላይ ወደታች ሲወርድ ያፈፃፀም ችግር አለ፡፡ ይሁን እንጂ ዴሞክራሲን እየመጠንኩ ትንሽ ትንሽ የማጎርሳችሁ እኔ እንጅ እናንተ እየጠቀለላችሁ ልትጎርሱ አትችሉም፡፡ ለውጥ የሚመጣውም በኔ እንጂ በሌላ አካል ሊሆን አይችልም፡፡ እኔው በኔ ‹በመተካካት› ዴሞክራሲንም ሆነ መልካም አሥተዳደርን በረጅም ጊዜ ሂደት እንደማሰፍን አትጠራጠሩ፡፡ ከኔ ውጭ የሚደርግ የትግል ሥልት ግን ሕገወጥ ብቻ ሣይሆን ሽብርተኝነትም ነው" ብሎ እንደሚመልስ መጠራጠር አያሻም፡፡

እነ አንዱዓለም አራጌ ደግሞ <በምንም መመዘኛ ባፋኙ ኃይል ለውጥ ሊመጣ አይችልም> ባዮች ናቸው፡፡ <መተካካት> የሚባለውም <ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም> እንደሚባለው ዓይነት ነው ሲሉ ይሞግታሉ፡፡ ልዩነታቸውም ከዚህ ላይ ነው፡፡

## መልካም አሥተዳደር እንዴት?

ስለመልካም አሥተዳደር ታላቁ ምሁር ዶ/ር ሐዲስ ዓለማየሁ *<ኢትዮጵያ ምን ዓይነት አሥተዳደር ያስፈልጋታል?>* በተባለው መጽሐፋቸው የሚከተለውን አስፍረዋል፡- *"መንግሥት የሕዝብ እንጂ ሕዝብ የመንግሥት ሊሆን አይችልም"* (ገጽ 13) በሌላ አነጋገር *"መንግሥት የሕዝብ አገልጋይ* እንጂ ሕዝብ አገልጋይ ወይንም ሎሌ ሊሆን አይችልም" ማለታቸው ነው፡፡ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ግን ከዚህ ሀቅና መርህ በእጅጉ የራቁ ናቸው፡፡ የሕዝብ ሎሌ የመንግሥት ጌታ፤ ያውም የታገተ ወይንም የተጠረነፈ ሕዝብ፡፡

እንግዲህ እነ አንዱዓለም አራጌ ከላይ እንደ ተመለከትነው ኢሕአዴግ ራሱ ሊደብቀው ያልቻለውን ከፋፋይ ሥርዓት መልከ እንዲይዝ ታገሉ እንጂ ያረቡ ዓለም የለውጥ ወላፈን እንኳን ሺው እንዲል አልተነፈሱም ነበር፡፡ ለምን ቢባል ያገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አይፈቅድምና፡፡





የኢሕአዴግ እውነተኛ ሥጋትና ፍርሃት ግን ያረቡ ዓለም የለውጥ ማዕበል ወደ አገራችን እንዳይመጣ በፖለቲካው መሥክ ንቁ ተሣታፊ የሆኑትን ወጣት ታጋዮች አስቀድሞ ታፔላ በመለጠፍ ማኮላሸትና ሌሎች ተሸማቀው አርፈው እንዲቀመጡ ለማድረግ ነው፡፡ እውነቱ ይኸ ነው፡፡

የሚያሣዝነውና የሚሰቀጥጠው ደግሞ አንዱዓለም አራጌ ጧት ልጁን ት/ቤት (ሙዋዕለ ሕፃናት) አድርሶ ማታ ሲመለስ ለውጡን ለማየት ፎቶ ለመታሰቢያ ከሕፃን ልጁ ጋር ተነስቶ ነበር፡፡ አባት እንደወጣ ሲቀር ሕፃኑ ማታ ት/ቤት ውሎ ሲመለስ አባቱን ሲያጣው ምን ሊሰማው እንደሚችል መገመቱ ከባድ ነው፡፡ ጧት ማታም እናቱን "እባቴስ?" እያለ ሲጠይቅ እናት የምትሰጠው መልስ ሲጨንቃት ሕሊናዋ ምን ያህል ሊቆስል እንደሚችል እናቶች ካልሆኑ በስተቀር ይህንን ሰቀቀን ማንም ሊረዳው አይችልም፡፡ እንግዲህ እንዲህ ያለው የሰላም ታጋይ ወይንም ለውጥ ፈላጊ ነበር እድሜ ልክ ተሸከሞ ከርቸሌ የተከረቸመው፡፡

አንዱዓለም አራጌ እድሜ ልክ ሊፈረድበት "ጥፋተኛ" ተብሎ የመፈረጃ የፍርድ የማቅለያ ሐሣብ እንዲያቀርብ ፍ/ቤት በጠየቀው ጊዜ፡-

*". . .እኔ በተፈጠርኩበት በዚህ ዘመን ለራሴ፣ ለልጆቼና ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ዴሞክራሲና ነፃነት እንደሚገባን (እንደሚያስፈልገን) በማመን አቅሜ በፈቀደው መጠን ታግያለሁ፡፡ ይህንን በማድረጌ በማንም ላይ በከፋት አልተነሣሁም፤ ሕግም ጥሼ አላውቅም፡፡ በድሃዋ አገሬ ጥቅም ላይም አልተነሣሁም፡፡ ፈጣሪየንም ሆነ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያሣዝን፣ ሕሊናዬን የሚቆጠቁጥ አንዳች ነገር ፈፅሜለሁ ብዬ አላምንም፡፡ ፈፅሞ ሰላም ይሰማኛል፡፡ እኔን ከዚህ ያቆመኝ የነፃነት ናፍቆት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችና ፍትሕ ለምኜ ስነፈግ ይኸ የመጀመሪያዬ አይደለም፡፡ ከሣሾቼ እንድጠጣው የፈለጉትን ጽዋ በፀጋ ከመጠጣት ውጪ ባልፈፀምኩት ወንጀል የማቅለያ ሐሣብ የመጠየቅ አማራጭን ሕሊናዬ ስላልተወለኝ አዝናለሁ"* ነበር ያለው፡፡

ናትናኤል መኮንን በበኩሉ ሲያዝ ከነአንዱዓለም ጋር በተመሣሣይ ቀንና ሰዓት ነበር፡፡ መንግሥት አለ ብሎ ሥራ ውሎ በ79 ቁጥር አውቶቢስ ተሣፍሮ ወደ ቤቱ ሲመጣ መገናኛ ላይ ድልድዩን እንደ ተሻገረ በታጣቂ ኃይሎች ተከቦ ነው የተያዘው፡፡ ይህ በራሱ የከፋ ሽብር ነበር፡፡ ናትናዔል የተያዘው ግን አውቶቢሱን በቦምብ ለማጋየት ቦምብ ይዞ አልነበረም፡፡ የምላ

ሳህኑን በፌስታል አንጠልጥሎ ነበር። እሱም እንደ አንዱዓለም ጥፋተኛ ነህ ተብሎ የመፋረጃ ሐሳብ እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ እንዲህ ነበር ያለው፦

*"ወንድሙን ወንድሙ እየገደለ ሐውልት የሚያቆምበት ዘመን እንዲያበቃ ያቅሜን አስተዋፅኦ ለማድረግ ሰላማዊ ትግል አድርጌያለሁ። ይህንን በማድረጌ አልቆጭበትም!"*



*የ18 ዓመት ፍርደኛ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ*

እውቁ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ሲያዝም በተመሣሣይ ሰዓትና ቀን ነበር። ህፃን ልጁን (ናፍቆትን) ከት/ቤት አውጥቶ በግል መኪናው ይዞ ወደ ቤቱ ሲሄድ ከመንገድ ተከቦ ነው የተያዘው። ህፃኑ ናፍቆት አባቱን ከነጣቂዎች ለማስለቀቅ በትንኝ አቅሙ በካልቾና በጡጫ ተፋልሟል። የፀጥታ ኃይሎቹ





እግዜር ይስጣቸው፤ ናፍቆትን ሽብርተኛ ብለው ካባቱ ጋር ቀላቅለው ወደ እስር ቤት አልወሰዱትም። እናቱን ጠርተው ነው ያስረከቧት። በዚህ ተግባራቸው ሊመሠገኑ ይገባቸዋል። ይች አገር ጨርሳ ወደ አረመኔነት አለመሸጋገሯ ተመስጌን የሚያሰኝ ነው። አጅሬ ኢጋዚ ቢሆን ኖሮ ግን የህፃን ናፍቆት አጥንት ስብርባሪ እንኳን አይገኝም ነበር። በነገራችን ላይ ህፃኑ ናፍቆትን እናቱ ሠርከዓለም ፋሲል የተገላገለችው (የወለደችው) በ97ዓ.ም ቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ነበር። እንግዲህ የዚች አገር የፖለቲካ ከፋትና ዝቅጠት እስከዚህ ድረስ የወረደ ነው።

ውድ ወገኖቼ፤ እንግዲህ በህፃን ናፍቆት አእምሮ ውስጥ ምን ተፀንሶ የሚያድግ ይመስላችኋል? አንዳንድ ጊዜ በግሌ ሣስብ እነዚህ "የሕዝብ ብሶት ወለደን" የሚሉ የሕወሓት ተጋዳላዮች ወላጆቻቸው ምን ዓይነት የጭካኔ መርዝ እየጋቱ አሣደጓቸው? ብዬ እጠይቃለሁ። እናንተም ጠይቁ። ለማንኛውም እስክንድር ነጋም የመፋረጃ ሐሳብ እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ የሰጠው መልስ እነሆ፦

*"ሀገሪቱ ውስጥ ሕጋዊና ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር መምጣት እንዳለበት እንደ ጋዜጠኛነቴና እንደ ዜግነቴ ስለማምን ልጽፍ የሚገባኝን ጽፌለሁ። ይህንን በማድረጌ ሕሊናዬን የሚቆጠቁጠኝ ነገር የለም!"*

እንግዲህ ይህንን ሁሉ ያፈና መዋቅር የዘረጉና በኋላም ዜጎችን በዘመቻ እየተለቀሙ እስር ቤት እንዲታጎሩ የመሩ "ታላቁ መሪያችን" ነበሩ። ይባስ ተብሎ ዛሬ በሙት መንፈሳቸው እንግዛችሁ ስንባል ደግሞ እጅግ አድርጎ የሚቆጠቁጥ ነው።



*የ18 ዓመት ፍርደኛ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ*

# ሽብር ፍለጋ ሞቃዲሾ ድረስ?

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ጎልታ ከምትታወቅባቸው ቁምነገሮች መሀከል አንዱና ዋናው የራሷን ስንዝር መሬት አሣልፋ የማትሠጥ፣ የሌሎችንም ቅንጣት የማትፈልግ መሆኗ ነው። ሁልጊዜም በተከላካይነት እንጂ አንድም ጊዜ አቅም አለኝ ብላ ባጥቂነት ወሰን አልፋ ወይንም ደንበር ጥሳ ጎረቤት አገራትን ወራ ወይንም ተንኩሣ አታውቅም። ይህ የተከበረ የሦስት ሺ ዘመን ታሪኳ በዚህ ትውልድ ግን በጦር ጠማኙ ኢሕአዴግ እጅ ላይ በመውደቋ ምክንያት መልካም ገፅታዋ እንደ በረዶ ክምር ቀልጦ ወይንም ተንዶ ወሰን ጥሳ ጎረቤት አገር ሶማሊያን ወረረች።

ኢሕአዴግ <ባሸባሪነት> ስም የገዛ ዜጎቹን የሚያምሰው አንሶ ደንበር ተሻግሮ ሶማሊያን በመውረር ያሜሪካንን ደም ሲበቀል ለኢትዮጵያ ደግሞ የዘለዓለም ደም በመትከል ጠላት ገዝቶላታል። ምንም ዓይነት የደንበር የይገባኛል ጥያቄ ሣይኖረን ወይንም እንደ 69 ዓ.ም 700 ኪሎ ሜትር ዘልቃ ሣትወረን አቶ መለስ ሠራዊታችን ሞቃዲሾ ድረስ ዘልቆ (በሕግ አስከባሪነት ስም) እንዲገባ ትእዛዝ የሠጡበት ምክንያት ለምንድን ነው? ካንድ "ዴሞክራት መሪ ነኝ" ከሚል የሚጠበቅስ ነበር ወይ? እነዚህን ጥያቄዎች ይዘን ስንቶቹስ ሞቱ? ስንቶቹስ ቆሰሉ? ስንቶችስ አሸዋ በልቷቸው ቀሩ? በውጤቱስ ኢትዮጵያ ምን አተረፈች? መልስ ሰጭ አካል ባታገኙም ጠይቁ።

ርግጥ ነው ሶማሊያና ሱዳን ለኢትዮጵያ መልካም የሚባሉ ጎረቤቶች አይደሉም። መቸም ይሁን መቸ ጥሩ ጎረቤቶችም የሚሆኑ አይደሉም። ሱዳን የደንበር ጥያቄ ባይኖራትም ከግብፅ ጋር በማበር በዚሁ መከረኛ ዓባይ ወንዝ ምክንያት ልክ እንደዚህ ቀደሟ መገዝገዟን አታቆምም። ከዚህ ቀደም ለኤርትራ ገንጣዮችና ለሕወሓት አስገንጣዮች ሁለንተናዊ ድጋፍ በመስጠትና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንደ ዋና መሠረት በመሆን የጁን እስካገኘችበት እለት ድረስ የልቧን ሠርታለች። ወደ ፊትም ለኛ በጎ ነገር ታስባለች ተብሎ አይጠበቅም። ትልቁ ቁምነገር ባጠመደችው ወጥመድ ወይንም በዘረጋችው አሽከላ መሸምቀቋ ነው። ኤርትራን ከኢትዮጵያ አስገንጥላ እኛን አሣዘነችን። እሷም ልታጣ የማትችለውን ለም አገርና የነዳጅ ክምችት ያለበትን ደቡብ ሱዳንን አጣች። <አትዋል ይዋሉብህ አትምከር ይምከሩ፤ በቆፈሩት ጉድጓድ ሣይገቡም አይቀሩ!> የሚባለው እንዲህ ያለው ነገር ነው። አንድ አገር ከዋናው አካል ሲገመስ ምን ያህል እንደሚያሣዝንና





እንደሚያም ሱዳን ቀመሰችው። በቆፈረችው ጉድጓድ ያለ አፈር መላሽ ገባችበት። ወደ ሶማሊያ ስንመለስ ደግሞ ሁኔታው ሌላ ነው።

እንደሚታወቀው ሶማሊያ ከኢትዮጵያ የመሬት ጥያቄ አለኝ በሚል በተደጋጋሚ ስትቱነኩስ መኖሯ ይታወቃል። በተለይም በ69 ዓ.ም እኛ በለውጥ ማዕበል እየተናጥን በነበርንበት ወቅት አጋጣሚውን ተጠቅማ ጊዜው አሁን ነው በሚል ድሬዳዋ ድረስ ዘልቃ ወራናለች። ዜያድባሬ በሕልም ግመል እየጋለበ ኢትዮጵያን ብቻ ሣይሆን ሶማሊያንም በጎሣ አናክሶ በመጨረሻ አፈራርሶ እሱም ሣያምርበት ካገሩ ተባሮ የትም ወድቆ ቀረ።

ሶማሊያ ልክ እኛ በ69 ዓ.ም ውጥረት ላይ በነበርንበት ወቅት አመች ጊዜ ጠብቃ በእብሪት እንደ ወረረችን ሁሉ እኛም ዛሬ እሷ መንግሥት አልባ ሆና በጦር አበጋዞቿ እየታመሠች ባለችበት ወቅት ገና ለገና <የተለያዩ የእስልምና አክራሪዎች ወይንም አሸባሪዎች ምሽግ ልትሆን ትችላለች> በሚል ሥጋት በልዕለ ኃያሏ አሜሪካ አደፋፋሪነት የኢትዮጵያ ሠራዊት ሞቃዲሾ ድረሽ ዘልቆ መግባቱ ጀግንነት ሣይሆን አንገት የሚያስደፋ ነበር።

ኢትዮጵያ ጣልቃ መግባት ካለባትም እንደተለመደው በጨዋ ደረጃ ለማንም ሳትወግን እንደ ጥንቱ ክብሯን ጠብቃ በጎረቤት አገር ወግ ሸማግሌ ወይንም አደራዳሪ ሆና ነበር መቅረብ የነበረባት፤ ክብሯን ዝቅ አድርጋ ለኮሎኔል አብዱላሂ ዮሱፍ ወግና ፍልሚያ ውስጥ መግባቷ ግን አሣፋሪ ነበር። ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሞቃዲሾ ድረስ የዘመተበት ምክንያት ምንድን ነው? እውን ሽብርተኞችን ፍለጋ ነው? ብለን ስንጠይቅ የሚከተለውን መልስ እናገኛለን፡-

<አልቃዒዳ ወይንም ሽብርተኝነት> በምስራቅ አፍሪካ ቀንድ ማለትም በመንግሥት አልባዋ አገር ሶማሊያ እንቁላሉን እየጣለ ነው፤ ሣይፈለፈል ከዚያው ላይ ወይንም ባለበት ገምቶ እንዲቀር አሜሪካ ሰላም አስከብራለሁ በሚል የኢትዮጵያ ሠራዊት ከመግባቱ በፊት ቀድማ ገብታ ነበር። ይሁን እንጂ የሶማሊያ ፋኖዎች ያሜሪካንን ወታደሮች ገለው በሞቃዲሾ ጎዳናዎች ለመቀጣጫነት ሬሣቸውን በመጎተት ዘግናኝና አሣፋሪ የዘላን ተግባር ፈፀሙ። ይህ ድርጊትም ያሜሪካንን ባለሥልጣናት በእጅጉ አስቆጣቸው። አርፈው እንዲቀመጡም አላስቻላቸውም። የምር እነዚያን ፋኖዎች ለመቅጣት ታጥቀው ተነሱ። ይህንን የበቀል ቀመር ሲቀምሩም በነጭ ወታደር ሊቋቋሟቸው እንደማይችሉ ቀድመው አውቀዋል። በመሆኑም "እሾህን በሾህ" እንዲሉ ወይንም "ጥቁርን በጥቁር" ከዚያው ጎረቤታሞችን

እስበሳቸው ማስተናነቅ እንደሚቻል ስልት ቀየሱ:: ለዚህ ስልትም ኢትዮጵያ ተመረጠች::

ያ ወቅት ደግሞ ኢሕአዴግ በቅንጅት የተሸነፈበት ወቅት ስለነበር <ድምፃችን ይከበር> ባሉ ወጣቶች ላይ በወሠደው አሸማቃቂ የግድያ ርምጃ በዓለም ዙሪያ ውግዘትና ጩኸት የበዛበት በመሆኑ አይከፍሉ መሥዋእትነት ከፍሎ ወይንም አሜሪካ የጠየቀችውን ባውንታ ተቀብሎ ያንን አሥፈሪ ጊዜ ከሷ ሥር ተሸጉጦ ማለፍ ነበረበት:: በመሆኑም ሁለቱ ተፈላላጊዎች ጊዜ አገናኘቻቸውና ባሜሪካ ያፍሪካ ጉዳይ ኃላፊዋ በጄንዳይ ፍሬዘር በኩል በሚስጢር አለቀ:: ከዚህ በኋላ አሜሪካ የቅንጅትን ጉዳይ ቀዝቃዛ ውሃ ቸለሰችበት:: አንዲት ነገር ሣትተነፍስ <ውሾን ያነሳ ውሾ> ብላ ጭጭ እንዳለች ቀረች::



*ያውሮፓ ኅብረትን ወክለው የታዛቢዎች ሰብሳቢ የነበሩት ወ/ሮ አና ጎሚዝ*

ያውሮፓ ኅብረትን ወክለው የታዛቢዎች ሰብሳቢ የነበሩት ወ/ሮ አና ጎሚዝ (በኢትዮጵያውያን አጠራር ሐና ጎበዜ) ጩኸት ውሃ በልቶት ቀረ:: ከዚህ በኋላ ነበር ጠ/ሚንስትር መለስ ለወጉ ያህል ፓርላማ አቅርበው ጦሩ አሸባሪዎችን የትም ይሁን የትም፣ ከገቡበት ገብቶ መዋጋት እንዳለበት ም/ቤቱን አሣምነው ሶማሊያ እንዲገባ ያስወሰኑት፣ ሀቁ ይኸ ነው::





ከዚህ ውጭ ግን አሸባሪዎች ሶማሊያ ውስጥ ኖሩም አልኖሩ እሷ በራሷ ለኢትዮጵያ መቸም የማትተኛ አሸባሪ ነች:: ይህ ሁሉ እንግዲህ ኢሕአዴግ የሚጓዝበት ስህተትን በስህተት የማረም አባዜ ነው::

ሶማሊያ የሠራዊታችን ዘው ብሎ መግባት ከቤንዚን ላይ ከብሪት እንደመጫር የሚቆጠር ነው:: በሷ ምክንያት በተዘዋዋሪም ቢሆን ያረቡን ዓለም ጥርስ እንደሚያስነክሱብን መወቅ አለበት:: ምንም ይሁን ሳትተነኩሰን በራሷ ችግር ተጠምዳ ባለችበት ወቅት ሽብርና ሽብርተኞችን ፍለጋ ሞቃዲሾ ድረስ መሄድ አልነበረብንም:: የዚህ ሁሉ ስህተት ድምር ውጤት "የታላቁ መሪያችን" መሆኑ ደግሞ በግልፅ ሊታወቅ ይገባዋል:: ወደፊት ወይ በኛ እድሜ ወይ ዘግይቶ ትውልድ እዳ ከፋይ እንደሚሆን ቅንጣት የሚያጠራጥር አይደለም:: እስከዚያው ግን እግዚአብሔር ተሸብረው ከሚያሸብሩና በሙት መንፈስ እንግዛችሁ ከሚሉ ይጠብቀን!!

<><><>



*የውሮፓ ኅብረትን ወክለው የታዛቢዎች ሰብሳቢ የነበሩት ወ/ሮ አና ጎሚዝ*

# ክፍል ሦስት

*አልሆን ብሎ ነገሩ ሲጠጥር*
*ሳቡት ካቦውን የላላው ይወጠር!*

## አንቀጽ 39 እንደ ዋሥትና

አንድ ሰው ቤት ለመሥራት ሲያስብ መሠረቱ የሚያርፍበትን አፈሩን በሙያተኞች ማስመርመር አለበት:: የሚነቃ፣ የሚናድና የሚንሸራተት መሆን አለመሆኑን በጥንቃቄ ማወቅ አለበት:: መሠረቱ በጥሩ ሁኔታ የተጣለና ተዋቅሮ የተሠራ ቤት ላደጋ የተጋለጠ አይሆንም:: መሠረቱ በጥሩ ሁኔታ ያልተጣለና በሚገባ ተዋቅሮ ያልተሠራ ቤት ከሆነ ግን በትንሽ ነገር መፍረሱና መደረማመሱ ምንም ጥርጥር የለውም:: እንደዚሁም ሁሉ ለነገ እንዲተርፍ ሆኖ በሥርዓት ያልተዋቀረና መሠረቱን ያልጣለ መንግሥት ከሆነ መፍረሱና መደረማመሱ አይቀሬ ነው:: ዛሬ ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ ይህንኑ ሀቅ አመላካች በመሆኑ አሥፈሪ ነው:: ጎሣን መሠረት አድርጎ በቋንቋ መሥፈርትነት የተዋቀረ በመሆኑ ለዘለቄታ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም::

የዘውዱ ሥርዓትም ሆነ የደርግ ኮሙኒስታዊ ሥርዓት የሕዝቦችን ጥቅምና መብት ሊጠብቁና ሊያስከብሩ ባለመቻላቸው ሊወድቁ ችለዋል:: ዛሬ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትም <አብዮታዊ ዴሞክራሲ> በሚል ፍልስፍና ቀፍድዶ በመያዝ ሕዝብ ፀጥ ብሎ ሲገዛ የሰላም አባት መስሎ በሸንበቆ ከዘራ ሊገዛ ሕዝብ <መብቴን> ብሎ ሲጠይቅ በጥይት እየቆላና ባሸባሪነት ስም እየወነጀለና እድሜ ልክ እየፈረደ ሊገዛ ከቶ አይቻለውምና እየገነባው ያለው ሥርዓት በድቡሽት ላይ የተሠራ ለመሆኑ እንኳን ሕዝቡ ኢሕአዴግ ራሱ ደህና አድርጎ ያውቀዋል::

ኢትዮጵያ ቢያንስ ከ85 በላይ የሚሆኑ ብሔር ብሔረሰቦች፣ ጎሳዎችና ነገዶች እንዲሁም የኅብረተሰብ ክፍሎች ያሏት አገር ናት:: እነዚህ ብሔር





ብሔረሰቦች፣ ጎሳዎችና ነገዶች ካራት የነገድ ሥሮች የተገኙ ናቸው:: እነሱም:-

1.ሴም 2. ኩሽ 3. ዖሞዎ 4. ናይሎቲክ ናቸው:: በመሠረቱ የዚህ ጽሑፍ ዓላማና ተልዕኮ ስለኢትዮጵያውያን ነገዶችና ጎሳዎች ምንነት ተንትኖ ለማስረዳት አይደለም:: ትልቁ ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከነዚህ አራት የነገድ ሥሮች የተገኙ መሆናቸውንና የደም ትሥሥር ያላቸው መሆኑን ጠቁሞ ለማለፍና ተገንጥለውም ለየብቻቸው ሊኖሩ እንደማይችሉ አእምሮ ላላቸው ግንዛቤን ፈጥሮ ለማለፍ ነው::

እንግዲህ ከነዚህ አራት የዘር ግንዶች የተገኙ ብሔር ብሔረሰቦችና ጎሳዎች ከረጅም ጊዜ ጀምረው ባንድ የመንግሥት ጥላ ሥርና ባንድ መልከዓምድር አብረው በመኖራቸው የደጋው ወደ ቆላው በመውረድ፣ የቆላው ወደ ደጋው በመውጣት በጦርነት፣ በንግድ በደጅ ጥናት፣ የጌታ በማደር፣ በፍልሰት፣ በስደት፣ ከቀያቸው በመራቅ አንዱ ከሌላው በመጋባትና በመዋለድ የደም ውህደትን ፈጥረዋል:: በመሆኑም ዛሬ ንፁህ አሮሞ ነኝ፣ ንፁህ ትግሬ ነኝ፣ ንፁህ አማራ ነኝ፣ ንፁህ የዚህ ጎሳ ወይንም የዚያ ነገድ አባል ነኝ የሚሉ ካሉ እነሱ የዋሆች ናቸው፤ ወይንም እንደ ሕወሓት አባላት በዘር በሽታ የተለከፉ ናቸው:: ለደም ውህደታችን ትልቁ ማስረጃችን ደግሞ የጠይም ውቦች መሆናችን ነው::

ጠይምነት እንዴት? ለሚለው ጥያቄ መልሱ የዓለም ሕዝቦች የዘር ግንዶች ሦስት ናቸው ተብሎ ይታመናል:: እነሱም:-

1. *ነጭ - ያውሮፓ ሕዝቦች አባት*
2. *ብጫ (ቀይ) - የኤሽያና የመካከለኛው ምሥራቅ ሕዝቦች አባት*
3. *ጥቁር - ያፍሪካ ሕዝቦች አባት ናቸው ተብሎ ይነገራል:: ይህ ሲባልም ቀለማቸውን (መልካቸውን) መሠረት ተደርጎ እንጂ በሰው ዘርነታቸው የተለያዩ አንዱ ከሌላው ትስስር የላቸውም ማለት አይደለም::*

እንግዲህ ጠይምነት እንዴት ለሚለው ጥያቄ መልሱ ኢትዮጵያኖች ከጥቁርና ከነጭ ይበልጠውንም ካጎራባች ሀገራት ካረቦቹና ከሕንዶቹ በቀይ ባሕርና በዔደን የባሕር ሠላጤ በንግድም፣ በፍልሠትም፣ በስደትም ወደ አፍሪካ ምድር ሸገር እያሉ ከኗሪው ጥቁር ሕዝብ ጋር በመጋባትና በመዋለድ ውብና ማራኪ የሆኑ የጠይም ፍልቅልቅ ሕዝቦችን ፈጠሩ:: ያልጠቆሩ፣ ያልነጡ፣ ወይንም ብጫ ያልሆኑ፣ በመጠንም ያልረዘሙ፣ ያላጠሩ ልከኛ ቁመት ያላቸው ተገኙ::

ይህ ጠይምነትም ባጭር ጊዜ ውስጥ የተገኘ መልክ አይደለም:: የረጅም ጊዜ አዝጋሚ የታሪክ ጉዞን ያስቆጠረ ነው:: ይህ ሂደት ዛሬም ቢሆን አልተቋረጠም፤ እንደ ቀጠለ ነው:: ለዚህም ነው የምሥራቅ አፍሪካ ሕዝቦች <አፍሮ አኻያን> እየተባሉ የሚጠሩት::

ታዲያ ዛሬ ዓለም እንደ ሙዳይ እየጠበበች በመጣችበት ወቅት <የዚህ ጎሳ፣ የዚያ ብሔረሰብ> እየተባባልን ቡድን ፈጥረን በጥላቻ የጎሪጥ መተያየታችንና መፋጠጣችን ለምን ይበጅ ይሆን? ዘመኑ ዘመነ ቴክኖሎጂ በሆነበት ወቅት እኛ ወደ ኋላ መቅረታችን ሊቆጨን ሲገባ፣ ጠላታችንም ኋላ ቀርነታችን ሆኖ ሳለ እሱን አንድ ሆነን ታግለን ማሸነፍ ስንችል አንዱ ጎሳ የሌላው ጎሳ ጠላትና ደመኛ እንደሆነ አድርገን በሕዝቦች መሀከል የጥላቻ መርዝ እየረጨን በጨለማ ውስጥ እንደሚከንፉ የሌሊት ወፎች መሆናችን አሣሳቢ እየሆነ መጥቷል:: ቢበቃን በተገባ ነበር:: ግን የሚበቃንና የሚጠቅመን አልሆነም:: ገዥዎቻችን ገና ሰላም አልናፈቃቸውም::

ገና ከማለዳው ያንድ መንደር ልጆች በወጣትነት ስሜት ቂምና በቀልን ቋጥረው በመሠባሰብ የመግቢያ በሩን እንጂ የመውጫ በሩን በቅጡ ሣያስተውሉ ያረጀ ያፈጀ ኮሚኒስቶች አላምጠው የተፉትን <የብሔር ጭቆና> በሚል <እስከ መገንጠል> የሚያደርስ መርህ ነድፈው መንቀሳቀሳቸው ሕወሓቶች ትልቅ ጥፋት ነበር የሠሩት:: ሕወሓቶች የትግራይን ክልል ከሌላው የኢትዮጵያ አካል ገንጥለው እንደ ሀገር ለማቆም የጥላቻ ሥንቅ ሰንቀው በረሃ መግባታቸው ዛሬም ድረስ ያለቀቃቸው ትልቅ የዘር በሽታ ነው የተጠናወታቸው:: በምንስ መመዘኛ ነው "የትግራይ ነፃ አውጭ" ተብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪ መሆን የሚቻለው? ጠይቁ::

21 ዓመታት በመንግሥትነት ተጉዘው እንኳን ከጎሣ አምላኪነት አለመላቀቃቸው በራሱ ከፉ የዘር ህመም እንደተጣባቸው በቂ ማረጋገጫ ነው::

የሕወሓት አባላት ገና ከመነሻቸው <የብሔር ብሔረሰቦች ጭቆና> ይዘው በረሃ ሲገቡ መፍትሔው <እስከ መገንጠል ድረስ> እውን ማድረግ ነው ብለው አምነዋል:: ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ሕገ-መንግሥታዊ እውቅና ሠጥተዋል:: ኢሕአዴግ <እስከ መገንጠል ድረስ> መብት የሚሠጠውን አንቀጽ 39ኙን ሲያፀድቅ አንድ አዛውንት ሙስሊም ከመደሰታቸው የተነሣ እየዘለሉ ባዳራሹ ውስጥ ሲቧርቁ የራሳቸው ቆብ (ኩፍያ) ወልቆ ነበር:: ዛሬ እኒያ አዛውንት ሙስሊም ምን ያህል እንደ ተሣካላቸውና ምን እንዳገኙ





አናውቅም:: ምናልባትም ሳያልፍላቸው አልፈው ይሆናል:: ለሕዝቡ ግን ጠብ ያለለት ነገር የለም:: ኢሕአዴግ <እስከ መገንጠል> መብት የሚሰጠውን አንቀጽ 39ኙን ሕገ-መንግሥታዊ እውቅና ሲሠጥ አምኖበትና የዘለቄታ መፍትሄ ይሆናል ብሎ አስቦ ሣይሆን ሕዝቦች በጥርጣሬና በጥላቻ እስበሳቸው የጎሪጥ እየተያዩ ሲፋጠጡ የሥልጣን ዕድሜው እንደሚረዝም በማመኑ ነው:: በመሆኑም ዛሬ አንቀጽ 39ኙን ለሥልጣኑ ማቆያ እንደ ዋሥትና እየተጠቀመበት ነው:: <እኔ ካልገዛኋችሁ ኢትዮጵያ ትፈራርሳለች> እያለም ያስፈራራል:: የሥልጣን ተቀናቃኞቹ እንኳን እሱ በቀደደው መስኖ እየፈሰሱ፣ አንድ ሆነው ስለአገር ማሰብ ተስኗቸው ግን ደግሞ እሱን <ጎሠኛ> እያሉ ሲያወግዙ ትንሽ እንኳን ሀፍረት አይሠማቸውም::

በመሠረቱ እንደ ኢትዮጵያ ያለችን የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች አገር ለመምራትና ለማሥተዳደር ጥበብንና ብልሃትን ይጠይቃል:: የመጀመሪያው ምንም አይነት ጎሣዊ አድልኦ ሣያደርጉ በእኩልነት መምራት ሲቻል ነው:: የሕወሓት <ልሂቃን> ደግሞ እንዲህ ዓይነቱ መርህ አይዋጥላቸውም፤ አያውቁትም:: በመሆኑም አንዱ ብሔር የሌላው ብሔር ጠላት እንደሆነ በመቀስቀስና በማራገብ <እስከ መገንጠል> የሚል መርህ በመቅረጽ ሕገ-መንግሥታዊ እውቅና በመሥጠት የገዛ ዜጎቹን አቧድኖ ለማፋለም የሚያፋጥጥ መንግሥት በዓለም ላይ አለ ከተባለ የኢሕአዴግ መንግሥት የመጀመሪያ ነው: በኢትዮጵያ እስከ ዛሬ ድረስ ይካሄዱ የነበሩት ደም አፋሳሽ የእሰበሰ ጦርነቶች <ጉብር አልገብርም> በሚል እንጂ <እገነጠላለሁ አትገነጠልም> በሚል አልነበረም::

ሕወሓት በኋላ ባምሳሉ የፈለፈላቸውን ኃላፊነት የመሸከም አቅምና ችሎታ የሌላቸውን ከጎኑ በማሰለፍ ኢትዮጵያውያንን በጎሳ ለማስተናነቅ ሲነሣ ቀደምት ነገሥታት የሠሩቸውን መልካም ተግባራት አሻራቸውን ከታሪክ ማኅደራት ለመፋቅ እንዲያመቸው ስንት በጎ ነገሮች እያሉ ለማሣመንና ተቀባይነት እንዲያገኝ ከፉ ከፉ ነገሮችን እየነቀሰ በማውጣት ባብዛኛውም እንደ ብሥራት አማራ የፈጠራ ድርሳናትን በቅጥፈት በማጨቅ አንዳንድ ጊዜም ዶክሜንተሪ ፊልሞች ሣይቀር በማቅረብ አንዱን ብሔር ገዥና ረጋጭ ሌላውን ብሔር ተገዥና ተረጋጭ በማስመሰል መስበክና በሕዝቦች ሕሊና ውስጥ ጥላቻና ከፋትን ማስረፅ ነው:: የዚህ እኩይ ተግባር ሰለባ የሆኑት ቀደም ሲል እንዳየነው በብሥራት አማረ ሣይቀር የተንበሳቆሉት የመጀመሪያው አፄ ምኒልክ ናቸው:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም ቢሆኑ የሕይወት ዋጋ ቢከፍሉም የጎሳ በሽታ ነውና አፅማቸው ከመወቀስ

አላመለጠም። ዘመኑ ርቆ ሌላ ዘመን ውስጥ ያለን ብንሆንም አፄ ቴዎድሮስም ከመወቀስና ከመዘለፍ ይባስ ተብለውም በሚያስገርም ሁኔታ ባሪያ ፈንጋይም ነበሩ ተብለዋል። ይህንን ሀቅ ለመረዳት በቅንጭብጫቢም ቢሆን ነገሥታቱ የነበሩበትን ዘመንና የተጓዙበትን አስቸጋሪና የፈተና ወቅት እንዴት እንዳለፉትና እንዴት እንደተጋፈጡት ለመዳሰስ ይሞክራል። እግረመንገዳችንም የዘመናችን የቅጥፈት ሥንክሳር ማጋለጥ የግድ እየሆነ መጥቷል።

<><><>





# አፄ ቴዎድሮስ



*አፄ ቴዎድሮስ*

እንደሚታወቀው አፄ ቴዎድሮስ በተነሱበት ወቅት የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ የተለየ መልክና ቅርፅ ነበረው። ባገር ውስጥ ማዕከላዊ መንግሥት ተዳክሞ በጎጥ መሣፍንት ኢትዮጵያ እየታመሠች ነበር። አንዱ ራስ ወይንም ደጃዝማች ሌላውን ራስ ወይንም ደጃዝማች <ገብር አልገብርም> በሚል በየቀኑ ፍልሚያ የሚገጥሙበት ወቅት ነበር። በዚያ ዘመን ገበሬው አርሶ ማምራት፣ ወልዶ መሣም፣ አሣድጎ መዳር፣ ነጋዴው ነግዶ ማትረፍ የሚቻልበት አልነበረም። ከሠቆቃውና ከምሬቱ ብዛት የተነሣ ኢትዮጵያኖች ሰው ሆነው የተፈጠሩበትን እለት ይረግሙ ነበር ይባላል።

በውጭ የነበረው የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ ቅኝ ገዥዎች አፍሪካን፣ ኤዥያን፣ ላቲን አሜሪካን እንደ ቅርጫ ሥጋ እየተቀራመቱ



*አፄ ቴዎድሮስ*

የነበሩበት ወቅት ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ግን ነፃና ሉዓላዊት ሀገር የነበረች ቢሆንም ከቅኝ ገዥዎች በከፋ መልኩ በመሣፍንት እየታመሰች ነበር፡፡

እንግዲህ ካሣ (አፄ ቴዎድሮስ) በዚህ ውጥንቅጡ በወጣበት ወቅት ነበር የሕዝብ እንባና ሰቆቃ አምጦ የወለዳቸው፡፡ በመሆኑም በዚያን ዘመን የገነኑ የጎጥ መሣፍንትን እስከነ ሥርዓታቸው መንግሎ ለመጣል ቴዎድሮስ ጨከን ያለ ርምጃ ከመውሰድ ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም፡፡ የሆነውም ይኸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የዘመነ መሣፍንትን አስከፊነት በቅጡ ያልተረዱ ወገኖች አፄ ቴዎድሮስን ከልክ ያለፉ ጨካኝና አረመኔ አድርገው ይሥሏቸዋል፡፡ ሀቁ ግን አፄ ቴዎድሮስ ሩኅሩኅም፣ አዛኝም፣ ምህረትን የሚያውቁ እንደነበሩ የሣቸው እሥረኛ የነበረው ዶ/ር ሄኔሪ ብላንክ ሣይቀር መሥክሮላቸዋል፡፡ ባንድ ወቅት አንዲት ምንትዋብ የምትባል ሴት፡-

*"ሥጋም እንዳያምረኝ ቋንጣ ሰቅያለሁ*
*ሲሻኝ ከወንድሜ ካባቱ እበላለሁ፡፡*
*ሺ ፈረስ ከኋላው ሺ ፈረስ ከፊቱ*
*ይህን ሳታይ ሞተች ኮሶ ሻጭ እናቱ!*
*ይህንን ሲሰማ ያጎራል ላመሉ*
*ማናትም ቢላችሁ ምንትዋብ ናት በሉ!'* በማለት መሣደቧ ለቴዎድሮስ ይነገራቸውና ተይዛ ትቀርባለች፡፡ መኳንንቱ ገሚሱ <ንጉሣችን ተሣድባለችና መሠቀል አለባት> ሲል ቀሪው ደግሞ <የለም ሴት ነችና ባይሆን ዳግመኛ እንዳይለምዳት አርባ ጅራፍ ተገርፋ ትለቀቅ> በማለት የየራሱን ፍርድ ይሠጣል፡፡ ቴዎድሮስ የመኳንንቱን አስተያየት ካዳመጡ በኋላ ወደ ሴትዮዋ መለስ ብለው፡-

"እቴ፤ እንዲያው ምን በድየሽ ነው የምትሰድቢኝ?" በማለት ሲጠይቋት፡-

"አባ ታጠቅ፤ ከዚህ የበለጠ ምን ሊበድሉኝ ኖሯል? ወንድሜን፣ አባቴን ገለውብኛል" ስትል መለሰችላቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ስሜታቸው ይነካና አንገታቸውን ደፍተው ለትንሽ ጊዜ ተከዘው ከቆዩ በኋላ ቀና በማለት ወደ መኳንንቱ አትኩረው እየተመለከቱ፡-

"ታዲያ ይህንን የመሰለ በደል ፈጽሜባት እኔን እንድታሞግስ ትፈልጉ ኖሯል?" በማለት ከወቀሷቸው በኋላ ዘጌ ማደሪያ ጉልት እንደ ሰጧት ዶ/ር ሄነሪ ብላንክ ጽፏል፡፡ ይሁን እንጂ ሴትዮዋ በሰጧት ጉልት አልተጠቀመችበትም፡፡ እስከ እልፈተ ሕይወታቸው ድረስ በሄዱበት እየሄደች ግብረ በላ ሆና ደስ ሲላት ስታሞግሳቸው ሲከፉት ደግሞ ስትሰድባቸው





ኖራለች፡፡ ይህ እንግዲህ ምህረትንና ይቅርባይነትን የሚያውቁ ለመሆናቸው ማረጋገጫ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ አፄ ቴዎድሮስ እንደማናቸውም ሰው የሚያዝኑና የሚጨነቁ መሆናቸውን የገለፁበት አጋጣሚ የሚወዷት ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች በሞት ሲለዩዋቸው፡-

*"እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሣትሄድ*
*እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ?*
*እጅግ ሥራ አዋቂ ትናትና ሞተች*
*መድኃኒቱን ምሣ ታበላኝ ነበረች!"* ሲሉ ስቅስቅ ብለው ማልቀሳቸው ትዕይነገርላቸዋል፡፡*(አፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት ገጽ 185)*

እንዲሁም ብላንክ ግሥተኛነታቸውን ሲገልፅ እንዲህ ብሏል "አፄ ቴዎድሮስ በራሳቸው ጉዳይ መታገሥ ይችላሉ፡፡ ባገር ጉዳይ ላይ ግን ፈጽሞ ትእግሥት የላቸውም" ሲል አግራሞቱን በተመሣሣይ መጽሐፍ ገልፆል፡፡

አፄ ቴዎድሮስ ሌላው ታላቅነታቸውን ያስመሠከሩበትና ላገራቸው ቀናዒ እንደነበሩ የገለፁበት አጋጣሚ ደግሞ ሣያወላውሉ በራሳቸው ላይ የወሰዱት ቆራጥ ርምጃ ነበር፡፡ ንጉሥ ነገሥቱ የሚመኩበትና የሚተማመኑበት የጦር መሪያቸው ፊታውራሪ ገብርዬ ከሮበርት ናፒዬር ጦር ጋር ተፋልሞ መሰዋቱንና በርካታ ታማኝ ወታደሮቻቸውም መሞታቸውን ሲነግሯቸው እጅግ አድርገው አዝነው፤ አግተዋቸው የነበሩትን ወይንም ለፍልሚያው ምክንያት የሆኑትን ያውሮፓ እስረኞችን ፈተው ከለቀቋቸው በኋላ ከድንጋይ ላይ ተቀምጠው በሁለት እጆቻቸው ራሳቸውን ደግፈው አቀርቅረው ማዘን ሲጀምሩ ራስ እንግዳ፡-

"ለምን ያዝናሉ? እነዚህን ነጮች እንመልሳቸውና ገለን ወይንም ተዋግተን እንሙት!" ሲሏቸው ተቆጥተው፡-

"አንተ ጅል ባለፈው ሁለት ቀናት ውስጥ የፈጀሁት ሰው አይበቃኝም? እነዚህን ነጮች ገድዬ አበሻን በደም እንዳጥባት ነው የምትፈልገው?" ብለው እንደመለሱላቸው ብላንክ በመጽሐፉ በገጽ 30-31 አብራርቶ ጽፏል፡፡ በመጨረሻዋ ሰዓት ይህንን ማለታቸው በራሱ ለወገንና ለሀገር ምን ያህል እንደሚጨነቁና ኃላፊነት እንደሚሠማቸው በቂ የሆነ ማረጋገጫ ነበር፡፡

አፄ ቴዎድሮስ ይህንን ሁሉ አድርገው በመጨረሻ መሸነፋቸውን ሲያውቁ አንድ ያበሻ ንጉሥ በነጭ ወታደር መማረከን ከሞት በላይ ሞት ስለሆነባቸውና በተለይም ለትውልድና ለታሪክ እንዲህ ዓይነት አሣፋሪ ታሪክ ላለማስቀመጥ ሲሉ በራሳቸው ላይ የወሰዱት ቆራጥ ርምጃ ዝንተ ዓለም የትውልድ መኩሪያ ሆነው ይኖራሉ:: ይህነኑ ርምጃ አወሳስዳቸውን ብላንክ አድንቆ ጽፏል:: አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያም <አፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት> በተባለው መጽሐፋቸው ብላንክን ዋቢ ጠቅሰው በገጽ 402 ላይ አስፍረዋል:: በወቅቱም የሚከተለው ስንኝ ተቋጥሮላቸዋል:-

"ገደልን እንዳይሉ ሙተው አገኟቸው
ማረከን እንዳይሉ ሰው የለ በኟቸው
ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው?
በመቅደላ በኩል ጨኸት በረከተ
የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ::
የሸዋን መኳንንት ሲንቁ ሲንቁ
የትግሬን መኳንንት ሲንቁ ሲንቁ
ወንድ ያለ፩ስዎ ገለውም አያውቁ!"

እንግዲህ አጼ ቴዎድሮስ አገርን ለማማከልና ከሁሉም በላይ ይችን አገር የጦር መሣሪያ የኢንዱስትሪ ባለቤት ለማድረግ ላይ ታች ሲባክኑ ከነጮች ጋር በገቡት አታካራ ሕይወታቸውን አሣልፈው እያሉ ይህንን ችግራቸውን በቅጡ ያልተገነዘቡ <ቤት ዘግተው አቃጠሉ፤ በገደል ላይ ጣሉ፤ ወዘተ. . .> በማለት እጅግ በራቀ ዘመን ተራምደው ተራ ዘለፋ ሲዘልፏቸው መስማት ሕሊናን ይሰቀጥጣል::

አሁን ባለንበት ዘመን እንኳን ነፍሳቸውን ይማረውና ታዋቂው የታሪክ ምሁር ደጃዝማች ዶ/ር ዘውዴ ገ/ሥላሴ በሃይማኖት ዓለሙ አቀነባባሪነት አፅማቸውን ጥላሸት ለመቀባት ሲባል ብቻ ላንድ ምሽት በተዘጋጀ የቴሌቪዥን መድረክ ተራ ሽፍታና ባሪያ ፈንጋይ እንደነበሩ እያንበሳቆሉ ሲገልፅዋቸው ሕሊናው ያልቆሰለ ንጹሕ ዜጋ አልነበረም::

ለመሆኑ ምሁሩ አፄ ቴዎድሮስን በዚህ የነሣ ሥርዓት ባሪያ ፈንጋይ ተራ ወንበዴ አድርገው ለምን አቀረቧቸው? ዓላማውስ ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች በወቅቱ መነሣታቸው አልቀረም:: ዓላማውና ተልዕኮው ይህነኑ መከረኛ አማራ ለማሸማቀቅና በሳቸው ታሪክ እንዳይኮራና አርማቸውን ወራሽ ትውልድ እንዳይፈጠር ቅስሙን ሠብሮ አንገቱን ደፍቶ እየቆዘመ የሚገዛ ዜጋ ለማፍራት ነው:: ይህ ዓይነቱ ትንኮሣ ግን ለዛሬ አንድነታችን





ብቻ ሣይሆን ለነገም ጉዟችን ጭምር የከፋትን ሥንቅ የሚያስቋጥር ነው:: ባጭሩ የደጃዝማቹ ንግግር ለማንም፣ ለምንም አይጠቅምም:: እንዲህ ዓይነቱ ተራ ዘለፋም ከምንወዳቸውና ከምናከብራቸው አዛውንት ምሁር አንደበት በመሠንዘሩ የነሠኝነትን ዝቅጠትና መጥፎነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሣይ ነበር::

እንደ እውነቱ ከሆነ በየታሪኩ ተጠቅሶ የምናገኘው ቴዎድሮስ የባሪያ ንግድን ወይንም ሽያጭን አጥብቀው ይቃወሙ እንደነበር ነው:: ደጃዝማች ዘውዴ ግን ገልብጠው ነገሩን::

እነ አቶ መለስስ 7 ሆነው ኋላቀር ጠመንጃ ይዘው አይደል እንዴ ከደደቢት ተነስተው ለመንግሥትነት የበቁት? ምንድን ነው አዲስ ነገር የሆነው? ሕወሓት የሠራው ከሆነ እንደታምር ሊነገር የሌሎች ሲሆን ግን በማፈሪያነት ሊጠቀስ? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ጠይቁ::

ወቃሾቹና አውጋዦቹ እሳቸው ፈፀሙት ከተባለው ድርጊት እጅግ ርቀው ሰብዓዊ ርኅራኄ የሰፈነባቸው ቢሆኑ ኖሮ ሊወቅሷቸውና ሊያወግዟቸው ተገቢ በሆነ ነበር:: ዓላማው ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደሞከርኩት ታሪካቸውን ጥላሸት ለመቀባትና ወራሽ ለማሣጣት በመሆኑ በጣም ያሣዝናል::

አሁን ባለንበት የሥልጣኔ ደረጃ ላይ ደርሰን እንኳን ሻዕቢያ በ1980 ዓ.ም በምዕራብ ኢትዮጵያ አነግን ከፊት በማስቀደም አሰሳ ላይ በሠፋሪ ወገኖቻችን ላይ የፈፀመው አሠቃቂ እልቂት ለሕሊና እጅግ አድርጎ የሚሰቀጥጥ ነው:: ሰብስበ ብሎ ጠርቶ ካንድ አዳራሽ ውስጥ በማጎር በውጭ በመቆለፍ አቃጥሏቸዋል:: የሕወሓት የትግል ጓድ ወይንም አጋር እስከዚህ ድረስ የከፋ አረመኔ ነው:: ሻዕቢያ በሰብዓዊ ሚዛን የማይቀመጥ መሆኑን በአይደር ት/ቤት ህፃናት ላይ ያደረሰውን የቦምብ ድብደባ አይተናል:: ታዲያ ይህን የመሰለ ወንጀል በዚህ ሥልጡን ዘመን እየተፈፀመ አፄ ቴዎድሮስን የመውቀስና የመኮነን ምን የሞራል ብቃት ይኖረናል? ይህም ሆኖ ግን አፄ ቴዎድሮስ ጥፋት አላጠፉም ብለን በጭፍን አንከራከርም:: በርካታ ስህተቶችን መሥራታቸው እውነት ነው:: ይሁን እንጂ አንዲት ኢትዮጵያን ለማማከል ሲሉ ይዘውት ከተነሱት ራእይ ጋር ከዘመኑ ርቀትና ኋላ ቀርነት አንፃር በማመዛዘን ልንገነዘብላቸው ይገባናል:: ከዚህ አልፈን ሥንጥር እየፈለግን ታሪካቸውን ጥላሸት መቀባቱ ግን ለዚህ ትውልድ ፋይዳ

የለውም:: አለው ከተባለም የበቀልን ሥንቅ ማስቋጠር ነው:: ይህ ደግሞ አይጠቅመንም::

<><><>





# አፄ ዮሐንስ 4ኛ



አፄ ዮሐንስ 4ኛ

በዝብዝ ካሣ (በዝብዝ የፈረሣቸው ስም ነው) እንደዚያን ዘመን ወጣቶችና ጎልማሶች ከትውልድ ቀያቸው (ከተምቤን) ወደ ጎንደር በመሄድ ያፄ ቴዎድሮስ ጭፍራ (ወታደር) ሆኑ:: ቴዎድሮስ ለወታደሮቻቸውና ለመኳንንቶቻቸው ማዕረግና ሹመት ሲሰጡ ለካሣም የባላምባራስነት ማዕረግ ሰጥተዋቸው ነበር:: ካሣ ምርጫ ግን በዚህ ማዕረግ ባለመርካታቸው አኩርፈው በመከዳት ወደ ተምቤን ተመለሱ::

ካሣ ምርጫ ተምቤን ውስጥ ትንሽ ከቆዩ በኋላ ራሳቸውን በራሳቸው ደጃዝማች ካሣ ብለው ማዕረግ በመሥጠት ወይንም በመሾም መንቀሳቀስ ጀመሩ:: ይሁን እንጂ የጀኔራል ሮበርት ናፒየር ጦር ወደ ኢትዮጵያ እስከ



አፄ ዮሐንስ 4ኛ

መጣበት ጊዜ ድረስ ባዬ ቴዎድሮስ ላይ ውስጥ ለውስጥ ከማሴር ያለፈ የትግራይን ሕዝብ ግብር እንዳይገብር አሣምፀው ለጦርነት የተሰለፉበት ጊዜ የለም:: ቴዎድሮስም ለካሣ ሽፍትነት ክብደት ሠጥተው ወደ ትግራይ ጦር አላዘመቱባቸውም:: በሌሎች ከባድ ካባድ ችግሮች ተጠምደው ስለነበር የካሣ ሽፍትነት ይህንን ያህል ክብደት እንዳልሰጡት መረጃዎች ይጠቁማሉ::

## "ምን ብጠላው በወንድሜ ላይ ደም አልይበት!"

እንደሚታወቀው አፄ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለዘመናዊ ሥልጣኔ በነበራቸው ጉጉትና ቀናዒነት የተነሣ ከእንግሊዝ ጋር በገቡት የከፋ ውዝግብ ምክንያት እንግሊዝ ቴዎድሮስ በመያዣነት አግተው የያዟቸውን ዜጎቻቸውን ለማስለቀቅ በጄኔራል ናፒየር የሚመራ ጦር በ1860 ዓ.ም መጥቶ ዘይለ ወደብ መሥፈሩ ተረጋገጠ:: ይኸኔ ከትግራይ መኳንንት መሀከል በግንባር ቀደምትነት ከጄነራል ናፒየር ጋር ተላልከው ለመንገድ መሪነት፣ ለሥንቅና ለመረጃ አቅርቦት የተገኙትና ሙሉ ፈቃደኛ የሆኑት ካሣ ምርጫ ነበሩ:: በመሆኑም የጄኔራል ናፒየር ጦር ከዘይላ ወደብ ተነስቶ በሠናፌ፣ ባጋሜ፣ ብዋርላ ደላንታ አድርጎ መቅደላ አምባ እስከሚደርስ ድረስ በመንገድ አንዳችም እንቅፋት አልገጠመውም ነበር:: የዚህ ምክንያቱ ያገር ተወላጅ መንገድ መሪና መረጃ አቀባይ በማግኘቱ ነበር::

አፄ ቴዎድሮስ በዚያች በመጨረሻዋ ፈታኝ ወቅት ሰው ሲፈልጉ ሰው ማጣታቸውና የገዛ ወገናቸው ጠላትን መንገድ እየመራና የሥንቅ አቅርቦት እያቀረበ ማየት ካሣዛኙ ታሪካቸው መሀከል እጅግ የከፋው ነበር ማለት ይቻላል::

ኢትዮጵያ ብዙ ጎልታ ከምትታወቅባቸው በጎ ምግባራት መሀከል አንዱና ዋናው በሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት የከፋ ደም መፋሰስ ቢደርስም እንኳን መኳንንቱ የውጭ ጠላት ሲመጣ በጭራሽ ቀዳዳ አይከፍቱም ነበር:: "ምን ብጠላው በወንድሜ ላይ ደም አልይበት!" በማለት አንድ ሆነው ወራሪውን ጠላት ረግጠው ያስወጡ ነበር:: ይህንን የቆየና የዳበረ ወግ ካሣ ምርጫ የጄኔራል ናፒየርን ጦር ሥንቅ በማቀበልና መንገድ በመምራት ሠበሩት:: አላፊውን ቴዎድሮስን መጥላትና የማያልፈውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ክብር ማዋረድና ያገርን አንጡራ ሀብት ማዘረፍ ታሪክ ይቅር የማይለው ወራዳ ተግባር ነበር ካሣ ምርጫ የፈፀሙት:: ምንም ያህል የሥልጣን ጉጉት ቢኖርባቸውም የጠላትን ጦር መንገድ ሊመሩ ባልተገባቸው ነበር:: ግን ተገባቸውና እየመሩ መቅደላ አምባ አደረሱት::





እንደ እውነቱ ከሆነ ታሪክም እንደሚጠቁመን ካሣ ምርጫ የናፒየርን ጦር በደጋው አገር እየመሩ መቅደላ ባያደርሱት ኖሮ ሊመጣ አስቦ የነበረው ታቹን ባፋር በረሃ ነበር:: በዚያ በኩል ቢመጣ ኖሮ ወታደሮቹ ውሃ ጥሙንና የበረሃውን ንዳድ ችለው ወደ ደጋው አገር የመዝለቃቸው ሁኔታ አጠራጣሪ ነበር:: በረሃውን ይወጡታል ቢባል እንኳን በረሃብና በውሃ ጥም፣ እንዲሁም በበረሃ ንዳድ በጣም የተጎዱ ስለሚሆኑ የጦርነቱ ሁኔታ ሌላ መልክ ሊኖረው በቻለ ነበር::

ለጠላት በር መክፈትንና ስለ መንገድ መምራት ስናወሳ ሌላም ሣንጠቅሰው የማናልፈው ቁስል አለ:: ያ ቁስልም የማይጨው ጦርነት ከመፈንዳቱ ቀደም ብሎ የቀደማዊ ኃይለሥላሴ አማች (የልዕልት ዘነበወርቅ ባል) የምሥራቅ ትግራይ ገዥ የነበረው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ አገሩንና ንጉሠ ነገሥቱን በዚያች ፈታኝ ቀውጢ ወቅት ከድቶ ኤርትራ በመግባት ልክ ካሣ ምርጫ የናፒየርን ጦር እየመሩ መቅደላ እንዳደረሱት ሁሉ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣም ኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ በምትፈልግበት ወቅት የኢጣሊያንን ጦር እየመራ መጣ::

ጄኔራል ናፒየር አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን በራሳቸው አጥፍተው የጦርነቱ ፍፃሜ ከሆነ በኋላ የዘረፈውን ዘርፎ የሚያወድመውን አውድሞ ለጉዞ ከመንቀሣቀሱ በፊት ለካሣ ምርጫ ለዋሉለት ውለታና ላበረከቱት ሁለንተናዊ አገልግሎት 12 ዘመናዊ መድፎች፣ 900 ሲናድር ጠመንጃዎች፣ ቁጥራቸው በትክክል ያልታወቀ ሽጉጦችና ከውትድርና ሙያ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ በርካታ ቁሳቁሶችን (እንደ ባይሮክለር መነፅር የመሳሰሉትን) በገፍ ካሥታጠቃቸው በኋላ እነዚህን ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን የሚያስተምሩና ጦራቸውንም ዘመናዊ ውትድርናን የሚያሠለጥኑላቸው ሁለት የእንግሊዝ ወታደሮችን (ኪርክሃምና ሉዊ የተባሉ) ካሥቀረላቸው በኋላ በመጨረሻ እንዳመጣጡ ወደ ሀገሩ ሲመለስም በክብር አጅበው አሸኛኘት አድርገውለታል::

ጄኔራል ናፒየር ጓዙን ጠቅልሎ ካገር እንደወጣ በዚያን ወቅት በሠራዊት ብዛትም ሆነ ባደረጃጀት ከነበሩት መኳንንት መሀከል የላስታው ዋግ ሹም ጎበዜ የተሻሉ ስለነበሩ ጊዜ ሳይሰጡ ተሻምተው ወዲያውኑ <አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ንጉሠ ነገሥት ዘ-ኢትዮጵያ> ተብለው ነገሡ::

ካሣ ምርጫ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ጄኔራል ናፒየር አስታጥቋቸው ቢሄድም የዋግ ሹም ጎበዜን ያህል ሰው ስላልነበራቸው ያፄ ተክለ ጊዮርጊስን

ንጉሠ ነገሥትነት ተቀብለው ራሳቸውን ሲያደራጁ ቆይተው በመጨረሻ እወጣዋለሁ ባሉበት ወቅት <አልገብርም> በማለት ማመፃቸውን በይፋ አስታወቁ:: በዚህ ወቅት አፄ ተክለ ጊዮርጊስ <አትችለኝም:: ሠራዊቴ እንደዚህ ጤፍ ብዙ ነው> ብለው አንድ አቅማዳ ጤፍ ባህያ አስጭነው ላኩባቸው:: በዝብዝ ካሣ በበኩላቸው <ሠራዊትዎ እንደ ላኩት ጤፍ ብዙ ቢሆንም በታጠቁት ዘመናዊ የጦር መሣሪያ እቆላለዎታለሁ!> በማለት ጤፉን ቆልተው መልሰው ላኩላቸው::

በዚህ ሁኔታ የዛቻና የማስፈራራት መልዕክት ከተለዋወጡ በኋላ ሁለቱም ሊለዝቡ ባለመቻላቸው አፄ ተክለጊዮርጊስ ከላስታ ተነስተው ወደ ትግራይ በመዝመት ዓድዋ አሰም ወንዝ አጠገብ ፍልሚያ ገጠሙ:: እውነትም ካሣ ጤፉን ቆልተው እንደላኩት ሁሉ ያፄ ተክለጊዮርጊስን ሠራዊት ናፒየር ባሥታጠቃቸው ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ቆልተው ንጉሠ ነገሥቱም በፍልሚያው ላይ ተገደሉ:: በዚሁ የጦርነቱ ፍፃሜ ሆነ:: በነገራችን ላይ ያፄ ተክለ ጊዮርጊስ ሚስት የካሣ ምርጫ እህት ስለነበሩ አልቃሽ:-

*"ጎዳዩ ወንድምሽ፣*
*የሞተው ባልሽ*
*ሐዘንሽ ቅጥ አጣ እኔ ምን ልበልሽ!"* ብሏቸዋል

## ካሣ ምርጫ አፄ ከሆኑ በኋላ የወሰዷቸው ርምጃዎች

ካሣ ምርጫ አፄ ተክለ ጊዮርጊስን ከገደሉ በኋላ <አፄ ዮሐንስ 4ኛ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ!> ተብለው ነገሡ:: በዚህ ወቅት ደግሞ የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ <አፄ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ> ተብለው ነገሡ:: ሁለት አፄዎች ባንድ ጊዜ ላንዲት አገር የሚቻልም፣ የሚታሰብም፣ የሚሆንም አይደለምና አንዱ ባጥቂነት መውጣት ስለነበረበት ለጦርነት ተሰላለፉ::

አፄ ዮሐንስ <ምታ ነጋሪት፣ ከተት ሠራዊት> ብለው ምኒልክን ለመውጋት ከትግራይ ተንቀሳቅሰው ወሎ ምድር ገቡ:: ይሁን እንጂ የዚያን ዘመን የሃይማኖት አባቶች እንደዛሬዎቹ ጭልጥ ያሉ ጥቅም አሳዳጆችና በጎሣ የተመረዙ አልነበሩምና ለሃይማኖታቸው፣ ለእምነታቸው የበረቱ፣ የተከበሩ፣ የተፈሩና አንቱ የተባሉ ስለነበሩ ተደማጭነት ነበራቸው:: በመሆኑም ሁለቱ





ወንድማማቾች ሥልጣን ለኔ ይገባኛል ምክንያት ደም በከንቱ መፋሰስ እንደ ማይገባቸው ግራ ቀኙን በያሉበት ከወቀሱና ከተቆጡ በኋላ ቀጠሮ ተይዞ ምኒልክ ወደ ወሎ እንዲጓዙ ተደርጎ ወሎ ውስጥ <ሊጩ ወይንም ሊች> ከተባለች ቦታ ሁለቱ አፄዎች ለዚሁ ተግባር ተብሎ ከተዘጋጀ ድንኳን ውስጥ ከታላላቅ የሃይማኖት አባቶች ጋር ገብተው ከብዙ ቆይታ በኋላ እንደገና ከድንኳኗ በመውጣት የርቁ ሁኔታ በምን ዓይነት መንገድ ይቋጭ ይሆን እያለ በጉጉት ለሚጠብቃቸው ሕዝብ ባዋጅ መልክ የሚከተለውን አስነገሩ:-

"አፄ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ" ሲባሉ ምኒልክ ደግሞ አንድ ደረጃ ዝቅ ብለው "ንጉሠ ሸዋ" መባላቸውን በተነገረና በተገለፀ ጊዜ ሕዝቡ ታላቅ ደስታና እልልታ አቅልጦ እንደነበር የእድሜ ባለጸጎች ይተርካሉ:: ከዚህ ውጭ ሁለቱ መሪዎች በሌሎች ጉዳዮች ላይ ምን እንደተነጋገሩ የሚታወቅ ነገር የለም::

እንግዲህ ከፍ ብሎ እንደ ተመለከትነው እሰበስ በሥልጣን ንጥቂያ ምክንያት የሚያፋጥጥ ዘመን ሲከሠት የሃይማኖት አባቶች የማስታረቅ፣ የማቻቻልና የመምከር፣ የመገሠፅ ተግባር ያከናውኑ ነበር:: የሞራል ብቃትም ነበራቸው:: "ሰዎች የሆኑ ሁሉ ሌሎችን እንደራሳቸው እንዲወዱና እንዲያከብሩ" የሐዋርያነት ተግባር ይፈፅሙ ነበር:: በዚህ ዘመን ግን ይህ መልካም ሃይማኖታዊ ሥነ-ምግባር ተገልብጦ "ሰዎች የሆናችሁ ሁሉ እንደ አውሬ እስበሳችሁ ተናከሱ!" በሚል ቃል የተተካ መስሏል:: ዛሬ የሃይማኖት አባቶች እንኳንስ የተጣሉን ሊያስታርቁ ይቅርና እነሱ ራሳቸው ጠብ አቀጣጣይ ቤንዚን ሆነዋል:: ሣይሞቱ የሞቱትና ዛሬ ሲሞቱ የሚያሠሩትን ሐውልት በቁማቸው ያስቆሙ እለት ነበር::

የዘመኑ ካህናትና ዳቆናት ኢሕአዴግ በሚያዘጋጃቸው የድጋፍ ሰልፎች ላይ በመገኘት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ከበሮ እየደለቁ፣ ከፊት ከፊት ሰልፉን የሚመሩ ናቸው:: እንደነዚህ ያሉትን የሃይማኖት ሰዎች ጆን ሐዘወይ ስፔንሰር በመታዘብ እንዲህ ይሏቸዋል:-

*". . .የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በርካታ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት የሚገኙባት ምትክ የማይገኝላቸውን ድርሳናትና ንዋየ ቅዱሳት ከመጠበቅ በስተቀር ማኅበራዊ ችግሮችን አልተገነዘቡም:: ማይማንና ሰስታም ካህናት ጊዜው እንዳልተለወጠ ሁሉ የተካበተ ሀብቷን ሙጭጭ ብለው ይዘዋል:: ቤተክርስቲያኒቱ ከኢጣሊያን ፋሽሽቶች አገዛዝ ጋር እንዳደረገችው ሁሉ*

*ከኮሚኒስት ደርግ ጋርም ልክክ አለች!!"* በማለት ተቸተዋቸዋል፡፡ *(ጥርስ የገባች አገር ገጽ 175)*

ስፔንሰር እንዳሉት እነዚህ የቤተክህነት አባቶች ከፋሽሽት ኢጣሊያና ከኮሙኒስት ደርግ ጋር ልክክ እንዳሉት ሁሉ ዛሬ ደግሞ በኢሕአዴግ <አብዮታዊ ዴሞክራሲ> ፀበል ተጠምቀው የካድሬ ተግባር ሲፈፀሙ ማየት ለእምነቱ ተከታዮች አንገት የሚያስደፋ ሆኗል፡፡ የሆነ ሆኖ ይህን በዚህ እናቁምና ወደ አፄ ዮሐንስና ወደ ንጉሥ ምኒልክ እንመለስ፤

አፄ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ ሊቸ ላይ ከታረቁ በኋላ የበለጠ እንዲተማመኑ በማሰብና በደም በሥጋ ለመተሣሠር ሲሉ የ12 ዓመቱን አርአያ ዮሐንስንና 7 ዓመት ከ6 ወራት የሆናትን ህፃን ዘውዲቱ ምኒልክን አጋብተው ሞት እስከለያያቸው ድረስ በጋብቻ በመተሣሰር መተማመኝን ለመፍጠር ጥረት አድርገዋል፡፡ የዚህ ዘመን ባለሥልጣትና ወያኔዎች ግን እንኳንስ በጋብቻ ሊያስተሣሥሩ ይቅርና በጉርብትና እየተጠራሩ ቡና አብሮ መጠጣትም እየቀረ ነው፡፡ በመሰረቱ የሕወሓት ሰዎች ቆም ብለው ማሰብና መፀፀት እስካልቻሉ ድረስ ውጤቱ አሣዛኝ ነው የሚሆነው፡፡ አንዱ የሌላውን ቁስል በስንጥር እንጨት የሚመነቁር ከሆነ ያንድነት ርሿችን ጭራሹኑ መሟጠጡ አይቀሬ ነው፡፡ በዚህ ውጤት የሚደሰቱ ካሉ ደግሞ ጊዜው ላይርቅ ይችላል፡፡

## ስህተት አንድ
## በወሎ ሙስሊሞች ላይ የወሰዱት ርምጃ

አፄ ቴዎድሮስ አገራቸውን ወደ አንድ ማዕከላዊ መንግሥት ለማጠቃለል ሲፈልጉ የጦር መሣሪያ እንደሚያስፈልጋቸው አምነዋል፡፡ በመሆኑም የእደ ጥበብ ሙያተኞችን ማሰባሰብና ተገቢውን ክብር መስጠት ነበረባቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ቴዎድሮስ ለሃይማኖት ከማመን ባለፈ የሚጨነቁ ንጉሥ አልነበሩም፡፡ ባንፃሩ አጼ ዮሐንስ 4ኛ ደግሞ ለእደ ጥበብ ሙያተኞችና ለዘርፉ ግድ አልነበራቸውም፡፡ ለኦርቶዶክስ ሃይማኖት ግን ቀናዒ ከመሆናቸው የተነሳ ሃይማኖትን መርሃቸው አደረጉ፡፡ በመሆኑም ለኢትዮጵያ አንድነት አንዱና ዋናው እንቅፋት የሃይማኖት ልዩነት ነው በሚል ወደ ጥፋት የሚያመራና የተሳሳተ መርህ ይዘው ተነሱ፡፡ ይህኑኑ ተግባራዊ ለማድረግ በዘመናቸው ከወሰዷቸው ስልት አልባ የተሳሳቱ ርምጃዎች መሀከል አንዱ በወሎ ሙስሊሞች ላይ የወሰዱት ርምጃ ነበር፡፡





አፄ ዮሐንስ ወሎ (ቦሩ ሜዳ ላይ) በ1870 ዓ.ም ንጉሥ ምኒልክና ራስ አዳል (ኋላ ንጉሥ ተክለኃይማኖት) በተገኙበት በተካሄደ ሃይማኖታዊ ጉባዔ ላይ የወሎ ሙስሊሞች ክርስቲያን እንዲሆኑ አዋጅ አወጁ፡፡ ግንባር ቀደም አርአያ ለመሆንም አፄ ዮሐንስ ይማም መሐመድ ዓሊን ክርስትና አንስተው የራስነት ማዕረግ በመሥጠት በክርስትና ስማቸው <ራስ ሚካኤል> ተባሉ፡፡ በኋላ ንጉሥ ሚካኤል የተባሉት የልጅ ኢያሱ አባት ናቸው፡፡ ንጉሥ ምኒልክ ደግሞ የወ/ሮ መስተዋትን ልጅ ይማም ዓመዴ ዓሊን በፈረስ ስማቸው <ይማም አባ ዋጠውን> ክርስትና አንስተው በክርስትና ስማቸው <ደጃዝማች ኃይለማርያም> ተባሉ፡፡

ባዋጁ ውስጥ <ትንባሆ ሲያጨሱ፣ ሱረት ሲምጉ፣ የተገኙ አፍንጫቸው እንዲፎነን (እንዲቆረጥ)፣ የታች ከንፈራቸውና ምላሳቸው እንዲቆረጥ የሚል> በመካተቱ ይኸው ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የፈቀዱ በፈቃዳቸው ወደ አቅራቢያቸው ቤተክርስቲያን እየሄዱ ክርስትና ተነሱ፤ ያልፈቀዱ ደግሞ በጭቃ ሹምና በፈረሰኛ እየተገደዱ ተነሱ፡፡ ክርስቲያን መሆን ሕሊናቸው ያልተቀበለላቸው ደግሞ አገር ጥለው ወደ ሱዳን ተሰደዱ፡፡ የኋላ ኋላ ለድርቡሾች መንገድ መሪ ሆነው በመምጣት የጦርነቱ ቀጥታ ተካፋይ በመሆን በቀላቸውን ሲወጡ እናስተውላለን፡፡ ይህም ይዘገያል እንጂ ሰው የሥራውን ወይንም የጁን እንደማያጣ በቂ የሆነ ማረጋገጫ ነበር፡፡

ክርስትና ተነሱ ተብለው በተገደዱ ጊዜ አንድ ሙስሊም የሚከተለውን ስንኝ ቋጥሯል፡-

*"ታናሽ ታላቅ በላን አርካ አደባባይ*
*አለልብ ሥጋ ይጣፍጣል ወይ?"* ሲል ምሬቱን ገልፆዋል፡፡

ወደ ሱዳን መሰደድ ያልሆነላቸው ሙስሊሞች ደግሞ ወደ ሸዋ እየመጡ ለምኒልክ የጌታ በማደር የምኒልክን ጎራ አጠናከሩት፡፡ በተለይም የወረዒሉ ሙስሊሞች ከመንዝ ጋር ኩታ ገጠሞች በመሆናቸው እምነታቸውን እንደያዙ ወደ መንዝ በመሻገር የምኒልክን ስምና ዝና ከርቀት አገነኑት፡፡ ባንፃሩ አጼ ዮሐንስ ቋሚ የሆነውን "አገር የጋራ ነው ሃይማኖት የግል ነው!" የሚለውን መርህ በመፃረራቸው የሕዝብን ፍቅርና አክብሮት በማጣት ኃይላቸው እየሳሳ ሲመጣ እናስተውላለን፡፡

# ስህተት ሁለት
# በቤጌምድር ሕዝብ ላይ የፈፀሙት ነውረኛ ተግባር

ያጼ ዮሐንስ ሁለተኛው ስህተት በቤጌምድር ሕዝብ ዘንድ ዛሬም ድረስ የሚያስወቅሳቸው በፍርደ ገምድልነታቸው ነበር። የትግራይን ሠራዊት አግተልትለው በማምጣት ከሰኔ እስከ ህዳር ወር መጨረሻ ድረስ ለ6 ወራት ደብረታቦር በመቀመጥ ሠራዊታቸውን በድፍን ቤጌምድር በተሠሪነት በማሠማራት ተዘፍዝፎ ሲያምስ ይከርማል። በልማዱ አንድ ሕዝቧ ሠራዊት በተሠሪነት በየቤቱ እንዲሸከም የሚበየንበት ባንድ ደጃዝማች ወይንም ፊታውራሪ አማካኝነት ወይንም በራሱ አነሳሽነት አልገብርም ብሎ ያመፀ እንደሆነ ነበር። ይህም ቢሆን መሸነፉን አውቆ ምሕረት ከጠየቀና ከገበረ የተመራበት ተሠሪ ሠራዊት ይነሳለታል እንጂ ለረጅም ጊዜ እንዲሸከም አይበየንበትም። አፄ ዮሐንስ ግን በተፃራሪው በሰላም ቀጠና ወይንም በሰላማዊ ሕዝብ ላይ የችጋር ወቅቶች እየተጠበቁ ለረጅም ወራት ሠራዊታቸውን በያመቱ የቤጌምድር ሕዝብ እንዲቀልብ ማድረጋቸው ስህተት ብቻ ሳይሆን ጭካኔም ነበር።

በዚያን ጊዜ የቤጌምድር ሕዝብ ባፄ ዮሐንስ ሠራዊት ከመዋረዱ የተነሣ ዘመነ መሣፍንትን እንደገና የናፈቀበት ጊዜ እንደነበርም በእድሜ አንጋፋዎች ይተርካሉ። ልክ ዛሬ አንዳንዶች አፋኙ የደርግ ሥርዓት በስንት ጣዕሙ እንደሙሉት ዓይነት ማለት ነው።

መቸም ቢሆን አንበጣና ሠራዊት የሠፈረበት ሕዝብ በሁለንተናዊ መልኩ መቅኖ የለውም። የቤጌምድር ሕዝብም በዚያን ጊዜ መቅኖ አጣ። ሥራ ውሎ ሲመጣ ሚስቱን ተገዳ ከወታደር ጋር ተኝታ ያገኛታል። ይህ ለወንድ ልጅ የከፋ ውርደት ነበር። አንዳንዶች ሥራ ትተው ሚስቶቻቸውን እየጠበቁ ከቤት መዋል ጀመሩ። ይህም ለገበሬው የከፋ ስቃይ ነበር። "ባገርና በሚስት የለም ዋዛ!" ያሉ እየገደሉ ዱር ቤቴ አሉ። ይህ ደግሞ የከፋ ጥፋትን በሕዝብ ላይ አስከተለ። አንድ ወይንም ሁለት ግለሰቦች በሚፈፅሙት ጥፋት የንጉሥ ነገሥቱ ሠራዊት ያችን መንደር ያወድማታል። ወንድ ልጅ የተባለ ሁሉ የፊጥኝ እየታሠረ አርባ ጅራፍ ይገረፋል። ሕዝቡ ተዋረደ፤ ተናቀ። ከያቅጣጫው የቁጭት ድምፆች መሠማት ጀመሩ። በዚህ ምክንያትም እስቴ ወረዳ አቶ ካሣ ገብረየስ በተባሉ ቀንደኛ አዛውንት መሪነት ሰባት ጎልማሶች በሕዝብ ተወክለው ለንጉሠ ነገሥቱ አቤቱታ ለማሰማት ወደ ደብረታቦር ሄዱ።





እነ አቶ ካሣ ገብረየስ ካፄ ዮሐንስ አደባባይ እንደ ደረሱ "አቤት አቤት!" ሲሉ አቤቱታቸውን አቀረቡ። በዚህ ጊዜ ሊጋባዎች (የንጉሡ አጋፋሪዎች) ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት አቀረቧቸው። አፄ ዮሐንስም:- "ምን ሆናችሁ ነው?" ሲሉ ጠየቋቸው።

"ጃንሆይ፤ ሠራዊትዎን ተሠሪነቱን ተቀብለን፣ አክብረን፣ ጥሩ እያበላንና ጥሩ እያጠጣን፣ ምንም ሣናጓድል ሚስቶቻችን ተነጠቅን! ይህንን ይፍረዱን!" ሲሉ አመለከቱ።

ከዚህ በኋላ አደባባይ የተሰበሰበው መኳንንት ይተችበት ጀመር። ግማሾች "እነዚህ ባላገሮች የሠራዊቱን ስም አጉድፈዋልና መቀጣት አለባቸው" ሲሉ ሌሎች ደግሞ "የለም ሠራዊት በሚሠፍርባቸው አካባቢዎች ሁሉ እንዲህ ዓይነት ነገሮች ይከሰታሉ። ይህ አዲስ ነገር አይደለም። ድሮም ቢሆን በግድ እንጂ ባላገርና ወታደር አይስማሙም። ስለዚህ እነዚህ ባላገሮች ቢያጠፉም ሕዝብ የላካቸው ስለሆኑ በወቀሣ ሲለቀቁ ይታየናል" በማለት ሰፊ ክርክር ከተካሄደ በኋላ በመጨረሻ የንጉሠ ነገሥቱ ውሳኔ በጉጉት ይጠበቅ ነበርና የሚከተለውን ወሰኑ:-

"አካፍሉት እንጂ፤ ምፅሪ ከትግራይ ጭኖ አልመጣ!" ሲሉ አሣዛኝና ነውረኛ ውሳኔ በመወሰን የነ አቶ ካሣን ልብ አደሙት።

ከዚህ በኋላ በድፍን ቤጌምድር ወንድ ልጅ የተባለ ሁሉ ካፄ ዮሐንስ ሠራዊት እየሸሸ የቻለ ሚስቱን እየያዘ ያልቻለ ሚስቱን እየጣለ ተሰደደ። መኳንንት ቀመሶች ደግሞ ወደ ሸዋ እየሄዱ የምኒልክን የወደ ፊት ተስፋ አለመለሙት። ለምሳሌ ከታላላቅ መኳንንት መሀከል ራስ ወሌ ብጡል( የእቴጌ ጣይቱ ብጡል ወንድም) እስከነልጃቸው (ደጃዝማች ጉግሣ ወሌ) በኋላ ራስ ተብለው የቤጌምድር ገዥ የነበሩት ተጠቃሾች ናቸው። ይህ ሁሉ የሆነው እንግዲህ ጣይቱና ምኒልክ ከመጋባታቸው በፊት ገና ከማለዳው ነበር። ምኒልክና ጣይቱ ከተጋቡ በኋላ ደግሞ የቤጌምድርና የየጁ መኳንንት በሙሉ ማለት ይቻላል አገራቸውንና ግዛታቸውን ላፄ ዮሐንስ ሠራዊት እየለቀቁ ወደ ሸዋ በመምጣት ምኒልክን ምኒልክ አሰኟቸው። ለምሳሌ አከስታችን ብለው ከመጡት መሀከል ወንድማማቾቹ ደጃዝማች አድማሱ ብሩና ደጃዝማች ዓያሌው ብሩ ተጠቃሾች ናቸው። ሌጣቸውን መጥተው ባንድ ጊዜ ለሁለቱም የደጃዝማችነት ማዕረግ ያጎናፀፏቸው ምኒልክ ነበሩ።

ከነዚህ ቀጥሎ ወደ ሸዋ የመጡት ከጉና እስከ በሽሎ ገዥ የነበሩት ያዋርላው ተወላጅ ደጃዝማች ይማም ተፈሪ ነበሩ። ካፄ ዮሐንስ ጋር

በመቀያየማቸው ምክንያት ግዛታቸውን ለቀው ፲፱ መኳንንትንና 25 ጭፍሮቻቸውን ይዘው ነበር ሸዋ የገቡት:: ካሥራ አንዱ መኳንንት መሀከል አንዱ የኔ ቅድመ አያት ፊታውራሪ ወርቅነህ ይመር ነበሩ:: ያነዬ ግራዝማች ነበር ማዕረጋቸው:: ምኒልክ ነበሩ የፊታውራሪነት ማዕረግ ያለበሷቸው::

እንግዲህ ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደ ሞከርኩት ባፄ ዮሐንስ ፍርደ ገምድልነትና ያመራር ስህተት የተነሳ እየተማረረና እያኮረፈ ወደ ሸዋ የሚመጣውን መኳንንት ምኒልክ በከብር እየተቀበሉ ማዕረግ ለሚፈልጉት ማዕረግ ፣ ገንዘብ ለሚሹት ገንዘብ፣ ማደሪያ ለሚሉቱ ማደሪያ እየሰጡ በማስደሰታቸው እንደ እናት ተቆጥረው <እምዬ> የሚል የቁልምጫ ስም የወጣላቸው ያነዬ እንደ ነበር ይነገራል::

ደጃዝማች ይማም ተፈሪና ቅድመ አያቴ ፊታውራሪ ወርቅነህ ይመር የራስ ወልደ ጊዮርጊስ (በኋላ ንጉሥ ተብለው ከራስ ጉግሣ ወሌ በፊት የቤጌምድር ገዥ የነበሩት) ባልደረቦች በመሆን ከግቤ ማዶ የነበሩትን አገሮች ማለትም ከፋን፣ ጅማን፣ ሊሙን. . . ወደ ማዕከላዊ መንግሥት እንዲጠቃለሉ አድርገዋል:: የቅድመ አያቴ መቀመጫም ባቦ ኮሣ ማርያም ከተባለች አምባ ነበር:: ኮሣ ማርያምን የተከሏት እሳቸው ነበሩ:: ወግ ማዕረግ አይተው፣ ኑረው፣ ሙተው የተቀበሩትም ካስተከሏት ቤተ ክርስቲያን ኮሣ ማርያም ነበር::

አያቴ (ያባቴ እናት) ወ/ሮ አለሙሽ ወርቅነህ ተወልደው አፋቸውን የፈቱት በኦሮምኛ ቋንቋ ሲሆን ካባታቸው እልፊት በኋላ ወደ አባታቸው አገር ጎንደር (ጋይንት) የሄዱት የ፲ ዓመት ልጅ ሳሉ ነበር:: እኔ እንግዲህ እንደዚህ ነኝ:: እናንተስ? ስንቶቻችሁ ትሆኑ እንደ አሜባ አንድ ሴልና ባንድ የጎሣ ደም የነጠራችሁት? ጠይቁ::

እንግዲህ አፄ ዮሐንስ ያነዬ በወሎና በቤጌምድር ሕዝብ ላይ በፈፀሙት ስህተት መኗሪያ ሲያሳጡት እሳቸውን እየሸሸ ለምኒልክ የጌታ በማደሩ እሳቸው ባንድ ጎሳ (በትግራይ መኳንንትና ሠራዊት) ብቻ ተከበው ርቃናቸውን ቀሩ:: ወደፊት እንደምናየው በጎጃም ሕዝብ ላይ የወሰዱት ያልተገባ ርምጃም ርቃናቸውን ቀርተው አወዳደቃቸው ሲከፋ እናስተውላለን::





## ስህተት ሦስት
## ከሪር አድሚራል ሔዊት ጋር ያደረጉት ስምምነት

አፄ ዮሐንስ በስህተት ሦስት የፈፀሙት ስህተት ከሪር አድሚራል ሔዊት ጋር ያደረጉት ስምምነት ሲሆን ያልተገባና በየዋህነት የተከናወነ ነበር:: በወቅቱ ለጎንደር አድባራትና ገዳማት መቃጠልና መዘረፍ ምክንያት ሲሆን ውሎ አድሮ ደግሞ ለሰሜን ኢትዮጵያ ቀጣይነት ላለው ችግር የመሠረት ድንጋይን ያስቀመጠ ውል ነበር:: የሰዐጢ፣ የዶጋሊ፣ በመጨረሻም ሕይወታቸውን ያጡበት የመተማ ጦርነት፣ እንዲሁም ከዚያ ወዲህ ያድዋና የማይጨው ጦርነቶችና የኤርትራ መገንጠልን ጨምሮ እስከ ሕወሓት መፈጠር ድረስ ያሉት ችግሮች ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የስምምነቱ ውጤቶች መሆናቸውን ልብ ልንል ይገባናል:: ዛሬ እየተጎነጨነው ያለነው መራራ ጽዋ አፄ ዮሐንስ ከሪር አድሚራል ሔዊት ጋር በፈፀሙት የቅርቃር ስምምነት ምክንያት መሆኑን ታሪክ እየገለበጡ የሚያነቡልን አፄ ዮሐንስ የተጓዙበትን መንገድና የፈፀሟቸውን ስህተቶች መለስ ብለው በጥንቃቄ ሊያጤኗቸው ግድ ይላቸዋል:: በዚህ አጋጣሚም ያነዬ አፄ ዮሐንስ የቅኝ ገዥ ወታደሮችን ከቅኝ ተገዥዎች ጋር ተፋልመውና ከንቱ የሆነ የሕይወት ዋጋ ከፍለው ነፃ እንዳወጧቸው ሁሉ የሕወሓት ባለሥልጣናትም በዚህ ዘመን ሞቃዲሾ ድረስ ሠራዊት ልከው ያሜሪካኖችን ደም ሲበቀሉ ለትውልድ ደግሞ የደም እዳ ማስቀመጣቸውንም አብረው ሊያዩትና ሊጤኑት ይገባቸዋል::

በመሠረቱ የንጉሠ ነገሥቱ የዋህነት የጧት ወዳጅ የማታ ጠላት እንደሚሆን አለመገንዘባቸው ነበር:: በሳቸው እምነት እንግሊዞች ያፄ ቴዎድሮስ ጠላት ስለሆኑ ለሳቸው የዘለቄታ ወዳጅ የሚሆኗቸው መስሏቸው ከሚገባው በላይ እንደተለማመጧቸው ማረጋገጫው ከስምምነቱ በኋላ ለንግሥት ቪክቶሪያ የፃፉት ደብዳቤ በቂ ማሣያ ነው:: እንዲህ ይነበባል:-

*“. . .ጥንቱንም በእግዚአብሄር ፈቃድ ለመንግሥት የበቃሁት እሰዎ በሠጡኝ ነፍጥ (ጠመንጃ) ባሩድ ነው (ጥይት) ነው:: አሁን ደግሞ ይልቁንም ፈጽሞ ደስ አሰኙኝ:: ከዚህ በፊትም እናት ለልጇ እንደ ምትጨነቅ ለኔ መንግሥት ሲጨነቁ ኖረዋል!” (ተክለ ፃድቅ መኩሪያ አፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት ገጽ 270)*

ወደ ስምምነቱ በቀጥታ ከመግባታችን በፊት ለግንዛቤ ያህል በትንሹም ቢሆን ወደ ኋላ መለስ ብለን ለወታደሮቹ መከበብ ምክንያት የሆነውን ማየቱ ጠቃሚ ነው::

በ1820 ዓ.ም በግብፅ የቱርክ እንደራሴ የነበረው አልባኒያዊው መሐመድ ዓሊ (ቅጥረኛ ነው) የላይኛውን ያባይ ሸለቆ ተፋሰስ ተከትለው ያሉትን አገሮች ጥንት ኑቢያ፣ ሜሮዌና ስናር ይባሉ የነበሩትን በጦር ኃይል ድል አድርጎ ባንድ ላይ አጠቃሎ <ሱዳን> የሚል አዲስ ስም በመስጠት በግብፅ ቅኝ ግዛት ሥር እንዲወድቁ አደረጋቸው:: <ሱዳን> ማለትም በዐረበኛ <ጥቁር ዐረብ> እንደማለት ነው:: እንግዲህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሒዊት ስምምነት እስከ ተፈረመበት ድረስ ሱዳናውያን በግብፅ ቁጥጥር ሥር ነበሩ ማለት ነው::

ኋላ ላይ ደግሞ ቅኝ ግዛት በተፋፋመበት ወቅት ግብፅ ራሷ በእንግሊዝ ቁጥጥር ሥር ስትወድቅ እንግሊዝ ቀደም ሲል ምፅዋን ጨምሮ በግብፅ ይዞታዎች ሥር የነበሩትን አገሮች በሙሉ በቁጥጥሯ ሥር ማድረግ ፈለገች:: በመሆኑም ቀደም ሲል ሱዳን ውስጥ ሠፍረው ከነበሩት የግብፅ ወታደሮች በተጨማሪ የራሷን ወታደሮች በመላክ ኃይሏን በማጠናከር የቅኝ ግዛት መሠረቷን ጣለች:: ይህ የቅብብሎሽ አገዛዝ ደግሞ ሱዳናውያንን አንገሻገሻቸው:: እናም ለነፃነታቸው ሲሉ አመፁ::

በመሪያቸው ስም (በመሐዲ) መሐዲስቶች ወይንም ድርቡሾች በመባል የሚታወቁት አማፂያን ከፍተኛ የሥንቅና የጦር መሣሪያ ከምችት ያሉባቸውን የጦር ካምቦች ከሰሳንና ገላባትን በመከበብ አስጨናቁ:: ያማፂያኑ ከበባ እጅግ የተጠናከረ ስለነበር ሠብሮ ለመውጣትም ሆነ ከጀርባ ገብቶ ለማስለቀቅ የሚቻል አልነበረም:: ስለዚህ የነበረው አማራጭ እንግሊዝ የሕይወትም ሆነ የቁስ ኪሣራ ሣይገጥማት በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ኪሣራ የተከበቡትን ወታደሮቿን ማስለቀቅ እንደምትችል አረጋገጠች:: ለዚህ ደግሞ አፄ ዮሐንስ እንደማያንገራግሩ ርግጠኞች ነበሩ:: የሆነውም ይኸው ነበር::

በዚህ መሠረት በግብፅ በኩል ሜሶን ቤይ የተባለ፣ በእንግሊዝ በኩል ደግሞ የተደራዳሪዎች የቡድን መሪ የእግሊዝ የባሕር ኃይል ም/አዛዥ ሪር አድሚራል ሒዊት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ግንቦት 18 ቀን 1876 ዓ.ም የመጀመሪያውን የቃል ስምምነት ከፈፀሙ በኋላ በታሪክ "የሒዊት ስምምነት" ተብሎ የሚታወቀውን የሠነድ ፊርማ ሰኔ 3 ቀን 1876 ዓ.ም





ተፈራረሙ:: ይህ ስምምነት አድዋ ላይ በመከናወኑ <"ያድዋ ስምምነት> በመባልም ይታወቃል::

ከዚህ ላይ ታዲያ መነሣት ያለበት መሠረታዊ ጥያቄ ኢትዮጵያ የሕይወት መሥዋእትነት ከፍላ፣ ከጎረቤት አገር ጋርም የዘለዓለም ቁርሾ ገብታ በመልሱ ምን አገኘች? ንጉሠ ነገሥቱስ ምን ምን ጥያቄዎችን አቅርበው ነበር? የሚሉትን ስናነሳ የምናገኘው መልስ የሚያስገርም ነው:: ሌላውን ዝርዝር ሁሉ ትተን ንጉሠ ነገሥቱ እንዲፈፅሙላቸው ካቀረቧቸው መሀከል ሁለቱን ብቻ ጠቅሰን እንመልከታቸው:-

*1. "የከሰላ ግዛት ወደ ኢትዮጵያ እንዲጠቃለል"*

*2. "ከምፅዋ ወደብ ከሚሰበሰበው ቀረጥ ከግብፅ ጋር እኩል የመካፈል መብት ይኑረኝ"* የሚል ነበር::

የንጉሠ ነገሥቱን ተለማማጭነት ልብ እንበል:: ዋናውን የወደብ የይገባኛል የሙብት ጥያቄ ጭራሹኑ ትተው ከወደብ የሚገኘውን ቀረጥ ከግብፅ ጋር እኩል ልካፈል ብለው የመጠየቃቸው ጉዳይ ያናድዳል:: ሌላው ቀርቶ ግብፅ እንደ የመን እንኳን ቀይ ባሕርን ማዶና ማዶ አታዋስነንም:: በተስፋፊነት የኛ አቅም በወነሰበት ወቅት ቱርክን ተከታ የተቀመጠች ናት:: አፄ ዮሐንስ ይህን እያወቁ በዚያች አስጨናቂ አጋጣሚ ተጠቅመው <ግብፅ ወደቤን ልትለቅልኝ ይገባታል> ብለው መሟገት ሲገባቸው የእለት ፍርፋሪ ለቃማ ከወደብ ከሚገኝ የቀረጥ ገቢ እኩል ልካፈል ብለው የመጠየቃቸው ጉዳይ በጣም ያስገርማል::

እንግሊዞቹና ግብፆቹ አጣብቂኝ ውስጥ ገብተው መውጫ ቀዳዳ በሚፈልጉበት ወቅት <ወደቤን ልትመልሱልኝ ይገባችኋል!> በማለት አምርረው ቢሟገቱ ኖሮ የምፅዋን ወደብ ማግኘት ይችሉ እንደነበር መገመት ይቻላል:: አሻፈረን ቢሉ እንኳን በወቅቱ የግብፅና የእንግሊዝ ወታደሮች በሱዳን ዓማፂያን ተከበው ስለነበር ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመውበት ቢሆን ኖሮ ያለጥርጥር የምፅዋን ወደብም ሆነ ሌሎቹን በግብፅ ቁጥጥር ሥር የነበሩትን ሁሉ አስለቅቀው መያዝ ይችሉ እንደነበር በጊዜው ሩቤንሰን (Rubenson) የተባለው ጸሐፊ ተችቶ የጻፈውን ዶ/ር ላጵሶ ጌ.ድሌቦ ዋቢ ጠቅሰው የጻፉትን ቀጥለን እንመልከት:-

*". . .የሱዳን መሐዲስቶች ወይንም ድርቡሾች በግብፅና በእንግሊዝ ወታደሮች ላይ በብሔራዊ የነፃነት አመፅ በተነሱበት ጊዜ በኢትዮጵያ ሰሜንና ምእራብ ጠረፎች በግብፅ ወታደሮች የተያዙ ሥፍራዎችን በቀጥታ ሄደው*

*በመውሰድ ፈንታ በጣም በሚያስገርም ሁኔታ በ1876 ዓ.ም ‹በዓድዋ ውል› አፄ ዮሐንስ ለብሔራዊ ነፃነታቸው በሚዋጉ እስላማውያን ላይ ለሁለቱም ማለትም ለሱዳንና ለኢትዮጵያ የጋራ ጠላቶች ከሆኑ ከግብጽና ከእንግሊዝ መንግሥታት ጋር ተባበሩ . . !" (የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ገጽ 269)*

ከስምምነቱ በፊትም ቢሆን ንጉሠ ነገሥቱ ምን ያህል ቸልተኝነት ያጠቃቸው እንደነበር ሩቤንሰን የተቹበትን ጠቅሰው ዶ/ር ላጵሶ ጌ ድሌቦ በተመሳሳይ ገጽ ያሰፈሩት እንዲህ ይነበባል፡-

*". . .በጉንደትና በጉራዕ ጦርነት አፄ ዮሐኝስና ራስ አሉላ ወራሪውን የግብፅ ጦር በታላቅ አርበኝነትና ወኔ ተዋግተዋል፡፡ የጠላትን ጦር ከደመሰሱ በኋላ ግን በጠላት እጅ የነበረውን መሬት በቀላሉ መውሰድ ሲችሉና ሲገባቸው ለመውሰድ አልሞከሩም ወይንም አላሰቡም፡፡ በተጨማሪም በሽንፈት ከጦር ሜዳ ለሸሸው ለግብፁ የጦር አዛዥ አፄ ዮሐንስ በራሳቸው አነሳሽነት ለሰላም ድርድር ያቀረቡትን አሳብ በጽሑፍ አስቀምጠው ከጦር ሜዳ ከተማረኩ እስረኞች ጋር ላኩለት፡፡ አዛዡም እስረኞቹን (ምርኮኞቹን) በነፃ ካገኛቸው በኋላ አፄ ዮሐንስ ለሰላም ያቀረቡትን አሳብ በመቀበል ፈንታ ‹ከጦር ሜዳ የተማረከውን የጦር መሣሪያ ጭምር በቅድሚያ ላኩልኝ› በማለት አፌዘባቸው. . ."* እውነትም ሊፌዝባቸው የሚገቡ ንጉሥ ነበሩ፡፡ ምርኮኞቻቸውን ይዘው መደራደር ሲገባቸው ደብዳቤ አሲዘው በመልቀቅ ምን ይዘው ነው የሚደራደሩት? ጠይቁ፡፡

ያም ሆነ ይህ ኢትዮጵያ ቃሏን አክብራ፣ በታሪክ "የኩፊት ጦርነት" በመባል የሚታወቀውን በራስ አሉላ የጦር መሪነት አዝምታ፣ ከባቢዎቹን (ድርቡሾቹን) ደምስሳ የተከበቡትን ነፃ አውጥታ በስምምነቱ መሠረት በምፅዋ በኩል አስወጥታ ወደየ አገራቸው እንዲሄዱ ስታደርግ በመልሱ ግን እንግሊዝ ጣሊያንን አምጥታ ምፅዋ ወደብ ላይ በማሥፈር ለኢትዮጵያ ጠላት ተከለችላት፡፡

## ስህተት አራት
## ራስ አሉላን ማጋዛቸው

እንደሚታወቀው የራስ አሉላ አባ ነጋ ቋሚ መፈክርና መርህ "የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ወሰን ቀይ ባሕር ነው!" የሚል ነበር፡፡ በመሆኑም ራስ አሉላ እንደ እሳት አለሎ እየተወረወሩ ቀደም ሲል ግብፆችን ድባቅ እየመቱ





እንደመለሷቸው ሁሉ በኋላም የንእግሊዝን የጡት ልጅ ኢጣሊያንን ሰዐጢ ላይ ድባቅ በመምታት አሣፍረው ቢመልሷትም የሩቅ ጊዜ ግቧ ኢትዮጵያን ጠቅላል መያዝ በመሆኑ አመቺ ጊዜና ወቅት እየጠበቀች መተንኮሷን አላቆመችም ነበር፡፡ በመሆኑም በጥር ወር 1879 ዓ.ም (ምፅዋ በሰፈረች በሁለተኛው ዓመት) ከምፅዋ በመንቀሳቀስ ዶጋሊ ላይ ጦርነት ከፈተች፡፡ በዚህ ወቅት አፄ ዮሐንስ መሀል አገር ነበሩ፡፡ እንዳሁኑ ስልክም ሆነ ሬዲዮ ባለመኖሩ የእዝ ሠንሠለትን ለመጠበቅ የሚቻል አልነበረም፡፡ በመሆኑም ራስ አሉላ ባላቸው ኃይል ከመመከት ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህ አፍጥጦ የመጣውን የጠላት ጦር ድባቅ በመምታት ካድዋ ድል ቀደምት የሆነውን የዶጋሊን ድል በታሪክ አስመዘገቡ፡፡ ዳሩ ግን ይህ አኩሪ ድል ሊያሸልማቸው ሲገባ ተወቅሰውና ተነቅፈው ከሥልጣናቸውና ከግዛታቸው ለመሻርና ለመጋዝ ምክንያት ሆነ፡፡

ጣሊያኖች የንጉሠ ነገሥቱን ደካማ ጎን ስለሚያውቁ "ራስ አሉላ ምንም ሣንነካው ወረረን" በማለት ገልብጠው በመጮሀቸው አፄ ዮሐንስ ከመሀል አገር ገሥግሠው ባሕረ ነጋሽ በመግባት "እኔ ሣላዝህ ጣሊያኖችን ወግተሃል!" በሚል አግዘው ለቦታው የማይመጥኑ የወንድማቸውን ልጅ ራስ ኃይለማርያምን የባሕረ-ነጋሽ እንደራሴ አድርገው በመሾም ጣሊያኖችን አስፈነደቋቸው፡፡ በዚህ ወቅት ደግሞ ድርቡሾች የንጉሠ ነገሥቱን እግር ጠብቀው ጎንደር ከተማ ድረስ በመዝለቅ ከ44ቱ አድባራት መሀከል 40ዎቹን አቃጥለው መጠነ ሠፊ ዘረፋም አካሄዱ፡፡ በድርቡሾቹ ወረራ የተበሳጨ አንድ የጎንደር ደብተራ "አላህ እነሱን ቢወዳቸው ነው ለድል ያበቃቸው!" ብሎ ማተቡን በጥሶ በመጣል በፈቃዱ ሰልሞ ከድርቡሾቹ ጋር ተቀላቅሎ መሄዱ ይነገራል፡፡

አፄ ዮሐንስ የጎንደርን መቃጠል ሰዐጢ ላይ ከጣሊያኖች ጋር ተፋጠው እንዳሉ በሰሙ ጊዜ ንጉሥ ተክለሃይማኖትን ወርደው ድርቡሾችን እንዲበቀሏቸው አዘዟቸው፡፡

ንጉሠ ተክለሃይማኖት የንጉሠ ነገሥቱን ትእዛዝ ተቀብለው እንዴት እንደዘመቱ ሂደቱን አለቃ ተክለ ሥላሴ ዋቅጅራ የተባሉ ሊቅ በጊዜው አብረው የነበሩ የጻፉትን ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ዋቢ ጠቅሰው ያሠፈሩት፡-

*"የጎጃም ሰው ያንጊዜ ወደ ጦርነቱ ሲሄድ አለቅጥ ጠግቦ እንደ እንቦሳ እየዘለለ የትምክህት ቃል ይናገር ነበር. . ."* ይሉና ፉከራውን እንዲህ በማለት አስቀምጠውታል፡-

"አይታሰስም ምጣድ በግምጃ

ዘንድሮ ድርቡሽ መትረፉን እንጃ!" እያለ ነበር ወደ ፍልሚያው የሄደው (ተክለፃድቅ መኩሪያ ገጽ 449)

ፍልሚያው የተካሄደው ጥር 10 ቀን 1880 ዓ.ም ሲሆን ቦታው ደንቢያ ሣር ውሃ ላይ ነበር:: የንጉሥ ተክለሃይማኖት ጦር ሊቁ እንደ ጠቀሱት በንቀት እየፎከረና እየተሳደበ ወርዶ ቢገጥምም ባንድ ዙር ፍልሚያ ብትንትኑ ወጥቶ በያቅጣጫው ሸሸት ሆነ:: ንጉሥ ተክለሃይማኖትና አቤኔ ሉቃስም ቀድመው ሸሹ:: ይህኑ የጦርነቱን ፍፃሜ አለቃ ተክለሥላሴ ዋቅጅራ እንዲህ አስቀምጠውታል:-

*". . .የንጉሥ ተክለሃይማኖት ወንድ ልጅ በለው ተክለሃይማኖት ዳሰው በተባለው ፈረሳቸው ምርኮ በምርኮ ሆነው ከግንባር ሲመለሱ አባታቸውና ጳጳሱ ሸሽተው ስላገኟቸው ተናደው ‹እኔን እንመለስ ሳይሉ ለሞት ዳርገውኝ ራስ በዛብህን ይዘው ፐለውኝ ሄዱ› በማለት ብዙ ቀን ተኳረፉ"*

በዚሁ በሣር ውሃው ፍልሚያ የሴት ልጃቸው ባል ደጃዝማች ጀንበሬ ጥሩ ሙያ ሠርተው ሲሰው ሚስታቸው ምንትዋብ ተክለሃይማኖት ከባላቸው ጋር ነበሩና ተማርከው መወሰዳቸውንና በእስላም እጅ አልበላም ብለው በርሃብ ተሠቃይተው እንደሞቱ ሊቁ ተርከዋል:: በተማረኩ ጊዜም የሚከተለውን ስንኝ መቋጠራቸውን አለቃ ተክለሥላሴ ጽፈዋል::

*"ጎጃም የምትሄዱ እንደኔ ማትቀሩ*
*ርኩስ በልታ ሞተች ብላችሁ ንገሩ!"*

አፄ ዮሐንስ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ድል መሆናቸውን በሰሙ ጊዜ ቀደም ሲል ፎክረው መውረዳቸውን ሰምተው ነበርና "ፎክረህ ወርደህ ተሸንፈህ፣ ሰውን አስፈጅተህ ተመለስህ!" ብለው ከወቀሷቸው በኋላ ንጉሥ ምኒልክን "ለኔ ብለህ ሣይሆን ለሃይማኖትህና ለማተብህ ስትል ሂድና ከድርቡሾች ጋር ተዋጋ!" በማለት እንዳዘዟቸው ተክለፃድቅ መኩሪያ አለቃ ተክለሥላሴን ዋቢ ጠቅሰው በገጽ 452 አስፍረዋል::

በዚህ አጋጣሚ ለዚህ ዘመን ወጣት ልጃገረዶች ወይንም ቆንጆዎች አራት ሞገደኛ ሞጋሽ ምንትዋቦችን አስተዋውቆ ማለፉ ጠቃሚ ይመስለኛል::

የመጀመሪያዋ ምንትዋብ ቋረኛዋ ያፄ በካፋ ባለቤት እቴጌ ምንትዋብ ሲሆኑ በፖለቲካው መስክ ከፍተኛ ተፅእኖ ፈጣሪ እንደነበሩ ይነገርላቸዋል::





ሁለተኛዋ ምንትዋብ ያፄ ቴዎድሮስ የመጀመሪያ ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች ዓሊ (የልጅነት ስማቸው ምንትዋብ ነበር) ለባላቸው ኮከብ አማካሪ እንደነበሩ ይተረከላቸዋል::

ሦስተኛዋ ሞገደኛ ምንትዋብ አፄ ቴዎድሮስ አባቷን፣ ባሏንና ወንድሟን የገደሉባት ስትሆን:-

*"ሺ ፈረስ ከኋላው ሸፈረሽ ከፊቱ*
*ይሆን ሳታይ ሞተች ኮሶ ሻጭ እናቱ . . .!"*

ብላ በድፍረት ስንኝ በመቋጠር እልኋን የተወጣችው ናት::

አራተኛዋ ሞገደኛ ምንትዋብ ካባታቸውና ከባላቸው ጋር ደንቢያ ሣር ውሃ ዘምተው ቢማረኩም ሃይማኖታቸውን ለመቀየር ቀርቶ "በእስላም እጅ አልበላም!" ብለው በርሃብ ተሰቃይተው መሞታቸው ፅናታቸውን የሚያሣይ ነው::

ንጉሥ ምኒልክ ያፄ ዮሐንስን ትእዛዝ ተቀብለው የሸዋንና የወሎን ጦር አስከትለው በሚያዝያ ወር ደብረታቦር በመግባት ሠፈሩ:: የቤጌምድር ጦር ተጠቃሎ እስከሚገባላቸው ድረስም 19 ቀናት ያህል ከተቀመጡ በኋላ በመጨረሻ ጎንደር በመግባት አዘዞ ላይ ሠፈሩ::

ንጉሥ ምኒልክ አዘዞ ሠፍረው በቆዩባቸው ቀናት ውስጥ ሁለት ጊዜ ወታደራዊ ሠልፍ አድርገዋል:: የጦሩ ብዛትም ሆነ የታጠቀው መሣሪያ ከበቂ በላይ በመሆኑ ሣር ውሃ ላይ መሽጎ የነበረው የድርቡሽ ሠራዊት ገና ሣይዋጋ መቋቋም እንደማይችል አውቆ ሙተማ ወርዶ መመሸጉን ታሪክ ጸሐፊዎች ጽፈዋል::

ንጉሥ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥቱ ባዘዟቸው መሠረት ወርደው መግጠም ሲችሉ በራስ አሉላ አባነጋ የደረሰው የመጋዝ እጣ በኔም ላይ ሊደርስ ይችላል በሚል ሥጋት ይመሥላል የንጉሠ ነገሥቱን የመጨረሻ ትእዛዝ ለመቀበል መልእክተኞችን ላኩ::

መልእክተኞች በቅንነት ንጉሠ ነገሥቱን ደስ ያሰኙ መስሏቸው "ምኒልክ ይዘውት የተሠለፉ የሠራዊት ብዛትና የታጠቀው የጦር መሣሪያ ጥራት እንኳንስ የድርቡሽ ጦር የእንግሊዞችም ጦር አይመከተው" እያሉ በማጋነን ሲተርኩላቸው በዙሪያቸው የከበቧቸው መኳንንትም ቀድሞውንም ቢሆን ለምኒልክ ቀናነት አልነበራቸውምና ተጨማሪና የመጨረሻ ውድቀታቸውን

የሚያፋጥን ሥህተት እንዲሠሩ ገፋፏቸው:: “እንዲህ ከሆነማ ድርቡሾችን ድል አድርጎ በማረከው የጦር መሣሪያ መልሶ ሊወጋን አይደል” በሚል ሥጋት “በመጣህበት አድርገህ አገርህን ሸዋ ግባ” የሚል መልእክት አስተላለፉላቸው::

ንጉሥ ምኒልክ ባፄ ዮሐንስ ያልተጠበቀ መልስ በጣም ተገርመው በመጡበት ሳይሆን ወደ ጎጃም በመሻገር ከንጉሥ ተክለሃይማኖት ጋር በመገናኘት አፄ ዮሐንስ ከሁለት አንዳቸውን ወይንም ሁለቱንም ሊወጓቸው ከመጡ ካንድ ላይ ሆነው ሊወጓቸው ተማምለው መለያየታቸው እውነት ነው:: እንዲያውም ንጉሥ ምኒልክ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ሣር ውሃ ላይ በተማረከባቸው የጦር መሣሪያ ምትክ ወይንም ከዚያም በላይ ሁለት ዘመናዊ መድፎችና 250 ሲናድር ጠመንጃዎችን ከበቂ ጥይቶች ጋር ሠጥተዋቸው መሄዳቸውን አለቃ ተክለሥላሴ ዋቅጅራ ጽፈዋል::

አፄ ዮሐንስ ንጉሥ ምኒልክ ከንጉሥ ተክለሃይማኖት ጋር በመገናኘት ዶልተውባቸው ሸዋ መግባታቸውን ባወቁ ጊዜ ባሕረ ነጋሽን አዲስ ለሾሟቸው ለራስ ኃይለማርያም ትተው፣ ራስ አሉላን ካጋዙበት አስመጥተው እሳቸውን በመያዝ ገሥግሠው መቀሌ ገቡ::

ሌላው አሣዛኝ ነገር ንጉሠ ነገሥቱ መቀሌ ከመድረሳቸው ቀደም ብለው ታመው ነበርና ልጃቸው ራስ አርአያ ዮሐንስ (የዘውዲቱ ምኒልክ ባል) በሞት በመለየታቸው ሐዘናቸው መሪር እንደነበር ይነገራል:: በርግጥም በዚያች የወከባ ወቅት የልጃቸው በሞት መለየት ከባድ ፈተና እንደሚሆንባቸው ምንም ጥርጥር የለውም::

ንጉሥ ነገሥቱ ምንም እንኳን ከባድ ሐዘን ቢወድቅባቸውም ያገር ጉዳይ ደግሞ ከምንም በላይ ነውና ሰኔ ወር መጨረሻ ላይ ዘውዲቱ ምኒልክን ጭምር ይዘው ቁጥሩ እጅግ ብዙ የሆነ ሠራዊት መርተው ደብረታቦር ገቡ::

## ስህተት አምስት

## በጎጃም ሕዝብ ላይ የወሰዱት ያልተገባ ርምጃ!

አፄ ዮሐንስ ሐምሌ እንደገባ ከደብረታቦር ተነስተው 15 ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዘው አሞራ ገደል ሲደርሱ ሠፈራ በማድረግ መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው ጉባዔ ተቀመጡ:: የጉባዔው ዓላማ “በቅድሚያ ድርቡሽን እንምታ ወይንስ ወደ ጎጃም ዘምተን ንጉሥ ተክለሃይማኖትን፣ ከዚያ ደግሞ ወደ ሸዋ





ተሻግረን ምኒልክን ማንበርከክ” የሚል ነበር:: በመሆኑም ወደ ጎጃም እንዝመት የሚለው ሀሳብ በማመዘኑ ወደ ጎጃም ተሻገሩ::

አፄ ዮሐንስ ወደ ጎጃም ይዘውት የዘመቱት የሠራዊት ብዛት፣ እንደ ሀምሌ ጎርፍ የሚያጥለቀልቅ በመሆኑ ሕዝቡ ገርሞት:-

*“እንካሣው በምርኩዝ እውሩ በመሪ የተከተለዎ*
*አህል አይበቅልም ወይ ንጉሥ ባገርዎ ”* ብሏቸዋል::

ንጉሥ ተክለሃይማኖት እንደ ተባለው አፄዮሐንስ የትግራይን ሠራዊት አግበስብሰው እንደሚመጡባቸው ያውቁ ነበርና ለረጅም ጊዜ የሚያቆይ ሥንቃቸውን፣ ምርጥ ታማኝ ሠራዊታቸውን ይዘው ሙተራ ተራራ በመውጣት ምሽግ ይዘው ጠበቋቸው::

አፄ ዮሐንስ፣ ንጉሥ ተክለሃይማኖት የመሸጉበትን ተራራ ከበው ብዙ ቀናት በመድፍ እየደበደቡ ቢያስጨንቁም ፍንክች የሚሉ አልሆኑም:: በሚያስደንቅ ሁኔታ ወደ አንባው ለመውጣት የሞከሩትን ወታደሮች በናዳ እንደቲማቲም እየጨፈለቁ ፈጇቸው:: የመድፉ ጥይትም እያፏጨ ወደ ዓባይ በረሃ እየሄደ ከሚያርፍ በስተቀር አንዳች ጉዳት ሊያደርስ አልቻለም:: ካምባው ወገብ ላይ የሚያርፈውም (ጊዜው ክረምት በመሆኑ) ከጭቃው ርሳሱ እየተረፎቀ ደፍ የሚል ድምፅ ከሚያሰማ በስተቀር ጥቀርሻ የመሰለ አቧራ እያስነሳና የተደበላለቀ መብረቃዊ ድምፅ እያሰማ የንጉሥ ተክለሃይማኖትን ጦር ማሸበር አልቻለም:: በዚህ የተበሳጩት ንጉሠ ነገሥት ሠራዊታቸውን በድፍን ጎጃም በማሠማራት ሰላማዊውን ሕዝብ አስመደመዱት:: ጦራቸው እጅግ በሚያሳፍርና በሚያሳዝን መልኩ ድርቡሽ በጎንደር ሕዝብ ላይ ከፈፀመው ጥፋት የከፋ ጥፋት በጎጃም ሕዝብ ላይ ፈፀመ::

ገበሬዎቹ በሬ ጠምደው ከሚያርሱበት ዘሩ እንደ ተዘራ በሬዎቹ ተፈተው ታርደው ሞፈሩና ቀንበሩ እየተፈለጠ ለሥጋ መጥበሻነት ዋለ:: የጥገት ላሞች ሳይቀሩ እየታረዱ እንቦሶቻቸው ሲያላዝኑ መስማት አንጀትን የሚያላውስ ሆነ:: ሕዝቡ በክርስቲያን ወግ እየሸሸ በያቅራቢያው ካለ ደብር የሙጥኝ ቢልም ያፄው ወታደሮች እያሣደዱ ጨፈጨፉት:: የቤተክርስቲያን በሮች፣ መቃዎች እየተፈለጡ የሥጋ መጥበሻ ሆኑ:: ፅላቶች እንዳልባሌ እቃ የትም ተጣሉ:: ልብሷን የተገፈፈችና ከብቶቿ የታረዱባት አንዲት ሴት:-

*“በላይኛው ጌታ በባልንጀራዎ*
*በቅዱስ ሚካኤል በጋሻ ጃግሬዎ*

*በጽላተ ሙሴ በነጭ አምብዛዎ*
*ጎጃምን ይማሩት ፈሪም አንለዎ!" ብላቸዋለች:: (ተክለ ፃድቅ መኩሪያ ገጽ 504-5)*

ይህነኑ ያፄ ዮሐንስን ወረራ አለቃ ተክለሥላሴ ዋቅጅራ ያይን እማኝነታቸውን ሲገልፁ:-

*". . .አፄ ዮሐንስ ጎዛምን ላይ ሠፍሮ አምባውን ሊሠብር በጭምትና በነማይ አፋፍ መድፉን ጠመደ:: ግን አልሆነለትም:: ኃይለኛው መድፍ ጅብላን እያለፈ ዓባይ በረሃ ወደቀ:: ቀላሉ መድፍ ደግሞ ያምባውን ገደል (ወገብ) እየመታ ቀረ:: ያን ጊዜ የንጉሥ ተክለሃይማኖት ወታደር (ተኳሽ) የመድፉን አረር (ጥይት) በመድፉ አፍ አስገብቶ ተረተረው! . . . ከዚህ በኋላ ያፄ ዮሐንስ ወታደር በጎዛምንና በማቻከል የተገኘውን የቤተክርስቲያን ሣንቃ እየነቀለ፣ ማገሩን እየፈለጠ አነደደው! ታቦቱንም ከመንበሩ እያወጣ በየሜዳው በጣለው ጊዜ ጳጳሱ አቡነ ሉቃስ ‹ድርቡሽን አጠፋለሁ ብለህ መጣሁ ያልከው ለጎጃም ሕዝብ አንተ ድርቡሽ ሆንክበት› አሏቸው" በማለት የጻፉትን ተክለፃድቅ መኩሪያ በገጽ 503 አስፍረውታል::* እውነትም የወረራውን አስከፊነት ሕዝቡ እንዲህ ሲል ገልጾታል:-

*"ጎጃም ተቃጠለ ዓባይ እስከ ዓባይ*
*ትግሬ ቅጠል ይዞ ሊያጠፋው ነወይ"*

ከዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ቁምነገር አለቃ ተክለሥላሴም ሆኑ አቡነ ሉቃስ ከተለመደውና ከባህላችን ባፈነገጠ መልኩ አፄ ዮሐንስን "አንተ" እያሉ ነበር የገለፅዋቸው:: ምናልባትም አፄው የፈፀሙት ተግባር ከተራ የመንደር ሽፍታ ያነሰ በመሆኑ ላንድ ንጉሠ ነገሥት ሊሰጥ የሚገባውን ክብር ነፍገዋቸዋል ማለት ነው::

ንጉሠ ነገሥቱ የጎጃምን ሕዝብ በሀምሌው ምድር የቁም ሲቃይ በሚያሣዩበት ወቅት ጣሊያኖች በበኩላቸው የሳቸውን መራቅ አጋጣሚውን በመጠቀም ከምፅዋ ገሥግሠው አሥመራ በመግባት ከመረብ ምላሽ ያለውን አገር "ኤርትራ" ብለው በመሰየም አዲስ ቅኝ ግዛት ፈጠሩ::

ቀደም ሲል እሳቸው ሰዐጢ በነበሩበት ወቅት ያጎታቸው የራስ አርአያ ልጅ ደጃዝማች ደበበ አርአያ እሳቸውን ከድቶ ምፅዋ በመሄድ ለጣሊያኖች የጌታ አደሮ ነበርና ልክ እሳቸው የናፒየርን ጦር ከዘይላ ወደብ እየመሩ መቅደላ እንዳደረሱት ሁሉ ደጃዝማች ደበበ አርአያም ጣሊያኖችን ከምፅዋ ወደብ መንገድ እየመራ በማምጣት እንደራሴቸውን ራስ ኃይለማርያምን





በቀላሉ ገሎ ባሕረ-ነጋሽን በጠላት እጅ እንድትወድቅ አደረገ:: የቀ.ኃ.ሥላሴ አማች ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣም ያደረገው እንዲሁ ነበር::

እንዲህ ሀቁ ይኸ ሆኖ እያለ ነው የሻዕቢያና የሕወሓት ሰዎች "ምኒልክን ኤርትራን ፈርሞ ለቋል" እያሉ አፅማቸውን የሚፈጩት:: አፄ ዮሐንስ ግድግዳውን ራስ አሉላ አባ ነጋን ይዘው ወደ መሀል አገር በመምጣት በነፃ የለቀቋትን ወይንም ያስረከቧትን አገር ምኒልክ በምን አቅማቸው ነበር ያነዬ ሊያስመልሷት የሚችሉት? ለማንኛውም ይህንን በተመለከተ ኋላ ላይ የሳቸውን ታሪክ በምንተርከበት ወቅት የምናየው ይሆናል:: አሁን ወደ ጎጃም እንመለስ::

ከፍ ብዬ ለመግልጽ እንደሞከርኩት ንጉሠ ነገሥቱ ንጉሥ ተክለሃይማኖትን ባሰቡት መልኩ ድል አድርገው ሊማርኳቸው እንደማይችሉ ባወቁ ጊዜ ወደ ሸዋ ተሸግረው ሌላ ጥፋት ለማጥፋት ባሰቡበት ምሽት ዘውዲቱ ምኒልክ ያባታቸው እጣ ፈንታ ስላሳሰባቸው:-

"ባለቤቴ ራስ አርአያ ቢኖሩ ኖሮ ጃንሆይና አባቴ ለጦርነት አይሰላለፉም ነበር" ብለው በመናገራቸው ይኸው ላፄ ዮሐንስ ሲነገራቸው የልጃቸው ሀዘን ገና ካንጀታቸው አልወጣም ነበርና ስቅስቅ ብለው አለቀሱ ይባላል:: ያች ምሽትም የሐዘን ምሽት ሆና ማምሸቷ ይተረካል::

ከዚህ በኋላ አፄ ዮሐንስ ወደ ሸዋ የመዝመታቸውን ጉዳይ ጠብ ርግፍ አድርገው በሙተው ዘውዲቱ ምኒልክን ደረጃዋን በጠበቀች በቅሎ፣ በመኳንንት አሣጅበው፣ ከንጉሥ ምኒልክ ጋርም እንዲያስታርቋቸው ለራስ ዳርጌ ደብዳቤ ጽፈው ወደ ሸዋ ላኳቸው::

አፄ ዮሐንስ ሠራዊታቸው በጎጃም ሕዝብ ላይ የፈፀመውን ጥፋት ለራስ ዳርጌ በጻፉት ደብዳቤ በፀፀት መልክ እንዲህ ነበር ያሉት:-

*". . .በኔም፣ በድሃውም (በሕዝቡ) ኃጢዓት እንደሆነ አይታወቅም አገሩን (ጎጃምን) ሣጠፋው ከራመሁ . . ."* (ተክለፃድቅ መኩሪያ ገጽ 442)

የሆነ ሆኖ በዘውዲቱ ምኒልክ አነጋገር ምክንያት ወደ ሸዋ ሊያደርጉት የነበረውን ጉዞ ሠርዘው ፊታቸውን ወደ ሙተማ ማዞራቸውን እናስተውላለን::

አንዳንድ አዛውንቶች ግን ሐሳባቸውን የቀየሩት "በዘውዲቱ ንግግር ሣይሆን በጳጳሱ ባቡነ ሉቃስ ውግዘት ሕሊናቸው ተነክቶ ነው" ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ "ንጉሠ ነገሥቱ ፊታቸውን ወደ ሙተማ ያዞሩት በዘውዲቱ

ንግግርም፣ ባቡኑ ውግዘትም አይደለም። ንጉሥ ምኒልክ ያፄ ዮሐንስን ሃይማኖተኛነት ያውቁ ስለነበር ባሕታውያንን ወደ ጎጃም በመላክ “. . .ወደ ሸዋ የሄደህ እንደሆነ ንጉሥ ምኒልክን ድል ታደርጋለህ፤ በነፍስህ ግን ትጎዳለህ። ወደ መተማ የሔደህ እንደሆነ ግን በሰማዕትነት ትሞታለህ በነፍስህም ትጠቀማለህ› ሲሏቸው ‹በሥጋዩ ተጠቅሜ በነፍሴ ከምጎዳ ሞት ይሻለኛል› ብለው ወደ መተማ ሔዱ. . .” ሲሉ ይተርካሉ። (ተክለፃዲቅ መኩሪያ ገጽ 536) ወደ መተማ ለመዝመት ጉዞ በጀመሩ ጊዜ ሕዝቡ፡-

*“ዘንድሮ ንጉሡ በድል ቢመለሱ*
*አውነትም ጎጃሜ ጎልደ፟ፏል ምላሱ!”* ብሏቸዋል።

ከስንኞቹ የምንረዳው ቁምነገር በህምሌው ምድር ያሰቃዩት ሕዝብ ደጀን ሊሆናቸው ሲገባ ረግሞና አውግዞ የሸኛቸው መሆኑን ነው።

አፄ ዮሐንስ መተማ እንደ ወረዱ በቀጥታ ተጣድፈው ወደ ጦርነት አልገቡም ነበር ይባላል። የኃይላቸውን መሣሣት፣ የባሕር-ነጋሽን በጣሊኖች እጅ መውደቅ አውቀው ስለነበር በርቅ ለመጨረስ ብዙ ሙከራዎችን አድርገው ነበር። ዳሩ ግን የድርቡሾቹ መሪ በንቀትና በማንጓጠጥ “ርቅ ልናደርግ የምንችለው በመጀመሪያ ሃይማኖተዎትን ቀይረው እስልምናን ሲቀበሉ ብቻ ነው” ሲላቸው እንደ አፄ ዮሐንስ ላለ ለሃይማኖቱ ቀናዒ ንጉሥ ምን ያህል ሊጎመዝዛቸው እንደሚችል መገመቱ አይከብድም። በዚህ እልህና ብስጭት ሣይሆን አይቀርም በመሪነታቸው ከርቀት ሆነው ማዋጋት ሲችሉና ሲገባቸው እንደ አንድ ወታደር ከመሀል ገብተው በጀግንነትና በኩራት ህይወታቸው ሊያልፍ ችሏል። ሕዝቡ ግን እንደ አንድ ወታደር መሀል ገብተው መዋጋታቸውን በመንቀፍ በጊዜው የሚከተለውን ብሏቸዋል፡-

*“አፄ ዮሐንስ ሞኝ ናቸው*
*እኛም ሁላችን ናቅናቸው*
*ንጉሥ ቢሏቸው በመሀሉ*
*ወሰን ጠባቂ ልሁን አሉ!”*

ያም ሆነ ይህ አፄ ዮሐንስ ስህተቶቻቸውን ሁሉ መተማ ወርደው ላገራቸው ዳርድንበር አንገታቸውን በመስጠት በደማቸው አጥበዋቸው አልፈዋል። ያ ጊዜም የራሱን ጊዜ ሆኖ አልፏል። በተረፈ ግን ለኤርትራ መገንጠልም ሆነ እስካሁን ከፍለን ላልጨረስናቸው እዳዎች የተጋለጥነው <“የሔዊት ስምምነት ምክንያት ነው> ሰንል ከባዶ ተነስተን አይደለም። ቢያንስ ካሥር ያላነሱ መሠረታዊ ነጥቦችን ይዘን ነው።





1ኛ. አፄ ዮሐንስ ከሪር አድሚራል ሔዊት ጋር ጥቅም በማያገኙበት ጉዳይ ባይፈርሙ ኖሮ እንግሊዝ ጣሊያንን አምጥታ ምፅዋ ላይ ባላሠፈረች ነበር።

2ኛ. ጣሊያን ምፅዋ ወደብ ባትቀመጥ ኖሮ ዶጋሊ ላይ ጦርነት ባልከፈተች ነበር። በመከፈቷ ግን ድባቅ ተመታ በውጤቱ ለራስ አሉላ መሻር ምክንያት ሆና በሩ ተከፈተላት።

3ኛ. በማይመለከታቸውና በማያገባቸው ጉዳይ ገብተው መሃዲስቶች ለነፃነታቸው ሲሉ የከበቧቸውን የቅኝ ገዥ ወታደሮች ተዋግተው በማስለቀቃቸው ለጎንደር አድብራት መቃጠልና መዘረፍ ምክንያት ባልሆኑ ነበር።

4ኛ. የጎንደር አድባራት መቃጠልና መዘረፍ ለንጉሥ ተክለሃይማኖት አማች መገደልና ለሴት ልጃቸው መማረክም ሆነ ጠቅላላ ሽንፈት ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ለመቃቃርም ሆነ ለጭራሹ መለያየት ምክንያት ሆነ።

5ኛ. የሔዊት ስምምነት ሌላው ውጤት ለጎጃም ሕዝብ በንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት መመዝበሩና የደጀኑን ሕዝብ ድጋፍ ያጡበትና ርቃናቸውን የቀሩበት መሆኑ ነበር።

6ኛ. የሔዊትን ስምምነት ባይፈርሙ ኖሮ የሣቸውን እግር ጠብቀው ጣሊያኖቹ በደጃዝማች ደበበ አርአያ መሪነት አሥመራ ገብተው ከመረብ ምላሽ ያለውን አገር <ኤትር> ብለው በመሰየም ቅኝ ግዛት አድርገው መያዝ ባልቻሉ ነበር። ያድዋ ጦርነት መከተልም የሥምምነቱ ውጤት ነበር።

7ኛ. የሔዊትን ስምምነት ባይፈርሙ ኖሮ የድርቡሾቹ መሪ ለሰላም እጆቻቸውን ሲዘረጉለት በበቀል ተነሳስቶ <በመጀመሪያ ሲሰልሙ ነው ድርድር ማድረግ የምንችለው> ብሎ ባይልከባቸው ኖሮ ምናልባትም በእልህና በብስጭት እንደ አንድ ተራ ተዋጊ ወታደር ከመሀል ገብተው በጥይት ተመተው መውደቅ ባልቻሉ ነበር።

8ኛ. የሔዊትን ስምምነት ባይፈርሙ ኖሮ ባምስት አመቱ ያርበኙነት ወቅት ኢጣሊያ ወጥታ በነፃ አውጭ ስም እንግሊዝ ገብታ አሥር ዓመት በመቆየት ሌላ መርዝ ዘርታ ባልወጣች ነበር።

9ኛ. የሔዊትን ስምምነት ባይፈርሙ ኖሮ ሻዕቢያና ጀብሐ የሚባሉ ተገንጣይ ቡድኖች ሊፈጠሩ ባልቻሉ ነበር።

10ኛ. ሻዕቢያ የተባለ ድርጅት ባይፈጠር ኖሮ የመገንጠል ጥያቄ አይኖርም ነበር፡፡ የመገንጠል ጥያቄ ካልኖረም ሕወሓት የሚባል የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት አይፈጠርም ነበር፡፡ የዚህ ድርጅት መፈጠር ግን የሔዊት ስምምነት የመጨረሻ ውጤት ነው ባይባልም ለጊዜው ኤርትራን አሥገንጥሎ የባሕር በር በላያችን ላይ አዘግቶብናል፡፡ ለዚህም ነው ገና ከፍለን ያልጨረስናቸው እዳዎች እንዳሉብን ለመጠቆም የሞከርኩት፡፡

<>◇<>





# ዳግማዊ አፄ ምኒልክ



*ዳግማዊ አፄ ምኒልክ*

አፄ ምኒልክ ወደ ሥልጣን በወጡበት ወቅት ባገር ውስጥ ካፄ ቴዎድሮስና ካፄ ዮሐንስ ጋር ሲነፃፀር ሰላም ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ግን ግዛትን ለማስፋፋት ሲሉ በምሥራቅ፣ በደቡብና በምእራብ ኢትዮጵያ የሰበሰ ፍልሚያ አላካሄዱም ማለት አይደለም፡፡ ኃይለኛ የሥልጣን ተፎካካሪ አልገጠማቸውም ለማለት እንጅ፡፡

ባገር ውስጥ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል በውጭ ያለው የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ ሁሉም ነገር ተጠናቋል ማለት ይቻላል፡፡ ቅኝ ገዥዎች አፍሪካን ከኢትዮጵያና ከላይቤሪያ በስተቀር ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር አድርገዋቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ አጎራባች አገራት ሱዳን፣ ኬንያና ኡጋንዳ በእንግሊዝ ቁጥጥር ሥር ሲውሉ ከፊል ሶማሊያ በእንግሊዝ ይዞታ ስር ቀሪው ደግሞ በኢጣሊያን ተይዟል፡፡ ጅቡቲ በፈረንሳይ



*ዳግማዊ አፄ ምኒልክ*

ተይዛለች፡፡ ኢትዮጵያንም ለመቀራመት የሦስትዮሽ ውል ተዋውለዋል፡፡ ባሕረነጋሽም ካናት አገሯ በኢጣሊያን ተገንጥላ <ኤርትራ> ተብላ በቅኝ ግዛት ሥር ወድቃለች፡፡

እንግዲህ የውጭው ሁኔታ ይህንን ሲመስል ንጉሠ ነገሥቱ ያድዋ ጦርነት እስከ ተጀመረበት ድረስ ከውጭ ወራሪዎች ጋር በዲፕሎማሲያዊ መስክ እየተፋለሙ ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ለዘመኑ ሥልጣኔ በራቸውን በመክፈት የሚችሉትን ሁሉ አድርገዋል፡፡ ይህንንም ሲያደርጉ ከወግ አጥባቂ መኳንንት ጋር እየተጋጩ እንደነበር ታሪክ ያወሳል፡፡ በመሆኑም በዘመናቸው ካከናወኗቸው መሀከል :-

1. *ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል (1902 ዓ.ም)*
2. *ዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት (በ1897 ዓ.ም)*
3. *ተሽከርካሪዎችን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፡፡*
4. *ከጂቡቲ አዲስ አበባ የባቡር ሐዲድ ማዘርጋት (ከ1890-1907 ዓ.ም ድረስ)*
5. *የደን መመናመን ወደ ፊት ሊከሰት ይችላል ብለው በማሰብ በዘመናቸው ባሕርዛፍን ካውስትራሊያ በማስመጣት ማስተከላቸውና ማራባታቸው፤*
6. *የሥልክ መሥመር ማዘርጋታቸው ሊጠቀሱ ከሚገባቸው ጥቂቶች ናቸው፡፡*

ቴሌኮሚኒኬሽን ወዳገራችን የገባው በ1886 ዓ.ም ያድዋ ጦርነት ከመከፈቱ ሁለት ዓመት ቀደም ብሎ ሲሆን በዓለም ደረጃ ገና አዲስ ግኝት ነበር፡፡ በአልክሳንደር ግርሃም ቤል በተፈለሰፈ በ17ኛው ዓመት ነበር ወዳገራችን የገባው፡፡ ይህም እጅግ ፈጥኖ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ፈጥኖ የመግባቱን ያህል ግን መቶ ሃያ ዓመት ተጉዞ ዛሬ አለማደጉ የሚያስገርም ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ አፄ ምኒልክ በዘመናቸው ወቅቱ ያፈራቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ወዳገራቸው ለማስገባት ጥረት አድርገዋል፡፡

የመጀመሪያው የሥልክ መሥመር ዝርጋታ የተካሄደው ካዲስ አበባ ወረዒሉ፣ ከወረዒሉ ቤጌምድር ጋይንት (አኔ አትብቴ ከተቀበረባት አጋጥ መናመስከ ነበር) ከዚያ ደግሞ ደብረታቦር ነበር የገባው፡፡ጋጥ መናመስከ ደብረታቦርንና ወረዒሉን በማዞሪያነት ማገናኛ ነበረች፡፡ የስልክ ቤቱ ፍራሽ ዛሬም ድረስ አለ፡፡ አገልግሎቱ የተቋረጠው ግን በጠላት ወረራ ጊዜ ነበር፡፡





በመሠረቱ አፄ ምኒልክ ያከናወኗቸው ዘመን ተሻጋሪ የጥበብ ውጤቶች የተጠቀሱት ብቻ ነበሩ ማለት አይደለም፡፡ እጅግ በርካታዎች ነበሩ፡፡ እነዚያን ሁሉ ከዚህ ላይ መዘርዘሩ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ጥቂት ምሳሌዎችን ብቻ ጠቀሼ ልለፍ፣ ከዚህ ይልቅ ሰፋ አድርጌ ለማየት የሞከርኩት የሚወቀሱበትንና የሚወገዙበትን ነው፡፡

አፄ ምኒልክን አጥብቀው የሚወቅሷቸውና የሚያወግዟቸው ያሁኖቹ የኤርትራ ልጆች (ሻዕቢያ) እና የትግራይ ፋኖዎች (ሕወሓቶች) ናቸው፡፡

ቀደም ብለን ያፄ ዮሐንስን ስህተቶች ባየንበት ወቅት ኢጣሊያኖች ባሕረ ነጋሽን ከመረብ ምላሽ <ኤርትራ> ብለው በመሰየም የያዟት አፄ ዮሐንስ ራስ አሉላን ይዘው ወይንም አግዘው ወደ መተማ በዘመቱበት ወቅት አጋጣሚውን በመጠቀም ነበር፡፡ ከዚያ በኋላም ባፄ ዮሐንስ ዙፋን ወራሾችና በንጉሥ ምኒልክ መሀከል በተፈጠረው የሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት ሁኔታዎች ስላገዟቸው ተደላድለው ለመቀመጥ ችለዋል፡፡ በኋላም ንጉሥ ምኒልክ አፄ ቢሆኑም ቀሪዋን ኢትዮጵያ ይዘው አመች ጊዜን ከመጠበቅ ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም፡፡ እንዲያውም ለቀሪዋ ኢትዮጵያ በመስጋት ኢጣሊያኖች የመረብን ወንዝ ተሻግረው እንዳይወሯቸው የውጫሌን ውል መዋዋላቸው እውነት ነው፡፡ እንግዲህ ሻዕቢያ የሚወነጅላቸው:-

1. "ከመረብ ወዲያ ያለውን አገር አገራቸው እንዳልሆነ ሁሉ በውል ፈርመው ለቀዋል" በማለት ነው፡፡ ሻዕቢያና ሕወሓት የወቅቱን የዓለምን ተጨባጭ ሁኔታና የምኒልክን አቅም በቅጡ ያጤኑት አይመስሉም፡፡ ለነገሩ ቢያጤኑትም የመገንጠል መርህ ያነገቡ ስለሆነ ምኒልክን ለማውገዝ ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡ እውነታው ግን ዙሪያውን በቅኝ ገዥዎች ተከበው እያሉ ኤርትራን ለማስለቀቅ ቢተነኩሱ ኖሮ መዘዙ ምን ሊሆን እንደሚችል ሕሊና ያለው ሰው ሊገነዘበው ይችላል፡፡ በዚያን ጊዜ የነበራቸው አማራጭ ቀሪዋን ኢትዮጵያ ይዘው መቆየት ነበር፡፡ የዚህ ሀቅም ኢጣሊያ ኤርትራ ላይ ተወስና መቅረት አለመሆኑ በውጫሌ ውል አንቀጽ 17 ምክንያት አይቀሬውን ያድዋን ጦርነት ማስከተሉ ነበር፡፡
2. ሌላውና ዋናው መወቀሻቸው ደግሞ "ያድዋን ድል እንደተቀዳጁ ወደ ፊት ቢገፉ ኖሮ ኢጣሊያኖችን ከኤርትራ ምድር ጠራርገው ማባረር ይችሉ ነበር" የሚል ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች አሁንም ያልተገነዘቡት ነገር ቢኖር ድል ማድረግ እንዳለ ሁሉ መልሶ ድል መሆን እንዳለም ነው፡፡ ኢጣሊያኖች ቢያንስ ከኢትዮጵያኖች የተሻለ የጦር መሣሪያ ነበራቸው፡፡

ሠራዊታቸውም የሠለጠነ ዘመናዊ ወታደር ነው:: የሥንቅ ዝግጅታቸውም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ደረቅ ሥንቅ ነው:: ለቁስለኞችና ለቀላል በሽተኞች የሚሆን መድኀኒትና የሕክምና ሙያተኞችም ነበሯቸው:: ባንፃሩ ያፄ ምኒልክ ሠራዊት የታጠቀው መሣሪያ አንድ ጎረስ ሲሆን በዚህ ላይ በዘመናዊ ውትድርና የሠለጠነ ሣይሆን በፈቃዱ የዘመተ የከተቴ ጦር ነበር:: ያ የከተቴ ጦር ደግሞ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የመበታተን እጣው ሰፊ ነው:: በሽታ ገብቶም እየጠረገው ነበር:: የሥንቅ አቅርቦቱም ባህያና ባጋሰስ የተጫነ ነው:: ዝቅ ሰፈም በሰው ትከሻ የተንጠለጠለ ነበር:: በዚህ ላይ ከዚያው ግንባር ተበስሎ የሚበላ ነበር:: ከዚህ ውጭ ያለው ደግሞ በየመንደሩ እየተመራ የሕዝብ ቀለብተኛ ሠራዊት ነበር:: እንግዲህ ይህንን ሁሉ ችግር ተቋቁመው ኤርትራን ለማስለቀቅ ቢሞከሩ ኖሮ ያለ ጥርጥር ጣሊያ መልሶ የማጥቃት እድሏ ሰፊ ነበር:: ይህ ከሆነ ደግሞ ኢትዮጵያን ጠቅልላ የመያዝ አጋጣሚው ከሰማይ የወረደ መና ነበር የሚሆንላት:: ይህም ሆኖ ዳግማዊ ምኒልክ ወደፊት ለመግፋት ቆርጠው ተነሥተው ነበር:: የትግራይ መኳንንት በመሟገታቸውና በመቃወማቸው ወደ ፊት ከመግፋት መታቀባቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ:: የሻዕቢያና የሕወሓት ልሂቃን ግን ይህንን ሀቅ ሸምጥጥ አድርገው ከደው ምኒልክን ባገር ሻጭነት በመወንጀል ገልብጠው ያነቡልናል::

ሻዕቢያና ሕወሓት በዚህ ሥልጡን ዘመን ገንጣይ አሥገንጣይ በመሆን በዲፕሎማሲያዊ መንገድ የተቀላቀለችን አገር እንደ ገና በትጥቅ ትግል በኃይል መገንጠላቸውና ማስገንጠላቸው ለዛሬዋ ኢትዮጵያ አንድነት መናጋትም ሆነ ለወደፊቱ ኤርትራ ሕልውና አስጊና የተዳፈነ ረመጥ ነው:: ዛሬ ያንዱን ተቃዋሚ ኃይል ሌላው እየተቀበለ በማስልጠንና መጠጊያ በመሥጠት የሚያደርጉት መሯሯጥና መወነጃጀል ለቁርሾው መከፋት በቂ ማረጋገጫ ነው:: እነሱ ይህን የመሰለ ወራዳ ተግባር እየፈፀሙ አፄ ምኒልክን ፈርመው አገር ሸጡ እያሉ የመወንጀል ምን የሞራል ብቃትና ሀገራዊ ኃላፊነት አላቸው? ሀፍረትን የሚያውቁ ቢሆን ኖሮ ሊያፍሩ በተገባቸው ነበር::

ቀጣይ ትውልድ እነሱን ምን ብሎ ሊጠራቸው እንደሚችል መገመቱ ከባድ አይደለም:: የሕወሓት ተጋዳላዮች ኢትዮጵያን በጎሣ አቧድነው እስበሱ በማፋለም የመጀመሪያዎች እንደ ሆኑ ሁሉ የገዛ አገራቸውንም ተዋግተው በማስገንጠልና ከማንም በፊት እውቅና በመስጠት በዓለም የመጀመሪያዎች ናቸው:: ቢያንስ ኤርትራ ጋራዎች ድረስ ዘልቀው ከኤርትራ





ፋኖዎች ጎን በመሰለፍ የትግራይን ልጆች ለማገዶነት ማቅረብ አልነበረባቸውም:: ደርግን መጥላት ሌላ ነገር ነው:: አገርን ተዋግቶ ማስገንጠልና የባሕር በር ማሣጣት ግን ታሪክ ይቅር የማይለው ወንጀል ነው:: ይህ ሁሉ ሆኖም ከኤርትራ ጋር በመልካም ጉርብትና የምንኖር ቢሆን ኖሮ ወቀሳውንም ሆነ ማስገንጠሉን በፀጋ በተቀበልነው:: ግን አልሆነም:: ሊሆንም አይችልም::

አፄ ምኒልክ ሌላው የሚወቀሱበት በደቡብ፣ በምስራቅና በምእራብ ኢትዮጵያ የግዛት ማስፋፋትን በመንቀፍ ሕይወት ጠፍቷል፣ ንብረት ወድሟል፣ የሚል ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ አገርን ማማከልና ወሰንን ማስፋት በየትም አገር ተከናውኖ አልፏል:: ኢጣሊያንን ለማማከል ገርባልዲ፣ ጀርመንን ቢስማርክ አከናውነውት አልፈዋል:: እንዲህ ሲኮንም ሁሉም ነገር አልጋ ባልጋ ሆኖ አይደለም:: እልህ አስጨራሽ ጦርነቶች ተካሂደውና አካል ጎሎ፣ ንብረት ወድሞ፣ ሕይወት ጠፍቶ እንጂ የመለኮትን ፀበል እየረጩ ያገር ምክልና ተከናውኖ አይታወቅም:: ሩቅ ሣንሄድ አፄ ቴዎድሮስ የከፈሉት የሕይወት ዋጋ በቂ ማረጋገጫ ነው:: ከዚህ አንፃር በዚያን ጊዜ አፄ ምኒልክ የወሰዱት ርምጃ አስፈላጊም፣ ተገቢም፣ ትክክልም ነበር ማለት ይቻላል:: እሳቸው በዚያን ወቅት የያዙትን ይዘው በቸልታ ተቀምጠው ቢሆን ኖሮ እንግሊዝ ምዕራብ ኢትዮጵያን ጋምቤላንና አሶሳን ከሱዳን ጋር፣ ደቡብ ኢትዮጵያን ከኬንያ ጋር ቀላቅላ ለመያዝ የሚሣናት ነገር አልነበረም:: ምሥራቅ ኢትዮጵያንም ቢሆን ከኢጣሊያን ጋር ተከፍላ እንደምትይዝ አይጠረጠርም:: ይህ ቢሆን ኖሮ ደግሞ ዛሬ ሐረሬና ሶማሌ ክልሎች የሚባሉ ባልነበሩ ነበር:: እንዲሁም የባቡሩን መሥመር ተከትሎ አዋሽ ወንዝ መለስ ፈረንሣይ ከጅቡቲ ጋር ቀላቅላ ለመያዝ አላደባችም ነበር ብሎ ዛሬ ማሰብ የዋህነት ነው:: ወቀሳው <በኢትዮጵያ ከምንጠቃለል ቅኝ ገዥዎች በያቅጣጫችን ተቀራምተውን ቢሆን ኖሮ ይሻለን ነበር> የሚል ከሆነ ሌላ ነገር ነው::

በመሠረቱ አፄ ምኒልክ የግዛት ማስፋፋት ሲያካሂዱ ቀድሞ የኢትዮጵያ አካል የነበሩትን እንጂ አዲስ አካባቢዎችን አልጨመሩም:: በመሀከሉ የተበታተነችና ኃይሏ የተዳከመች ኢትዮጵያን ነበር ከቅኝ ገዥዎች እየተከላከሉ ያጠናከሩት:: ይኸነኑ ተከትሎ ኢትዮጵያን በመቶ ዓመት ታሪክ በመከተር <አፄ ምኒልክ ናቸው ጠፍጥፈው የሠሯት> በማለት ያበሻ ቅኝ ገዥ አድርገው በመፈረጅ እኩል ከቅኝ ገዥዎች ጋር ማውገዝና ጥላሸት መቀባት ነው የተፈለገው:: ይህንንም የሚያራግቡት የሻዕቢያና የሕወሓት ከፍተኛ

ያመራር አባላት ናቸው:: ይኸነኑ ተከትለው የኦነግ አባላትም የመገንጠል መርህ ነድፈው ለረጅም ጊዜ መንቀሳቀሣቸውና አፄ ምኒልክን ማውገዛቸው እውነት ነው:: ከዚህ ላይ ግን ሦስት ስንኩል አስገራሚ ነገሮችን አንስቶ ማየት ተገቢ ነው:: እነሱም:-

አንደኛው ስንኩል አስገራሚ ነገር ኢትዮጵያን የመቶ ዓመት ባለታሪክ ብሎ መፈረጅ እብደትም፣ ክህደትም፣ ቅዠትም ነው:: ቀረብ ያለውን እንኳን ትተን ራቅ ያለውን ብንመለከት በ1520 ዓ.ም ግራኝ አሕመድ በማዕከላዊ መንግሥት ላይ አምፆ የተነሣው ከመሀል አጋዴን ነበር:: ይህ የሚያመለክተንም በዚያን ጊዜ እንኳን ኦጋዴን የኢትዮጵያ አካል እንደነበረና የሶማሌ ክልል ሕዝብም ኢትዮጵያዊ መሆኑን ነው የምንረዳው:: በዚያን ጊዜም ያፄ ልብነድንግል መቀመጫ መሐል ሸዋ ዱከም አካባቢ እንደ ነበር በየታሪኩ ተመዝግቦ ይገኛል::

ግራኝ አሕመድ ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ተነስቶ ድል በድል እየተቀዳጀ ትግራይ ጫፍ (ባሕረ ነጋሽን ጨምሮ) ድረስ ዘልቆ ከዚያ ሣያልፍ ወደ ጎንደር ተመልሶ መቀመጫውን ከዚያ ያደረገውም ያለ ምክንያት አልነበረም:: ሱዳን የሌላ አገር በመሆኗ ከወሰን ማለፍ ስላልቻለ ነበር:: በተረፈ ግን ኢትዮጵያ አሁን ካላት ይዞታዋ በቅኝ ገዥዎች ዙሪያውን ተኮርኩማ ጠባ እንደሆነ እንጂ ድሮም የነበረች፤ አሁንም ያለች፤ ወደፊትም የምትኖር ሀገር ነች:: ታሪኳ በመቶ ዓመት ሊጎረድ የቻለውና የባሕር በር ያጣችው "በታላቁ መሪያችንና" በዘመነ ሕወሓት ነው:: ቢያንስ የሦስት ሺ ዘመን ባለታሪክነቷ ቢቀር ግራኝ አሕመድ ያቃጠላቸው አድባራትና ቤተ ክርስቲያናት የ500 ዓመት ዕድሜ ያላት አገር ለመሆኗ ከበቂ በላይ መሥክሮች ናቸው:: ሕወሓት ግን ከቀኝ ወደ ግራ ነው የሚያነብልን::

ሁለተኛው ስንኩል አስገራሚ ነገር ኦነግ ልክ እንደ ሻዕቢያ የመገንጠል መርህ ይዞ በመነሳቱ አፄ ምኒልክን በቅኝ ገዥነት መፈረጁ ትልቅ ስህተት ብቻ ሣይሆን ትልቅ ጥፋትም ነው:: አባቶቹ በስንት መስዋዕትነት የገነቡትን ቤት ካፍራሽ ኃይሎች ጎን ተሠልፎ ለማፍረስ መንቀሳቀሱ ሐሰብ ስንኩል መሆኑን ነው የምንረዳው::

በመጀመሪያ ነገር የኦሮሞ ሕዝብ የሠፈረበት ምድር ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ጀምሮ መሀል ለመሀል ያገሪቱን እንብርት ይዞ እስከ ምዕራብ ኢትዮጵያ ድረስ ነው:: ይህም የመሬት ስፋት ቢያንስ ያገሪቱን ሠፊውን ክፍል የያዘ ነው:: ይህ ከሆነ ታዲያ ኦነግ ለምንድን ነው የመገንጠል መርህ





ይዞ የተነሳው? ብለን ብንጠይቅ መልሱ አንድም ቅዠት ነው፤ አልያም ስንኩልነት ነው:: በመሆኑም የኦሮሞ ልጆችን ኢትዮጵያዊ ስሜት በመገደል የጉም ሥር አስጨብጦ ማከነፍ ነው::

ሦስተኛው ስንኩል አስገራሚ ነገር ቀደም ሲል የምናውቀውና የተለመደው በቁጥር አናሳ የሆነው ሕዝብ በብዙሃኑ ተጨቁኛለሁ ባለ ጊዜ የመገንጠል ጥያቄ ሊያነሣ የሚችል መሆኑን ነበር:: የኦሮሞ ሕዝብ ግን በቁጥር ከሁሉም ይልቃል:: ይህ ከሆነ ታዲያ ኦነግ የቱን ይዞ፣ የቱንስ ትቶ ነው የሚገነጠለው? ከውቅያኖስ ወጥቶ ከኩሬ ውስጥ ለመንቦጫረቅ? ይህም ማፈሪያነትና ስንኩልነት ነው::

በመሠረቱ በወረቀት ላይ ካርታ ሠርቶ <ይህ የኔ ክልል ነው> ማለት ይቻላል:: የመገንጠል መርህ ይዞ ወደ መሬት ሲመጡት ግን እንደ ወረቀት ላይ ካርታው ቀላል አይሆንም:: መዘዙ ብዙ ነው:: ለኦሮሞ ሕዝብ ጠላት ማብዛት ነው:: የዚህ ውጤት ደግሞ ተያይዞ መውደቅ ነው:: መልሱ እንደ ሰው እናስብ፤ ልንሸከም የምንችለውን ኃላፊነት እንመዝን ነው::

ኦነግ በውስጡ አብረውት ለረጅም ጊዜ የኖሩትን የሕብረተሰብ ክፍሎችን <ከክልሌ ውጡ> ብሎ ከማወክ ይልቅ አቅፎ በመያዝ ጊዜው በሚጠይቀው የምርጫ ካርድ ተጠቅሞ በድምጽ ብልጫ ሥልጣን መያዝ ይችል ነበር:: ርግጥ ነው <ነፃ ምርጫ በኢትዮጵያ አለ ውይ?> የሚል ጥያቄን ሊያስነሳ ይችላል:: መልሱ ይቻላል ነው:: ካልተቻለ ደግሞ ትግሉን በዚህ ዙሪያ ማድረግ ይቻል ነበር:: ኦነግ ያደረገው ግን ኢሕአዴግ ባጠመደለት ወጥመድ እንደሞኝ አውሬ ሰተት ብሎ በመግባት ንፁሐን ዜጎችን በገመድ እያነቀ በገደል በመጣሉ ኢሕአዴግ ከተጣሉበት ገደል አስከሬናቸውን እያወጣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በቴሌቪዥን በማሣየት ርቃኑን ካስቀረው በኋላ <ባሸባሪነት> ወንጀሎ ስሙንም እስከ መጨረሻው ድረስ አጥቁሮ ከሽግግር መንግሥቱ ገፍትሮ አባረረው:: በርግጥም በወቅቱ ከዚህ የበለጠ ሽብር ሊኖር አይችልም:: ኦነግ በጊዜው አስከፊና አሣፋሪ ጥፋት በወገኖቹ ላይ ፈፅሟል:: ንፁሐን ዜጎችን በገመድ እያነቀ ወደ ገደል መጣሉ ከፉ የታሪክ ቁስል ነው ለኦሮሞ ሕዝብ ያስቀመጠው:: ርግጥ ነው ሁሉንም ጥፋቶች እሱ ብቻውን እንዳልፈፀማቸው ሕዝብ ጠንቅቆ ያውቃል:: በስሙ ግን ብዙ ሥራዎች ሠርተውበታል::

ኦነግ የሌሎቹን ብሔር ሕይወት ማጥፋቱ ብቻ ሣይሆን ብዙ የኦሮሞ ልጆችን ሕይወት ጭምር አጠውልጓል:: በሞት፣ በሥራት፣ በስደት እንዲንገላቱ ምክንያት ሆኗል:: በወቅቱ በስሜት ፈረስ ይጋልብ ስለነበር

እሱን አምነው የተጠጉ ሁሉ ዛሬም ድረስ አበሣው አለቀቃቸውም:: ገና ከጧቱ <በአሸባሪነት> ተፈርጇልና::

አፄ ምኒልክ ሌላው የሚወገዙበት ይኸነኑ አገርን የማስፋፋት ሂደት ተከትሎ <ጡት ቆረጡ፣ ብልት ሰለቡ!> እየተባሉ መከሰሳቸው ነው:: መቸስ ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ግዛትን ለማማከልና ለማስፋት ሲታሰብ ሁሉም ነገር በቀናነት ይከናወናል ብሎ ማሰብ አይቻልም:: ጡትም ተቆርጦ፣ ብልትም ተሰልቦ ይሆናል:: በዚህ ሙግት ውስጥ አንገባም:: የሚያሟግተን ግን አንድ ሀቅ አለ:: <ጡት ቆረጠ፣ ብልት ሰለቦ> እየተባለ የሚወገዘው <ነፍጠኛ> እየተባለ የሚጠራው ሠራዊት ነው:: ይ ሠራዊት ደግሞ በጅምላ አማራ ነው ተብሎ ተፈርጇል:: እውነት ያፄ ሚኒልክ ሠራዊት አማራ ብቻ ነበር? ተራውን ወታደር እንተወውና የሠራዊቱን መሪዎች ብንመለከት እንኳን ራስ ጎበና፣ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፣ ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶን መጥቀሱ ብቻ በቂ ነው:: ለነገሩ ስመ ጥሩው ራስ ጎበናም <ጎበና> እየተባሉ በገዛ ስማቸው ተወግዘዋል:: የሚገርመው ታዲያ ዛሬ ከኢሕአዴግ ጋር ተሠልፈው የኦሮሞን ሕዝብ የሚያተራምሱትን የኦሕዴድን አባላት የኋለኛው ትውልድ ምን ዓይነት ስም ያወጣላቸው ይሆን? በኔ እምነት ላዔ ቴዎድሮስ ፊታውራሪ ገብርዬ፣ ላዔ ዮሐንስ ራስ አሉላ፣ ላዔ ምኒልክ ራስ ጎበና የብረት አለሎ በመሆን በዚች አገር የፖለቲካ ሕይወት ከነገሥታቱ ባላነሰ መልኩ የጎላ ተፅዕኖ እንደነበራቸውና ይህንንም ተከትሎ በሕዝብ ዘንድ ዛሬም ድረስ ተከባሪዎችና ተፈቃሪዎች መሆናቸው በቂ ምስክር ነው::

እንግዲህ ከፍ ብዬ ለመጠቆም እንደሞከርኩት የምኒልክ ሠራዊት አማራ ብቻ ነበር ብለን የምናስብ ከሆነ እጅግ ተሣሥተናል:: የምኒልክ ጦር አማራ ብቻ ነበር ብለን የምናምን ከሆነም፤ እንደሚታወቀው ያማራ ሕዝብ በባህሉም፣ በወጉም፣ በታሪኩም ጡት የመቁረጥና ብልት የመስለብ ልማድ ወይንም ወግ የለውም:: ርግጥ ነው መሪዎቹን ተከትሎ ተዋጊና ጦረኛ መሆኑ እውነት ነው:: ይህንን የሚክድ ዜጋ አይኖርም:: ዳሩ ግን በታሪኩም፣ በባህሉም የሌለ ተቀፅላና አስከፊ ስም የተሰጠው በዚህ የጎሳ ሥርዓት በመሆኑ ሁኔታውን አሣዛኝ ያደርገዋል::

ራቅ ባሉት ዘመናት የትኞቹ የሕብረተሰብ ክፍሎች ነበሩ በባህላቸው፣ በወጋቸው፣ ለዝናና ለጅግንነት ሲሉ ብልት በመስለብ ግዳይ ይጥሉ የነበሩት? ብለን ብንጠይቅ ለመልሱ አንቸገርም:: ዛሬ ታዲያ ይህን መሣይ ድርጊት የሚፈፅሙ የማህበረሰብ ክፍሎች በሌሉበት ሥልጡን ዘመን <የምኒልክ





ሠራዊት ጡት ቆርጧል፣ ብልት ሰልቧል!> እያልን ማውገዙ ቂምና በቀልን ተክሎ ለማለፍ ካልሆነ በስተቀር ለዚህ ትውልድ የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው? የሌለ ታሪክ ፈጥሮ ጥላሸት መቀባቱስ ማንን ይጠቅማል? ጠይቁ::

በመሠረቱ ጥፋትና ጉዳት አልደረሰም ብሎ የሚከራከርም የለም:: የብሔር ጭቆናም አልነበረም ብሎ መካድም አይቻልም:: ግን ደግሞ ጉዳቱም፣ ጭቆናውም ያንዲት አገር ሕዝብ እንጂ አንድን ብሔረሰብ ብቻ ነጥሎ ከፋት ተሸካሚ ለማድረግ የሚደረገው የቅጥፈት ሩጫ በጎ ሥንቅ አይኖረውም:: እውነትነት ስለሌለው የጉም ሥር እንደ መጨበጥ ይቆጠራል:: ይህም ሆኖ አስተማሪና ችግር የሚቀርፍ ቢሆን ኖሮ ወቀሣውን ለመቀበል ወይንም ለመሸከም ባልከበደ ነበር:: ከፋቱ በበቀልተኘነት ስሜት ነጥሎ ጥላሸት ከመቀባቱ ላይ ነው:: እንዲህ አይነቱ ስንኩል አስተሳሰብም ሌላ የከፋ በቀልንና ጥላቻን ያስቋጥር እንደ ሆነ እንጂ የአእምሮ ቆሻሻን በፍፁም አያፀዳም:: በተጨባጭ የዚህ የዚያ ብሔረሰብ ሣይባል አጥፊን በጥፋቱ ማጋለጥ ሲቻል ብቻ ነው በፀፀት አንገት መድፋት የሚቻለው:: ከዚህ ውጭ ግን አንድን ሕዝብ በጅምላ መጥላትና ማውገዝ ከፉ የደም በሽታ ነው::

ሌላው ስላፄ ምኒልክ ሠራዊት ሲነሳ ፈጥኖ ወደ አእምሯቸውን ውስጥ የሚመጣው <ነፍጠኛ> የሚለው ምስል ነው::

<ነፍጠኛ> ማለት ባጭሩ ጠመንጃ አንጋች ማለት ነው:: ይህነኑ ቃል አለቃ ደስታ ተክለወልድ <አዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት> በተባለው መጽሐፋቸው "ነፍጥ፤ በያይነቱ ጠመንጃ፣ ጠላትን የሚያሸብር፣ የሚያሸሸ" ብለውታል:: እንግዲህ ስለፍቸው ይህን ያህል ካልን ታሪካዊ አመጣጡን ደግሞ ቀጥለን እንመልከት:-

<ነፍጥ> የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተደመጠው ከዛሬ 500 ዓመታት በፊት በግራኝ አሕመድ ወረራ ወቅት እንደነበር አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: በዚያን ወቅት ቱርኮች ለግራኝ በድምፁ ብቻ እየተተኮሰ የባላንጣን ጦር የሚያሸብር ሞርተር መሠል መሣሪያ አስታጥቀውት እንደነበር ይነገራል:: የዚህ መሣሪያ ተግባር እየተተኮሰ በድምፁ ብቻ ማሸበር እንጂ ርሳስ ኖሮት ተወርውሮ ዒላማ የሚመታ አልነበረም:: ሁኔታውን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ያህል ባሩድ ብቻ ተሞልቶ ዛሬ በባዕላት ቀናት እንደሚተኮሰው መድፍ ማለት ነው:: እንግዲህ ያፄ ምኒልክ ሠራዊት <ነፍጠኛ> ተብሎ የተሰየመው የጦር መሣሪያ የታጠቀ፣ ያነገተ፣ የተሸከመ

ለማለት ይመስላል። የወቅቱ የጦር መሣሪያም ሲናድር፣ ናስማስር፣ ውጅግራ ሲሆኑ አንድ ጎረስ ነበሩ። ያም ሆኖ ምንም ዓይነት የጦር መሣሪያ የሌለው ሕዝብ <ነፍጥ የታጠቀ ሠራዊት ወረረን> ቢል አያስገርምም። የሚያስገርመው የሚኒልክ ሠራዊት አንድ ባንድ ተኳሽ ጠመንጃ ያነገተው <ነፍጠኛ> ከተባለና ይህንንም ተከትሎ አማራ ብቻ የታሪክ እዳ እንዲከፍልና እንዲሸከም ከተጠየቀ ዛሬ ከሰላሳ ጎራሽ ከላሽንኮቭ ጀምሮ እጅግ የተራቀቁ ዘመናዊ የጦር ጀቶች ድረስ እስከ አፍንጫው የታጠቀውንና ከሙቶ ያላነሱ ጄኔራሎች ባንድ ጎሣ ብቻ የሚመራውን የኢሕአዴግን ሠራዊት ቀጣይ ትውልድ ምን ብሎ ሊጠራው ነው? <ነፍጠኛ!> የሚለው ስያሜስ ይመጥነዋል? ነው ቁናውን በቁና መሠፈር እንዲሉ እሱም በተራው <የትግሬ ነፍጠኛ> እየተባለ በታሪክ እንዲጠራ ፈልጎ? የዚህ እዳስ በቀላሉ ተከፍሎ የሚያልቅ ይሆናል?

ገዥው ፓርቲ የሥልጣን እድሜውን ለማራዘም ሲል እያራገበ ያለው የጎሳ ፖለቲካ የኋላ ኋላ መዘዙ ብዙ ነው። ላገር አንድነትና ለሕዝቦች ደህንነት አይጠቅምም፤ ጠንቅ ነው። ታመነም አልታመነ ሕወሓት በተራው ለትግረኛ ተናጋሪ ወገኖቻችን ጠንቅ እየተከለላቸው መሆኑ በግልፅ መታወቅ አለበት።

<የነፍጠኛው ሥርዓት> እያሉ በማውገዝ ባንፃሩ ግን በዚህ ሥልጡን ዘመን ከሥልጣን ላይ ተጣብቆ ለመቆየት ሲባል ዜጎች ባነጣጥሮ ተኳሾች ግንባር ግንባራቸውን እየተመቱ የሚወድቁ ወጣቶች ለነገ መጥፎ ሥንቅ ነው። (የ1997 ዓ.ምንና 1998 ዓ.ም ያስታውሷል) ላገርና ለወገን የሚጠቅመው ያለፉ ቁስሎችን እንዲሽሩ ተቀራርቦ በመወያየት ብሔራዊ ርቅ ማውረድ ሲቻል ብቻ ነው። ሁላችንም የዚች አገር ባለድርሻዎች መሆናችንን አውቀን የድርሻችንን ለመወጣት ፈጣሪ ቅን ልቦና ይሠጠን ቀጥለን ደግሞ ቀ.ኃ.ሥ የሚወቀሱበትን እንመልከት።

<><><>





# አፄ ኃ/ሥላሴ



አፄ ኃ/ሥላሴ

አፄ ኃይለ ሥላሴ በቆዩባቸው ረጅም የሥልጣን ዘመናቸው ላገራቸው ዕድገት በርካታና ቀላል የማይባሉ ተግባራትን አከናውነዋል። ካከናወኗቸው መሀከል ጥቂቶቹ:-

1. *ኤርትራን አንዲት ጥይት ሳያጮሁ በዲፕሎማሲያዊ መሥክ ተጠቅመው ከናት አገሯ እንድትቀላቀል አድርገዋል።*
2. *ኢ.አ.ድ.ን ከመሠረቱት ያፍሪካ መሪዎች አንዱ ከመሆናቸውም በላይ ዋና ጽ/ቤቱ አዲስ አበባ እንዲሆን አድርገዋል።*



አፄ ኃ/ሥላሴ

3. *አፄ ምኒልክ የጀመሩትን የዘመናዊ ት/ቤት ማስፋፋት ተግባር አጠናከረው ገፍተውበታል። በዘመናቸውም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ከፍተዋል።*

ባጭሩ ደርግ አሥራ ሰባት ዓመታት እንዳብጠለጠላቸው ያሉ ንጉሥ አልነበሩም። ላገራቸው እድገት የሚችሉትን ሁሉ አድርገዋል። በዘመናቸውም <ፀሐዩ ንጉሥ> እስከ መባል የደረሱ ነበሩ። ያለመታደል ጉዳይ ሆኖ ግን "እድሜና ገመድ ሲረዝም የሚጠልፈው ነገር አያጣምና" እድሚያቸውም፣ ሥልጣን ላይ የቆዩበት ጊዜም በመርዘሙ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም እጅ ላይ ወደቁና አሟሟታቸው ከፋ።

ቀ.ኃ.ሥ ላገራቸው ብዙ በጎ ነገሮችን ያከናወኑትን ያህል በርካታ የሚነቀፉባቸውም ነገሮች መኖራቸው እውነት ነው። ከሚነቀፉባቸው መሀከል አንዱና ዋናው ሥልጣን እያያዛቸው በመፈንቅለ መንግሥት በመሆኑ ምክንያት ያሥተዳደር መዋቅራቸው እስከመጨረሻው ድረስ በጥርጣሬና በሤራ የተተበተበ እንደነበር በሰፊት ይነገራል። ሥልጣናቸውን በማጠናከር ትኩረት በመሥጠት ሙሉ ጊዜያቸውን በዚህ ላይ እውለው ሣለ ኢጣሊያ በ1928 ዓ.ም ወረራ በመከፈቷ

ያኔ እንደ ምኒልክ በደል ሣይወጡ በመቅረታቸውና ሽንፈት ሲመጣም ጦራቸውን ማይጨው ላይ ፀትነው ወደ አውሮፓ መሰደዳቸው ለሳቸውም የሕሊና ቁስል ላገራቸውም ሀፍረትን ያከናነበ ነበር።

አፄ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ የሽገጥ ጥይት የጠጡላት፣ አፄ ዮሐንስ መተማ ላይ አንገታቸውን የሰጡላት፣ አፄ ምኒልክ አድዋ ተራሮች ላይ ድልን ያጎናፀፏት አገር የቀ.ኃ.ሥ ወደ አውሮፓ በዚያን ወቅት መሠደድ እንግዳ ነገር ስለነበር በእጅጉ አንገትን አስደፍቷል። በዚህ ምክንያትም እድሜቸውን ሙሉ የሕሊና ረፍት ማጣታቸውና ከኋለኛው ትውልድ ጋር ያፋጠጣቸው ይኸው የሽሽታቸው መዘዝ እንደነበር በሰፊት የሚነገርና የሚታወቅ ነው።

ሌላው የሚወቀሱበትና የሚነቀፉበት ይህነኑ ሽሽታቸውን ተከትሎ ከሥደት ተመልሰው ካርቱም በቆዩባቸው ወራት ያሳሰባቸውና ያስጨንቃቸው የነበረው ካርበኞች ጋር እንዴት ተጣጥመው በሥልጣን ላይ መቆየት እንደሚችሉ ነበር። በርግጥም ካርቱም የመግባታቸው ዜና ባገር ውስጥ እንደተሰማ ባርበኞች በኩል የወቅቱ መፈክር፦





"ያፈረሰ ቄስ አይቀድስ፣ የሸሸ ንጉሥ ተመልሶ አይነግሥ!" የሚል ነበር። በመሆኑም ንጉሠ ነገሥቱ ያርበኞችን የኃይል ሚዛን ለመጠበቅ ሲሉ ራሳቸውን ከስደተኞች ጎን በማሰለፍ ለባንዳዎች የመጀመሪያውን የምሕረት አዋጅ ያወጁት ጎጃም ጠረፍ (አሜድላ) ላይ እንደ ደረሱ ነበር። የምሕረቱ ቃል የሚከተለው ነበር፦

*". . .በግድም፣ በውድም ቢሆን ከዚህ ቀደም ከኢጣሊያኖች ውስጥ ወይንም ውጭ ሁነህ አገርህንና ንጉሠ ነገሥትህን የበደለህ ሁሉ ባለፈው ጥፋትህ ምሬሃለሁና ዘርህን ለማጥፋት፣ ርስትህን ለመንቀል፣ ስምህን ለመደመሰስ፣ ደምህን ለማርከስ ቆርጠ በመጣው ጠላታችን ላይ ከዳር እስከዳር ክንድህን አንሳ! . . ."* የሚል ነበር። *(ጎንደሬ በጋሻው ገጽ 257)*

የወቅቱ የኃይል አሰላለፍም የሚከተለው ነበር፦

1. *አርበኞች አምስት ዓመት ሙሉ በዱር በገደሉ ይባክኑ የነበሩ።*
2. *ስደተኞች አምስት ዓመት ሙሉ በስደት የቆዩ (ንጉሠነገሥቱን ጨምሮ)*
3. *ባንዳዎች አምስት ዓመት ሙሉ ለጠላት ሁለንተናዊ አገልግሎት የሰጡ ነበሩ።*

እንግዲህ ንጉሠ ነገሥቱ የወሰዱት ርምጃ ስደተኞችንና ባንዳዎችን አቅፈው በመያዝ አርበኞችን መግለፅ ነበር።

በመሠረቱ ለባንዳዎች ምህረት በመሥጠታቸው አይነቀፉም። የሚነቀፉት ራሳቸውን ሥልጣን ላይ ለማቆየት ሲሉ ጅምላ ምህረት በመሥጠታቸው እጅግ የከፋ ጥፋት ባገርና በወገን ላይ ያደረሱ ባንዳዎች የምህረቱ ተጠቃሚዎች በመሆናቸው ባምስት ዓመቱ ያርበኝነት ወቅት ከፈፀሙት ጥፋት እጅግ በላቀ መልኩ ከነፃነት በኋላ ባርበኞች ላይ በደል በመፈፀማቸው ለንጉሡም ሥልጣን ውስጥ ውስጡን ለመቦርቦርም ሆነ ላገሪቱም ውድቀት፣ ለዘውድም ማክተም እንደ ዋና ምክንያት ሆኗል። ዛሬም የባንዳና የብልቁባሽ ልጆችና የልጅ ልጆች አገሪቱን እያመሷት ይገኛሉ። ባንፃሩ ያርበኞች ልጆችና የልጅ ልጆች እንደ ዔሊ አንገታቸውን ቀብረው ይገኛሉ። ወይንም አገር ጥለው ተሠደዋል።

ንጉሠ ነገሥቱ ጠላት ተወግዶ ሥልጣናቸውን ሲያደላድሉ የቢሮክራሲውን ሥራና ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ለባንዳዎችና ለስደተኞች በመሥጠታቸው ያርበኞች እጣ ፈንታ ለባንዳዎችና ለሥደተኞች ማጎብደድ

ነበር፡፡ እንደ በላይ ዘለቀና እንደ ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሀዋርያት ያሉ ስመጥር አርበኞች ለባንዳዎች ለማጎብደድ የጎፈነናቸው በጥይትና በስቅላት ተቀጥተዋል፡፡ የቀሩትንም በረጅም የግዞት ዘመናቸው እንደ ዘመኑ የኤድስ በሽታ አንድ ባንድ አመንምነው ፈጅተዋቸዋል፡፡ አንዳንዶችም እድሜቸውን ሙሉ በደጅ ጥናት ጎብጠው ለቁምነገር ሣይበቁ ለእልፈት በቅተዋል፡፡

የግርማዊነታቸውን ልዩ ባህልና የሥልጣን ሥሱነት በተመለከተ ለረጅም ጊዜ በቅርብ የሚያውቋቸው ስፔንሰር እንዲህ ይሏቸዋል፡-

*"ኃይለ ሥላሴን በግልና በሥራ ላውቃቸው እድል ነበረኝ፡፡ . . . መንታ ባህሪ የነበራቸው ሰው ነበሩ፡፡ ደፋር፣ ፈሪ፣ መሠሪ፣ አምነት የማይጣልባቸው፣ ምህረት የለሽ፣ ራስ ወዳድ፣ ንፉግ፣ ታይታ የሚወዱ፣ ባንፃሩ ጨዋ ሰው የሚፈለገውን እንዲወስድ የሚፈቅዱ ነበሩ . . ."* በማለት ይገልፅዋቸዋል፡፡ *(ጥርስ የገባች ሀገር ገጽ 188)*

ሌላው ምሁርና አርበኛ ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ <ሸክም የማይከብደው ሕዝብ> በተባለው መጽሐፋቸው በገጽ 101 ላይ *". . .ንጉሡ ከስደት ተመልሰው ሥልጣን ከያዙ በኋላ በስደተኞችና በባንዳዎች እየተመሩ <የምንወደውና የሚወደን ሕዝባችን> በሚል ቃል አርበኞችን በባዶ ተስፋ እየመገቡ ተመናምነው እንዲያልቁ አድርገዋል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት አርበኞች ከሥልጣኔ ያወርዱኛል ብለው በመሥጋት ሲሆን ሌላው ላገራቸው ከሳቸው የተሻለ ታሪክ አርበኞች ስለሠሩ ላርበኝነት የሚገባቸውን ክብር ላለመሥጠት ነበር፡፡ ንጉሡ ከሳቸው ሌላ የታሪክ ተሻሚ እንዲኖር የማይፈልጉ ቀናተኛ ስለነበሩ ነው . . ."* ብለዋቸዋል፡፡

እንግዲህ ግርማዊነታቸው ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ተጠራጣሪና ሰውን የማያምኑ፣ ይበልጠውንም ካርበኞች ጋር እሳትና ጭድ በመሆናቸው መጨረሻቸውም፣ አሟሟታቸውም ሣያምር ቀረ፡፡ ለነገሩ ንጉሠ ነገሥቱ የጃቸውን ነበር ያገኙት፡፡ ልጅ ኢያሱን ወደ ማይጨው ሲዘምቱ አስቆልምመው እንዳስገደሏቸው ይነገራል፡፡ የንግሠተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ አሟሟትም ቢሆን እስካሁን ድረስ እንቆቅልሽ ነው፡፡ በወቅቱ ሕዝቡ በሥነ ቃል፡-

*"አቴ ምኒልክ ድመት ነው ርማቸው፣ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን ሐነር ገደላቸው!"* ተብሏል፡፡





ያልታደሉ ንጉሥ በመጨረሻም ከደርግ ላይ ጥሏቸው አሟሟታቸ የከፋውን ያህል ከ17 ዓመት በኋላ ደግሞ ከኢሕአዴግ እጅ ላይ አፅማቸው ወድቆ ጥቀርሻ ቀባቸው፡፡ ቅብብሎሹ የሚያሣዝንም ነው፡፡ ዛሬ ግን ባቶ መለስ ሙት መንፈስ አገር እየታመሰች የበቀል ሐውልቶች እየተገነቡልን ነው፡፡

<>

# ክፍል አራት

*"ወንድም ወንድሙን እየገደለ ሐውልት የሚያቆምበት ዘመን እንዲያበቃ ያቅሜን አስተዋፅኦ አድርጌአለሁ! በዚህም አልቆጭበትም!"*

ናትናኤል መኮንን
ፍ/ቤት የፍርድ ማቅለያ ሐሳብ በጠየቀው ጊዜ የሰጠው ቃል ነው፡፡

# የበቀል ማስታወሻ ሐውልቶች!

ኢሕአዴግ ሕዝብን ከሕዝብ ወይንም ብሔርን ከብሔረሰብ ለማናከስ ከሚጠቀምባቸው ስልቶች መሀከል አንዱና ዋናው የበቀል ማስጨበጫ ሐውልቶችን እየቀረፀ በየቦታው ማቆም ነው፡፡


ቀደምት ነገሥታት የሠሯቸው ሐውልቶች ከውጭ ወራሪዎች ጋር የተደረጉ ትንቅንቆችን ቀጣይ ትውልድ እንዲዘከራቸው ለማድረግ የወል ምስሎችን አቆሙልን እንጂ ቂምና በቀልን እንድናስታውስና አንዱ ብሔረሰብ በሌላው ብሔረሰብ ላይ ጣቱን እንዲቀስርና ጥርሱን እንዲነክስ አልተከሉልንም፡፡ ወይንም የበቀል ሥንቅ አቁመው አላቆዩንም፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን ያድዋ ድል መታሰቢያ ሐውልት (አራዳ ጊዮርጊስ አጠገብ ያለው የዳግማዊ አጼ ምኒልክ)፣ የስድስት ኪሎው የሰማእታት ሐውልት፣ አራት ኪሎ ያለው የድል መታሰቢያ ሐውልት፣ የብፁእ አቡነ ጴጥሮስ የሰማእትነት መታሰቢያ ሐውልት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህ ሐውልቶች እንደቆሙለት ዓላማና ተልዕኮ የሚነግሩን ምስጢር አላቸው፡፡ እንደ መረዳት አቅማችንና ግንዛቤችን መልእክቶቹን እንጨብጣለን፡፡








*የብፁእ አቡነ ጴጥሮስ የሰማእትነት መታሰቢያ ሐውልት*




*የ6 ኪሎው የሰማዕታት ሐውልት*



የብፁእ አቡነ ጴጥሮስ የሰማእትነት መታሰቢያ ሐውልት




የ6 ኪሎው የሰማዕታት ሐውልት

ኢሕአዴግ በየቦታው ያቆመልን ሐውልቶች ግን የሚያስተላልፉልን መልዕክትና የሚነግሩን ምስጢር የመቅደላን (የእንግሊዞችን ወረራ)፣ የመተማመን (የመሐዲስቶችን ወይንም የድርቡሾችን ፍልሚያ)፣ ያድዋን፣ (የኢጣሊያንን ጦርነት)፣ ወይንም የትናንቱን የ69 ዓ.ም የሶማሊያን የግፍ ወረራ እንድናስታውስ የሚነግሩን ሐውልቶች አይደሉም:: አንዱ ብሔረሰብ በሌላው ወገኑ በሆነው ብሔረሰብ ላይ በቀል ጨብጦ፣ ከፋት አርግዞ፣ ቂም ሰንቆ አመች ጊዜና ቦታ ጠብቆ እንዲበቀልና የከፋ ጥፋት እንዲፈፅም ታልመው የቆሙ ሐውልቶች ናቸው::

የሚገርመው ደግሞ "ፍየል ከመድረስ ቅጠል መቆንጠሷ" እንዲሉ ሕወሓት/ኢሕአዴግ በ84 ዓ.ም የዳግማዊ አፄ ምኒልክ ሐውልት መፍረስ አለበት ብሎ ባዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ ኦሮሞ ወገኖቻችንን መስቀል አደባባይ አሰልፎ ሲያስጮህ ውሎ በማግስቱ ደግሞ አቶ መሥፍን ኢያሱ በተባሉ ግለሰብ አማካኝነት ይፍረስ የተባለው ሐውልት ከፍተኛ ወጭ ተመድቦለት በነሐስ ቀለም እንዲታደስ አድርጓል:: ይህንን ድርጊት ስናስተውል ሕወሓት ምን ያህል ሠብቀኛና ቁማርተኛ የፖለቲካ ድርጅት መሆኑን ነው:: የዚህ ዓላማና ተልዕኮ ግልጽ ነው:: ኦሮሞ አፈርሳለሁ ሲል ሌላው ዜጋ <አታፈርስም> በሚል ደም ለማፋሰስ ነበር:: ግን እንዳሰበው አልሆነለትም:: ጅጅጋ ላይም የዕውቁን አርበኛ የደጃዝማች አፈወርቅ ወ/ሰማዕትን የመታሰቢያ ሐውልት በዘመኑ አሥፈርሷል:: በመሠረቱ ደጃዝማች አፈወርቅ ከኢጣሊያን ጋር ኦጋዴን ላይ ተናንቀው የተሰው ጀግና እንጂ የሶማሌ ዜጎቻችን በግፍ የረሸኑና ያሰቃዩ አልነበሩም:: ዓላማው እስካሁን እንደ ተገለፀው የዚችን ሀገር የቁርጥ ቀን ልጆችና የልጅ ልጆች አንገታቸውን እንዲደፉና ተሸማቀው እንዲኖሩ ቅስማቸውን ለመሥበር ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲታይና ሲታሰብ የጠላት ተልዕኮም ያለበት ይመስላል::

በመሠረቱ እንዲህ ለምን ሆነ? ወደ የትስ እየሄድን ነው? መጨረሻችንስ ምን ሊሆን ነው? ብለን ብንጠይቅ መልሳችን አስፈሪ ነው:: ምናልባትም ላንዳንዶቻችን ከረመጥ ላይ ጭድ ጎዝጉዘን የተቀመጥን ያህል ሊሰማን ይችል ይሆናል:: ወይንም ደግሞ ከቤንዚን ላይ ክብሪት ጭረን የለኮስን ያህል ሊሰቀጥጠን ይችላል:: ይህ እውነት ነው:: ዞሮ ዞሮ ግን የዚህ ሁሉ መዘዙ ጎሰኝነት መሆኑን ልብ ልንል ይገባናል::

የጎሰኝነት ከፋቱ የኔ ከሚላቸው ውጭ ያሉትን የማኅበረሰብ ስብስቦች በጅምላ መጥላቱ ነው:: ይህ ደግሞ ከፉ የጭንቅላት ካንሠር ነው:: ወይ ራስን ወዶ በራስ ላይ እንዳይደረግ የማይፈለግን ከፉ ነገር በሌሎች ላይ






እንዳይደረግ አለመፍቀድ ጨዋነት ነበር:: ይህ ግን የመሪዎቻችን መርህም የመዳረሻ ግብም አይደለም:: ምናልባትም በዚህ ሁኔታ የምንቀጥል ከሆነ ኑሯችን እንደ ፍልፈል ከመሬት ውስጥ አፈር ወደ ላይ እየገፉን ይሆናል፤ ወይንም እንደ ሌሊት ወፎች በጨለማ ውስጥ የምንከንፍ ፍጡሮች እንሆናለን::

የጎሰኝነት የጥላቻ መንስዔው የበታችነት ስሜት የሚፈጥረው የስነ ልቦና ቀውስ ስለመሆኑ የመስኩ ባለሙያዎች ይናገራሉ:: በዚህ ምክንያትም ጎሰኞች ጀግኖችን ፈርተው ይጠላሉ:: ሙተው እንኳን ባፅማቸውና በሙት መንፈሳቸው ይሸበራሉ:: ከነተረቱ እንኳን <አባክህ ጌታየ ሙት ውቃሽ አታድርገኝ> ነበር:: በዚህ ዘመን ግን ተገልብጦ ሙት ቀስቃሽ ሆኗል:: ለዚህም ነው ጎሰኞች የጀግኖችን ገድል ከታሪክ ማህደር እስከ መፋቅ ድረስ የሚራመዱት:: የደጃዝማች አፈወርቅ ወ/ሰማዕትን ሐውልትም እስከ ማፍረስ ድረስ የተጓዙት ከዚህ አንፃር ነው::

ኢጣሊያ በ1928 ዓ.ም ዳግም አገራችንን ወራ በድል አድራጊነት ላምስት ዓመታት ተቆጣጥራን በነበረበት ወቅት ከወሰደቻቸው እስከፊ ርምጃዎች መሀከል ባድዋው ዘመቻ ጊዜ የተፋለሙትንና ያፋለሙትን ጀግኖች ልጆችና የልጅ ልጆችን እንዲሁም የነዚህን ዘሮች እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ እንደ ዱር አውሬ እያደነች አጥፍታቸዋለች:: ይህንን እስከፊ ርምጃ ስትወስድም በውስጥ አወቅ ባንዳዎችና ብልቁባሾች ጠቋሚነት ነበር:: ዛሬም ሕወሓት እየሠራ ያለው ሥራ ሲጤን ከኢጣሊያን ቀጥታ የተቀዳ ይመስላል:: የስመጥር አርበኞችን ልጆችንና የልጅ ልጆችን የተለያዩ አሸማቃቂ ስሞችን በመለጠፍ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ወደ ባዕዳን አገራት እንዲሰደዱ ማድረግ ነው:: ከዚህ ሲከፋም ቁርሾን ለትውልድ የሚያቆዩ ሐውልቶችን ማቆምና የሾቀ ትውልድ እንዲፈለፈል ምቹ ሁኔታን መፍጠር ነው::

ሕወሓት/ኢሕአዴግ በየቦታው ያቆመልን ወይንም የተከለልን ሐውልቶችም ዛሬን ብቻ ሣይሆን ቀደም ሲል እንደ ገለፅኩት ቀጣይ ትውልድ ቂምና በቀልን አርግዞ እንዲኖርና አንዱ ብሔር የሌላው ደመኛና ጠላት እንደሆነ በማስመሰል በቀልን እየተከለልን ነው:: ለምሳሌ ኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ ምእራብ ዳርቻ ከፈፋው ላይ የቆመውን ሐውልት አትኩረን ስንመለከተው ከንጣቱና ከቅርፁ አንፃር የሰው ቅልጥም አምሳያ ነው ማለት ይቻላል:: ይህንን ቅልጥምም ያፈሰሱት ያፄ ምኒልክ ነፍጠኞች ናቸው እንደሚባል አይጠረጠርም:: ይህነን ነው እንግዲህ ኦሕዴድ /ኢሕአዴግ ለቀጣይ የኦሮሞ ልጆች የሚያቆያቸው የጥበብ ቅርስ፤ ይህም ሆኖ

የኦሮሞ ልጆች በዘመነ ኢሕአዴግ መብታቸውን ተጎናፅፈው ከሆነና ካልተንገላቱ፣ ካልታሠሩ፣ ካልተገረፉና ካልተሰደዱ <የነፍጠኛውን ሥርዓት> የሚባለውን በረጋጭነቱ የሚያስታውሱበት አንድ ነጭ ሐውልት ብቻ ሣይሆን አሥር ቢሠራላቸው አግባብ ነው ማለት በተቻለ ነበር፡፡ አሁንም የመብት ረገጣው ከዚያ ኋላቀር ሥርዓት የባሰ ከሆነና ግፉ ከቀጠለ ግን ቀጣይ ትውልድ ነጩን ሐውልት ነቅሎ <ጨለማ ሕይወት ነበር የገፋነው> ብሎ በምትኩ ጥቁር ሐውልት ሊሠራ እንደሚችል መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ለዘመኑ ቴክኖሎጂ ሣንታደል የበቀል ሐውልቶችን ሥንሠራና ስናፈርስ ልንኖር ነው፡፡ ወይንም መበቃቀልን እንደ መልካም ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ ልናሸጋግረው ነው፡፡



ኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ ላይ የቆመው ሐውልት

ሐውልት እንሥራ ካልን ደግሞ አሰሳ ላይ ቤት ተዘግቶባቸው ለተቃጠሉት፣ በደኖ ላይ ለተጨፈጨፉቱ፣ አርባ ጉጉ ላለቁት፣ አስቦት ገዳም፣ ጎንደር አደባባይ ኢየሱስ ለተገደሉት፣ ባርሲና በሐረር እስከነ ሕይወታቸው በገመድ እየታሠሩ ለተጣሉቱ፣ በጋምቤላ፣ በሲዳማ ላለቁት ሁሉ እጅግ ስቅቅ የሚያደርጉ ሐውልቶችን መሥራት ሊኖርብን ነው? ሰኔ 1 ቀን 97 ዓ.ም እና ጥቅምት 2 ቀን 98 ዓ.ም ባዲስ አበባ ጎዳናዎች የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው <የህዝብ ድምጽ ይከበር> ብለው በተሰለፉ ወጣቶች ላይ ባነጣጥሮ ተኳሾች ጭንቅላታቸውን እየተበረቀሱ የተገደሉት ሁሉ ጊዜው ሲፈቅድ ሐውልት ሊቆምላቸው ነው?






ሚያዝያ 30 ቀን 1989 ዓ.ም ጧት ወደ ሥራው ደፋ ደፋ እያለ ሲሄድ ከመንገድ ተደፍቶ የቀረው ያሡፋ ማሩ ደምምኮ ያስታዋሸ ያለህ እያለ ወደ እግዚአብሔር እየጮኸ ነው፡፡ እንዲሁም ጥር 1 ቀን 1989 ዓ.ም እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ሊቀጻጸሱ ባሉበት፣ ታቦት እየዞረ በጥይት የተገደሉት ባህታዊ ፈቃደ ሥላሴምኮ የሰማዕትነት ሐውልት ሊያስፈልጋቸው ነው? እንደዚህ ከሆነ ደግሞ በዘመነ ኢሕአዴግ ፋብሪካዎቻችን ሁሉ ሐውልቶች ብቻ ሊሆኑ ነው? ይህ ከሆነ ደግሞ ሠርተን ከድህነት አሮንቃ ውስጥ የምንወጣበት ራእይ ቀርቶ ቅዠት እንኳን ላይኖረን ነው፡፡ የጥላቻ መርዝ በሕዝቦች መሀከል እየተረጨ እንዴት ብለን ነው ከርሃብ የምንላቀቀው? ጠይቁ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የምናየው ደግሞ ባሕር ዳር ላይ የተገተረውን ሐውልት ነው፡፡ ይህ ሐውልት ለምንና ለነማን እንደቆመ የሚያውቁት ተካዮቹ ብቻ ናቸው፡፡ ባጭሩ ግን ያማራ ክልል ርእሰ ከተማ ከሆነችው ባሕርዳር ላይ በመተከሉ <ላማራ ታጋዮች> ሣይሆን አይቀርም ብለን እንገምታለን፤ ግን ደግሞ መቅደላ ላይ፣ መተማ ላይ፣ አድዋ፣ ማይጨው፣ ባምስት ዓመቱ ያርበኝነት ዘመን ለተዋደቁት ጀግኖች አባቶቻችን ወይንም በ69 ዓ.ም አጋዴን አሸ በልቷቸው ለቀሩቱ መደበኛና ሚሊሺያ ሠራዊት መታሠቢያ የቆመ ሐውልት ይሆን? ጠይቁ፡፡ በርግጠኝነት ግን ለተጠቀሱት እንዳልቆመላቸው መናገር እንችላለን፡፡ ታዲያ የት ላይ ለተፋለሙትና ለተዋደቁት ነው ሐውልት የቆመላቸው? ብለን ራሳችንን ብንጠይቅ የሚከተለውን መልስ እናገኛለን፡-



*በባህር ዳር ላይ የቆመው «ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት» ሐውልት*



የቅልጥም አምሳያ ሐውልት

በፊት ኢሕዴን በኋላ ሁን ያሉትን ለሆነው ብአዴን ታጋዮች የቆመ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም:: ይህ ከሆነ ደግሞ ያማራው ነፍጠኛ በኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ የቆመው <ቅልጥም ሠባሪ!> ተብሎ ሐውልት ተሠርቶበት እያለ ባሕሩ ዳር ላይ ደግሞ <ለነፃነት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለብሔረሰቦች እኩልነት፣ ለፍትሕ ሲዋደቁ ለተሠው!> ተብሎ ሐውልት የቆመላቸው የትኞቹ አማራዎች ናቸው? የትስ ላይ የተፋለሙ ናቸው? ከነማንስ ጋር ነው የተፋለሙት? የሚሉ ጥያቄዎችን ማስነሰታቸው የግድ ነው:: ወይንም ደግሞ "ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት" እንደሚባለው ዓይነት ይሆን? ይህንን ሁሉ ስናስብ ምን ዓይነት ሰብቀኛና አሸማቂ ሥርዓት ውስጥ ያለን መሆናችንን በውል እንገነዘባለን::

መቀሌ ላይ የቆመው ሐውልትም ይዞት ያለው መልዕክት ከተጠቀሱት የተለየ አይደለም፤ ያነኑ መከረኛ አማራ የትግራይ ልጆች በጥላቻ ሲመለከቱት እንዲኖሩ የቆመ ሐውልት ነው::

ከዚህ አዲስ አበባ ደግሞ መስቀል አደባባይ ወደ ቦሌ መውጫ <የቀይ ሽብር የሰማዕታት መታሰቢያ ሙዚየም> ተሠርቷል:: የዚህ ሙዚየም መልዕክትም ልክ እንደ ሐውልቶቹ የቂምና የበቀል ማስታወሻ ሆኖ እንዲኖር የተሠራ እንጂ ደምን የሚያደርቅ አይደለም:: ዓላማው ለፕሮፓጋንዳ ትርፍ ማግበስበሻ ታስቦ የተገነባ ነው:: ለዚህም ነው ደግመን ደጋግመን መሪዎቻችን እነማናቸው? ምንስ እየሠሩልን ነው? በማለት የምንጠይቀው::





አልታደልንም እንጂ ሕዝብ የመሪዎቹን ማንነትና ምንነት ማወቅ ብቻ ሣይሆን የሰብቅና የቅጥፈት ሥራ ሲሠሩ ሲያይ ከሥልጣናቸው የማውረድ መብትም ነበረው::

ለመሆኑ በነጭ ሽብርተኞች በጠራራ ፀሐይ በየጎዳናው ዳር ግንባር ግንባራቸውንና ከኋላ ጭንቅላታቸውን እየተመቱ የወደቁትስ አይዘከሩም? እነሱ ኢትዮጵያኖች አይደሉም? እናት'አባት፣ እህት'ወንድም፣ አጎት፣ ዘመድ አዝማድ አስታዋሽ የላቸውም? የነዚህ ወገኖች እንባና ደም እንዲደርቅስ አይፈለግም? ደመኛነቱስ ከነማን ጋር ነው? ከደርግ ጋር መሠለፋቸው ከሆነ ወንጀላቸው ዛሬ ከዚህ ጎሰኛ መንግሥት ጋር የተሰለፉት የወደፊት እጣ ፈንታቸው ምን ሊሆን ነው? እውነት እንነጋገር ካልን ኢሕአፓን በመጀመሪያ <ከክልሌ ውጡ!> ብሎ ጨፍጭፎ ካሲንባ ተራራ ያስወጣቸው ማነው? ሕወሓት አልነበረም? ሀቁ ይኸ ሆኖ እያለ ደርግን ብቻ የታሪክ ተጠያቂ ለማድረግ የሚደረገው ሩጫ ያስተዛዝባል:: በበኩሌ ሁሉም የየራሱን ድርሻ ማንሳት እንዳለበት አምናለሁ::

ሐውልት ወይንም ሙዚየም ያስፈልጋል ከተባለም <የቀይ ሽብርና የነጭ ሽብር> ተብሎ ሳይለይ የሁሉንም ደምና እንባ የሚያደርቅ በታሪክ አሣዛኝነቱን የሚገልፅ ሆኖ ቢሠራ የሁሉንም ስሜት ስለሚገዛ ገዥውን ፓርቲም የሚያስመሰግነው በሆነ ነበር:: ወደ አንድ ጎን ማዳላት ግን "ያዞ እንባ ማንባት ነው" የሙዚየሙ መሪ ቃል (ሞቶ) "አደራ መቹም እንዳይደገም!" የሚል ነው:: ታዲያ ወዳንድ ጎን እያዳሉ እንዴት "መቹም እንዳይደገም!" ብሎ ጥሪ ማስተላለፍ ይቻላል?

97 ዓ.ም እና 98 ዓ.ም ጅምላ ጭፍጨፋ አልተደገመም? ወይንስ ኢሕአዴግ የሚገላቸው እንደ አሸባሪ ተቆጥረው? እነዚህምኮ የሕዝብ ልጆች ናቸው? ኢሕአዴግ ሲገል ፍትሐዊ ሊባል፤ ደርግ በገደላቸው በጭራቅነት ሊፈረጅና ሊጠየቅ? እንዴት እንዲህ ሊኮን ይቻላል? ጠይቁ::

በሕይወት ያሉት የኢሕአፓ አባላት በዓለም ዙሪያ እንደጨው ተዘርተው እየባዘኑ ወዳገራቸው ገብተው በሰላማዊ መንገድ እንዳይታገሉ በጠረኛነት ወንጅሎ በማገድ ለተሰውቱ ሙዚየም መሥራቱ ቅቤ ማንጎት ነው::

እነዚህ ሐውልቶችና ሙዚየም ሁሉንም በደልተኞች ያሣተፉ ባለመሆናቸው የብሔራዊ ምስልነት የላቸውም:: በመሆኑም ዘመን ተሻጋሪዎች ሊሆኑ አይችሉም:: ይህ ከሆነ ደግሞ ያንድ ወቅት መፈክር ሆነው ከነበረው ሥርአትና መንግሥት ጋር ይወድቃሉ:: ለዚህ ምሳሌ

የሚሆነን ፒያሣ የሕንድ ኮሚኒቲዎች (ማኅበረሰቦች) ለግርማዊነታቸው ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት ለመግለጽ ሲሉ በ25ኛው የብር እዩበልዩ የዘውድ በዓላቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ያቆሙላቸውን ደርግ ሥልጣን እንደያዘ አፍርሶታል፡፡ ጊዮርጊስ ያለውን ያድዋን ድል የመታሰቢያ ሐውልትና ሌሎቹን ሐውልቶች ግን አልነካቸውም፡፡ ለምን ቢባል የሕዝብ ሀብቶች ናቸውና፡፡

ኢሕአዴግ በተራው ሥልጣን እንደያዘ ደርግ የሠራውን ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ፊት ለፊት ያለውን ግዙፍ ሐውልት ነቅሎ ባይጥለውም አስታዋሽ አጥቶ የውሃ ማስተላለፊያ አሸንዳዎቹ ወላልቀው ዳዋ ውጦት እያየነው ነው፡፡ ሌላ ምሳሌም እንጨምር፡-

ደርግ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን አሻራዎች ሁሉ አጥፍቶ አፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ፊት ለፊት የሌኒንን ሐውልት አቁሞ ነበር፡፡ ይህ ሐውልት በቆመበት ወቅት የሕዝብ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ እንደነበር እናስታውሰን፡፡ የተሰጠው መልስ ግን <የፀረ አብዮተኞች ተግባር ነው> የሚል ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ቀ.ኃ.ሥ ሐውልት ሊሠራላቸው ይገባ ነበር ብለን ባንከራከርም ለሀገራቸው እድገት ግን ብዙ መድከማቸው እውነት ነው፡፡ ሌኒን ግን ኢትዮጵያን ምናልባትም በዓለም ካርታ ላይ ካልሆነ በስተቀር ጨርሶ አያውቃትም፡፡ ታዲያ በምን ውለታ ነው ደርግ የነሐስ ሐውልት ያቆመለት? ብለን ብንጠይቅ መልሱ ከዚያው መከረኛ ሥልጣን ላይ ተጣብቆ ለመቆየት ሲባል ለሶቬቶች የእጅ መንሻ የቀረበ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህ ደግሞ የኢትዮጵያን ክብር ጨርሶ ያንኮታኮተ ነበር፡፡ በመሆኑም የሌኒን ሐውልትም ከደርግ ጋር አብሮ ወድቋል፡፡ ስለዚህ የምንሠራቸው ሥራዎች ሁሉ ዘመን ተሻጋሪዎች እንዲሆኑ የዚህ ብሔረሰብ፣ የዚያ ጎሣ ሳይባሉ የሁሉንም ሕዝቦች ሁለንተናዊ ስሜት የሚገዙና የሚያንፀባርቁ ሆነው መሠራት አለባቸው፡፡

ዘመን ተሻጋሪዎች የምንላቸው ቅርሶች ጥቅል የሀገር ሀብት ሆነው ጊዜና ወቅት የማይሽራቸው ወይንም መንግሥትና ሥርዓት በተቀየሩ ቁጥር አፍራሽ ኃይል የማይዘምትባቸው፣ ሕዝብ <የኔም> ብሎ የሚኮራባቸውና የሚመካባቸው መሆን አለባቸው፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን ያከሱም ሐውልቶች፣ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ የጎንደር የነገሥታት ግንቦች በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህ መቼም ይሁን መቸ አፍራሽ አይዘምትባቸውም፡፡ ስለዚህ የሚተከሉ ሐውልቶችም ሆኑ የሚገነቡ ኪነ-ሕንፃዎች ሕዝብ በሙሉ <የኔም ናቸው> ብሎ የሚኮራባቸው መሆን





እንዳለባቸው ይታመናል፡፡ ወደ አንድ ወገን ያጋደሉ ከሆኑ ግን ከጊዜ ጋር ፈራሾች ናቸው፡፡ ርግጥ ነው የወል ሀብት ሆነውም የግል ክፋት የተጠናወታቸው ግለሰቦች አጣመው በመተርጎም የሕዝብን የባለቤትነት ስሜትና ሀገራዊ ፍቅር ለማሣጣት ሲሞክሩ ይስተዋላሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

ጠ/ሚንስትር መለስ ባንድ ወቅት "ያከሱም ሐውልቶች ለወላይታው ምኑናቸው . . ." በማለት የተናገሩት የብዙዎችን ሕሊና በወቅቱ ማቁሰሉ ይታወቃል፡፡ የጠ/ሚንስትሩ አነጋገር "ኢትዮጵያ የምትባል አገር ከመቶ አመት የበለጠ ዕድሜ የላትም፡፡ ምኒልክ የሠሯት ናት" ለማለት ነው፡፡

ድሮ ድሮ የመሪዎች ንግግር ከፈላስፋዎች ጋር የሚወዳደርና ለጥቅስ የሚበቃ ነበር፡፡ በዚህ ዘመን ደግሞ የሚያሣፍርና አንገት የሚያስደፋ ሆኗል፡፡ የሚገርመው ደግሞ በእንዲህ ዓይነቱ መሪ ሙት መንፈስ እንግዛ መባሉ ነው፡፡


ስለሐውልት ግንባታ ስናነሳ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ሌላ አሣዛኝ ድርጊት አለ፡፡ ይኸውም አፍሪካ ሕብረት ግቢ ውስጥ የጋናው መሪ የነበሩት ንክሩማን ክዋሜ (Nkruma Kwame) ሐውልት ሲቆምላቸው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ግን ላፍሪካ ነፃነት እንዳልደከሙና ዋጋ እንዳልከፈሉ ተቆጥረው ወደታች መታየታቸው የብዙዎችን አንጀት ቆርጧል፡፡ ጠ/ሚንስትር መለስ ተጠይቀው ሲመልሱ፡-

*"ላፍሪካ ነፃ መውጣት ከኃይለሥላሴ ንክሩማ የተሻሉ ሆነው በመገኘታቸው ነው"* ማለታቸው የበለጠ ሕሊናን አቁስለዋል፡፡

ሌላም የምንጠቅሰው አለ፡፡ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ደርግ ካሠራው፣ ሐውልት ወደ ቀኝ ሲል ትንሽ ከፍ ብሎ ለኩባውያን የመታሰቢያ ሐውልት ቁሞላቸዋል፡፡

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ በለውጥ ማዕበል ውስጥ በነበረችበት ወቅት <ጊዜው አሁን ነው> በሚል የሶማሊያ ሠራዊት በ1969 ዓ.ም የምሥራቁን የሀገራችን ክፍል በወረረበት ወቅት ኩባውያን ከኛ ጎን በመሰለፍ ደማቸውን አፍስሰዋል፤ አጥንታቸውን ከስከሰዋል፡፡ ለዚህ ውለታቸውም ለመታሰቢያነት ሐውልት ቢቆምላቸው እጅግ የሚያስመሰግን ተግባር ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለምን ከማይመጥን ቦታ ላይ ከዚያ ጥሻ ውስጥ እንደተሠራች በበኩሌ አይገባኝም? በርካታ አደባባዮች እያሉን ከዚያ ውድማ ውስጥ የመተከሏ ጉዳይ የይስሙላ ይመስላል፡፡

በሌላ በኩል ግን እንደ ቅጠል ረግፎ የቀረው ዋናው ባለታሪክ የኢትዮጵያ የቀድሞው ሠራዊትና አገሬ ትበልጥብኛለች ብሎ ሞፈር ቀንበሩን ሠቅሎ፣ ቤተሠቦቹን በትኖ የዘመተው ሚሊሻ ሠራዊት አስታዋሽ አጥቶ እንደ ዉሻ ሬሣ አጋዴን አሸዋ ወድቆ መቅረቱ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ምን ያህል በቀልተኛና ጎሰኛ መንግሥት መሆኑን ከበቂ በላይ ማረጋገጫ ነው። እሱን አጅበው ለመጡት በየቦታው ለነገ ቁርሾ የሚሆኑ ሐውልቶችን ሲያቆምላቸው ከባዕዳን ወራሪ ጋር ተናንቀው ለወደቁት ግን እንኳንስ የታሪክ ምስክር የሚሆን የሐውልት ምልክት ሊያቆምላቸው ቀርቶ በሕይወት ያሉትን <የደርግ ሠራዊት> በማለት ጦር ኃይሎች ሆስፒታል የህክምና ካርዳቸውን ሣይቀር ሜዳ ላይ በመጣል በስብሶ እንዲቀር አድርጓል።



የቀድሞው የኢትዮጵያ መደበኛው ሠራዊት ከግማሽ ሚሊዮን በላይ እንደሚሆን ይገመታል። እያንዳንዱ ሠራዊትም ባማካይ ባምስት ቤተሰብ ቢወከል ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ቤተሰብ ወይንም ትውልድ የትም ተጥሏል ማለት ነው። የሥግነት ሐረግ ሲመዘዝ ደግሞ እያንዳንዱ ሠራዊት አባት፣ እናት፣ እህት፣ ወንድም፣ አክስትና አጎት ይኖረዋል። ይህ ሁሉ ሲታሰብ ደግሞ ከ10 ሚሊዮን የበለጠ ተቆርቋሪ አለው ማለት ነው።






ሕወሓት የጎሳ ጥላቻን ሥንቁ አድርጎ ሲነሳ ወይንም በረሃ ሲገባ በመጀመሪያ ዒላማ ያደረገው <አፄ ምኒልክ ጠፍጥፈው ሠሯት የሚላትን ኢትዮጵያ> ማፈራረስና እሱ በፈንታው <ሕወሓት ሠራሽ አዲሲቷ ኢትዮጵያ> የሚላትን የባሕር በር አልባ ጉራጅ አገር መፍጠር ነው። ለዚህም ነው ያንድነት ተጠሪና መሠረት እሱ ነው በሚል ከመነሻው ጀምሮ አማራን ቀንደኛ ባላንጣው አድርጎ በየደረሰበት የሚመታውና የሚያስመታው። ከ50 ዓመታት በላይ ልምድና የዳበረ እውቀት ያለውን የቀድሞውን ሠራዊት እንዳለ የበተነውም ያንድነቱ ምሰሶና ጠባቂ ነው በሚል ነው። ባሕር ኃይሏን በትኖ የባሕር በር አሣጣት። ለዝነኛነቱ የልጅ ገፀበረከት ሣይቀር የተበረከተለትን አየር ኃይሏን አፍርሶ አብራሪዎቹ ኤርትራን ጨምሮ የባዕዳን ሀገራት አሠልጣኞች ሆኑ። የምድር ኃይሏም የትም ተበትኖ ለቆሰለላትና ለደማላት አገሩ የበይ ተመልካች ሆኖ የመከራ ኑሮ እየገፋ ይገኛል።

ታዲያ ትልቁ ጥያቄ ይህ ሁሉ ሠራዊትና የሠራዊት ቤተሠብ ቂምና በቀል አልቋጠረም ማለት አንችልም። አዝኗል፤ ቆዝሟል፤ ባይሞትም ሞት የተፈረደበት በመሆኑ ጥላቻውን የሚያሽርለት፣ እባጩን የሚያፈርጥለት መፍትሄ ይፈልጋል። አለበለዚያ ትውልድ ጅረት ነውና ዛሬን በንቀት ብናልፍ ነገና ከነገ ወዲያ የሱን በቀል መወጣት አለብን የሚል ትውልድ ብቅ አይልም ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። እነዚህ ሁሉ ውስብስብ ችግሮች ተንቀውና ቸል ተብለው መታለፍ የሌለባቸው ቁምነገሮች ናቸው።

ሕወሓት በኢሕአዴግነቱ 21 ዓመታት ተጉዞ ይህንን እንደ ሀምሌ ደመና እየከበደ የመጣን ችግር ማስተዋልና መገንዘብ ከተሣነው ውጤቱ ቁናውን በቁና የመሠፈር እድሉ ሠፊ ነው። የዚህ ውጤት ደግሞ ለዚች አገርና ለዚህ በኑሮ ውድነት ለተንበሳቀለ ሕዝብ የሚበጅ አይደለም። የሚበጀው ጨኸት ቀንሰን ስንወያይና ስንመካከር ነው። ከአንግዲህ ለኢሕአዴግ የሚያዋጣው ምንም ይሁን ምን ከጀብደኝነትና ከትምከህት ተላቆ ብሔራዊ መግባባት መፍጠር ሲችል ብቻ ነው።

<><><>



የቅልጥም አምሳያ ሐውልት

# ፓርቲዎች ማደሪያዎች ወይንስ ማደናገሪያዎች

ባሁኑ ወቅት የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ እጅግ በፈጣን ሁኔታ የእድገት ግሥጋሴ ላይ ይገኛል:: ባንፃሩ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ እጅግ በሚያሣዝንና በሚያሳፍር መልኩ እያሽቆለቆለ ነው:: ከነፃ ውድነቱ፣ ከፍትሕ ጥማቱ ሌላ በጎሳና በብሔረሰብ ልዩነት የተነሣ በፖለቲከኞች እንደገመድ ጉተታ ጨዋታ ወዲህና ወዲያ ሲያጓትቱት ማየት ሕሊናን ያቆስላል:: የፓርቲዎቹ ጋጋታ ሲታይ ደግሞ <ማደሪያዎች ወይንስ ማደናገሪያዎች?> ያስብላል::

ሕወሓት አንዱን ገዥ ሌላውን ተገዥ አድርጎ የሣለላቸውን የሰብቅና የከፋት ሥዕል ፖለቲከኞቻችንም አምነው በመቀበል፣ ትናንትን በመውቀስና በማውገዝ ለዛሬው ችግራችን አንዳች መፍትሄ ሳይፈልጉ ነገ እነሱ የሚወቀሱበትን ጥቁር ነጥብ እያስቀመጡ ይገኛሉ:: አንዳንድ ጊዜ በሚያሣፍር መልኩ ተግጦ በተጣለ አጥንት እስበሳቸው እንደሚቧጨቁ ዉሾች በመናከስ የመከራውን ዘመን እንዲራዘም የድርሻቸውን እየተጫወቱ ይገኛሉ::

የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢሕአዴግ ብቻ ሣይሆን ኑሮዬና ማደሪያዬ ተብለው በተቋቋሙ የፓርቲዎች ጋጋታ እየታመሰ፣ በስሙ ብቻ <-ዴድ፣ -ነፃነት፣ -ግንባር. . .> እየተቀጠሉ በየማግሥቱ በሚፈበረኩ ፓርቲዎች መሣለቂያ መሆኑ ያሣዝናል:: ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት ሦስት እየሆኑ የፖለቲካ ፓርቲ መመሥረት ወይንም ማቋቋም ወጭን የማይጠይቅ የፈጠራ ሥራ ሆኗል:: የቀልድ ጨዋታም እየመሠለ መጥቷል:: ሌላው ቀርቶ አንዱን ብሔረሰብ <እኛ ነን የምንወክለው> በሚል አንዱን ብሄረሰብ እንደ ድፎ ዳቦ ሲቆራርሱት ማየት በራሱ ታምር ያሰኛል:: ለማንኛውም የፓለቲካውን የቁማር ጨዋታ በተመለከተ ለመፍረድ እንዲያስችለን እነሆ:-

## ኦሮሞ

የኦሮሞ ሕዝብ በቁጥር ካገሪቱ ሕዝብ ያንደኛ ደረጃን ይዞ ይገኛል:: ዳሩ ግን ይህ ሕዝብ በገዛ ልጆቹ ሣይቀር መቀለጃ ወይንም የፖለቲካ ድርጅቶች ቤተ ሙከራ መሆኑ ደግሞ ያሣዝናል:: የመገንጠል ዓላማ ይዞ ለረጅም ጊዜ





የኦሮሞን ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሲያናክስ የኖረውን ኦነግን ሣይጨምር አሥር የፖለቲካ ድርጅቶች አንዱን የኦሮሞ ሕዝብ እንደ ቅርጫ ሥጋ ለመቀራመት ሲያሰፈስፉ ማየት መታደል ወይንስ መታገል? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው:: ዝርዝራቸውን እነሆ:-

1. *የኦሮሞ ሕዝብ ነፃነት አንድነት ግንባር (ኦነአግ)*
2. *የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኦብኮ)*
3. *የኦሮሞ ሕዝብ ኮንግረስ (ኦሕኮ)*
4. *የኦሮሞ ፌደራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን)*
5. *የኦሮሞ አቦ ነፃነት ግንባር (ኦአነግ)*
6. *የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ)*
7. *የኦሮሚያ ነፃነት ብሔራዊ ፓርቲ (ኦነብፓ)*
8. *የኦሮሞ ነፃነት ፓርቲ (ኦነፓ)*
9. *ገዳ ሥርዓት አራማጅ ፓርቲ (ገሥአፓ)*
10. *የመላ ኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራቲክ ፓርቲ (መኦሕዴፓ)*

እንግዲህ እነዚህ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተመዝግበው እውቅና አግኝተው ሠርቲፊኬት የጨበጡ ናቸው:: ገና ለመቋቋም ዝግጅት ላይ ያሉ አራት ድርጅቶችም እንዳሉ በግሌ ለማወቅ ችያለሁ:: ለጊዜው የሚቋቋሙትን እንተዋቸውና በተቋቋሙት ላይ ትዝብታችንን እንስጥ::

እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ አሥሩ የፖለቲካ ድርጅቶች እያንዳንዳቸው ባማካይ አሥር አሥር አባላት ቢኖሯቸው 100 አባላት ይኖሯቸዋል እንበል፤ እነዚህ መቶዎቹ ባንድ የድርጅት ጥላ ሥር ሆነው አመራር ሠጭ በመሆን ለኢትዮጵያ አንድነት ታግለው ቢያታግሉ የኦሮሞን ሕዝብ ጥቅምም ሆነ ክብር ወይንም መብት ማስጠበቅ በቻሉ ነበር:: ዳሩ ግን ዕውቀቱም፣ ቀናነቱም፣ ብቃቱም የላቸውምና በየማግሥቱ ከሠፈር ዕድር ባነሰ መልኩ ሁለት ሦስት እየሆኑ ድርጅት በማቋቋም የሕዝብን ሕሊና ከኢሕአዴግ የበለጠ እያደሙት ይገኛሉ::

ለመሆኑ የነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች ኢሕአዴግን <ጎጠኛ፣ ጎሰኛ፣ ከፋፋይ> ብለው የመውቀስና የመቃወም ምን የሞራል ብቃት ሊኖራቸው ይችላል? ሌላው አስገራሚ ነገር ደግሞ አንድ የኦሮሞ ዜጋ በምርጫ ወቅት የኔን መብትና ጥቅም የሚያስጠብቅልኝ ወይንም የሚሟገትልኝ ይኸኛው ድርጅት ነው ብሎ ለመምረጥ አንዱን ከሌሎቹ ለይቶ ለማወቅ መመዘኛ የለውም፤ ወይንም የቅርብ መረጃ አያገኝም::

ፕሮግራማቸው አንዱ ከሌሎቹ ልዩነቱና አንድነቱ በግልጽ አይታወቅም:: በመሆኑም በምርጫ ወቅት ገዥውን ፓርቲ ከማጀብ ያለፈ ፋይዳ እስካሁን ሲያመጡ አላየንም:: ድርጎ ከመቀበል በስተቀርም የትግል ፅናትም የላቸውም::

## ጉራጌ

እንደሚታወቀው የጉራጌ ሕዝብ በሥራ ወዳድነቱ በንብ የሚመሠል ሕዝብ ነው:: የጉራጌ ሕዝብ <ጠላትሕ ማነው?> ተብሎ ቢጠየቅ <ሰንፍናና ሥራን መምረጥ ነው> ብሎ እንደሚመልስ አይጠረጠርም:: የጉራጌ ሕዝብ በሥራ ወዳድነቱ ብቻም አይደል የሚታወቀው:: በኢትዮጵያዊነቱም ጭምር ነው:: የጉራጌ ሕዝብ ከኢትዮጵያዊነት ውጭ ሌላ ቅዠት የለውም:: ታዲያ ይህንን ታታሪና ሥራ ወዳድ ሕዝብም በፖለቲካ ድርጅቶች ሊበልቱት ሞክረዋል:-

1. *የጉራጌ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ጉሕዴግ)*
2. *ሶዶ ጎርደና ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ሶጎሕዴድ)*
3. *የእንደገኝ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (እሕዴን)*
4. *የዱቤና ደጋኒ ብሔረሰብ ፓርቲ (ዱደብዴፓ)*
5. *ወለንኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ወቋተሕዴን)*

ደግነቱ ሁሉም <ዴሞክራት> በመሆናቸው በኢሕአዴግ ያጣነውን የዴሞክራሲ ጥማት በነዚህ እናረጥባለን::

## አፋር

ያፋር ሕዝባችን በሰሜናዊ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ዳርቻ ወይንም ኢትዮጵያን ከቀይ ባሕር የሚያዋስን ሲሆን ይህ ሕዝብ ባርብቶ አደርነት ይበልጠውን ይታወቃል:: ይህ ሕዝብም እንደ ጉራጌ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራና <እንኳን እኛ ግመሎቻችን ሰንደቃላማችን ጠንቅቀው ያውቃሉ> የሚል ሕዝብ ነው:: ያፋር ሕዝብ ኩሩ፣ ንቁ፣ ቁጡ ግን ደግሞ ካልነኩት የማይነካ ጨዋ ሕዝብ ነው:: ያለመታደል ጉዳይ ሆኖ ይኸ ሕዝብም በፖለቲካ ድርጅቶች ከመከፋፈል አላመለጠም::

1. *የአፋር ብሔራዊ ዴሞክራሲያ ፓርቲ (አብዴፓ)*
2. *የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (አአዴአግ)*
3. *የአፋር ነፃ አውጭ ግንባር ፓርቲ (አነአግፓ)*





4. *የአፋር ብሔራዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (አብአዴግ)*

## ሶማሌ

የሶማሌ ሕዝባችን በምሥራቅ ኢትዮጵያ ከካራማራ ተራራ ጀምሮ ሠፊውንና የተንጣለለውን የኦጋዴንን በረሃ አጠቃሎ የሚይዝ ሲሆን በእንስሳት አርቢነት ይታወቃል:: ይህ ሕዝብም አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ቋንቋ ተናጋሪ ሆኖ እያለ ጊዜ ከፈጠረው ውጭ መሆን ስላልቻለ የመገንጠል ዓላማ አንግቦ የሚታገለውን አብነግን ሳይጨምር በሦስት የፖለቲካ ድርጅቶች ተከፍሎ ይጓተታል:-

1. *የምእራብ ሶማሌ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ሶዴፓ)*
2. *የሶማሌ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ሰሕዴፓ)*
3. *የሶማሌ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅ (ሶዴኃቅ)*

## ሐረሪ

የሐረሪ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አንስተኛ ቁጥርና ጠባብ ይዞታ ይዞ ግን ደግሞ በክልል የተከለለ ሕዝብ ነው:: ይኸ ሕዝብም በሦስት የፖለቲካ ድርጅቶች ከመወከል አላመለጠም::

1. *የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ (ሐብሊ)*
2. *የሐረሪ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ሐሕዴፓ)*
3. *የሐረሪ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ሐዴድ)*

ቀጥለን ደግሞ የደቡብን ሕዝብ እንወክለዋለን የሚሉትን ድርጅቶች አንድ ባንድ እንመለከታለን:: እንደሚታወቀው የደቡብ ሕዝብ ቢያንስ ከ45 ያላነሱ ጎሳዎችና ብሔር ብሔረሰቦች የሚኖሩበት ክልል ነው::

## ሐድያ

1. *የሐድያ ብሔር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ሐብዴድ)*
2. *የሐድያ ብሔር አንድነት ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ሐብአዴድ)*

## ሲዳማ

1. *የሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን)*
2. *የሲዳማ ሀድቾ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ሲሀሕዴድ)*

## ወላይታ

1. ወላይታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ወሕዴግ)
2. ወላይታ ዴሪያ የሞያ (ወዴየ)

## ጋሞ

1. የጋሞ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ጋዴድ)
2. የጋሞ ጎፋ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት (ጋሕዴአ)

የከንባታ ብሔር ኮንግረስ (ከሕኮ)
የዘይ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ዘሕዴድ)
የደንጣ ዱባም ከችንችላ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ደዱ ከሕዴድ)
የጌዲኦ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ጌሕዴድ)
የየም ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (የብዴን)
የጠምባሮ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ጠሕዴሕ)
የባሕር ወርቅ መሰመስ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ባወመሕዴድ)
የኮንሶ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሕብረት (ከሕዴድ)
የኦሞ- ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ሕብረት (ኦሕዴሕ)
የዶንጋ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ዶሕዴድ)
የዲል ወቢ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ዲወሕዴን)
የቤንች ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ቤሕዴድ)
የሸኮና አካባቢ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ሸአሕዴድ)
የማኦኮም ልዩ ወረዳ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ (ማኮልወሕአን)
የጋምቤላ ሕዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጋሕአዴን)
የቤንሻንጉል ጉሙዝ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (ቤጉሕዴአግ)

## አርጎባ

1. የአርጎባ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (አብዴን)
2. የአርጎባ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (አሕዴድ)
3. ትግሬ ወርጅ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ትወብዴአፓ)





1. ትግራይ ለዴሞክራሲና ለፍትሕ (አረና)
2. ሕዝቢ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት)

1. የመላ አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአሕድ)
2. ብሔረ አማራ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን)

እስካሁን የገለጽኳቸው በየጎሳቸው የክልል ድርጅቶች የሆኑትን ነው:: ቀጥየ ደግሞ በጥቅል የደቡብን ሕዝቦች እንወክላለን የሚሉትን ሦስት የፖለቲካ ድርጅቶች እነሆ:-

1. የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ሕብረት (ደኢሕዴሕ)
2. የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች አንድነት (ደኢዴኃአ)
3. የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢሕዴን) ናቸው::

ቀጥለው የሚዘረዘሩት ደግሞ አገር አቀፍ ወይንም ኅብረ ብሔር ነን የሚሉት ናቸው::

1. የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኢሕአዴድ)
2. የኢትዮጵያ አዲስ ምዕራፍ ፓርቲ (አዲስ ምእራፍ)
3. የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)
4. የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ ፓርቲ (ኢሰዴፓ)
5. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (አብዴፓ)
6. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያውያን ፓርቲ (ኢዴፓ)
7. የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራት ፓርቲ (ኢሶዴፓ)
8. የኢትዮጵያ ዴሞክራት ሕብረት ፓርቲ (ኢዴሕ)
9. መላው ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (መኢደፓ)
10. የኢትዮጵያ ፓን አፍሪካኒስት ፓርቲ (ኢፓአፓ)
11. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት (ኢዴኃሕ)
12. የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ (አብአፓ)
13. የመላው ኢትዮጵያ ብሔራዊ ንቅናቄ (መኢብን)
14. ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ (ቅንጅት) ፎርጅዱ ነው::
15. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴአን)

16. *ብርሃን ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ (ብአዴፓ) ይኸ ፓርቲ ከአንድነት ጋር የተዋኸደው ነው።*
17. *አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)*
18. *የኢትዮጵያ ፍትሕና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ግንባር (ኢፍዴኃግ)*
19. *የኢትዮጵያ ራእይ ፓርቲ (ኢራፓ)*
20. *የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ)*
21. *የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ ፓርቲ (ኢሰዴፓ)*

እንግዲህ የፓርቲዎቹ ቁጥር አዲስ የተቋቋሙት ሣይጨመሩ የክልልና አገር አቀፎቹን ጨምሮ 80 ገደማ ይሆናሉ። አዲስ የተቋቋሙትና እውቅና ያላገኙት ሲጨመሩ ቁጥራቸው ወደ 98 እንደሚደርሱ ይታመናል። የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ጎሣዎች ቁጥር ከ85 በላይ-ናቸው ይባላል። የፓርቲዎቹ ብዛት ግን ከጎሣዎቹ በላይ ናቸው። የዚህ ምክንያቱ እያንዳንዱ ብሔረሰብና ጎሳ በሦስትና ባራት በመወከሉ ነው። በዚህ ሁኔታስ እየተጓተትን እንዴት ብለን ነው ልባዊ አንድነት ኖሮን እድገት ልናመጣ የምንችለው? እስቲ አምርራችሁ ጠይቁ። ዘጠኝ ባንዲራ መስቀላችንስ ዘጠኝ ሱሪ ያስታጥቀን ይሆን? ወይንስ አባቶቻችን እንደሚሉት "ዘጠኝ ሱሪ ከምን... አያድንም" እንደሚሉት።

በመሠረቱ የፖለቲካ ድርጅት መሥርቶ አንድን ጨቋኝ ሥርዓት መታገል መብት ብቻ ሣይሆን ግዴታም ጭምር ነው። እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብም የፖለቲካ ድርጅት አቋቁሞ በክልልና በተወካዮች ም/ቤት የራሱን ወኪሎች ቢያስቀምጥ መብቱን ማስከበር ብቻ ሣይሆን አገራዊ ስሜቱንም ከፍ ያደርግለታል። ይሁን እንጂ አንዱን ብሔረሰብ እንደ ሸንኩርት ካራትና ካምስት ከዚያም በላይ መከታተፍ በገዛ ዜጋ እንደመቀለድ ይቆጠራል። የትስ ለመድረስ ነው? ምንስ ለማምጣት ነው? አንድን ጨቋኝ ሥርዓት ከዘጠና ዘጠኝ ተበጣጥሶስ በምን ታምር ነው ታግሎ በድምፅ ብልጫ ማሸነፍና ለውጥ ማምጣት የሚቻለው? ጠይቆ።

የሕዝቡ ፍላጎትና ምርጫ አሁንም አንድ ሁኑ ነው። ቀናነቱ አለመኖሩ እንጂ ባንድ የፖለቲካ ጥላ ሥር ሆኖ፣ አገራዊ ራእይ ሠንቆ ቁመንለታል ለሚሉቱ ብሔረሰብ ወይንም ጎሳ መሟገት ይቻል ነበር። የከፋት ፍላፃ ደግኖ መፋጠጡ ግን ማንን ይጠቅማል? ዛፉን ቆርጦ በቅርንጫፉ ለመኖርስ እንዴትይታሰባል? ጠይቁ።





እነዚህ እስካሁን የጠቀስኳቸው 80 ፓርቲዎች መሀከል 65ቱ የ2002 ዓ.ም ምርጫን ተካፍለዋል። ውጤታቸው ግን ኢሕአዴግን ከማጀብ የዘለለ አይደለም። 4ኛው ዙር ምርጫ ኢሕአዴግ ተቃዋሚዎችን የገደለበት ብቻ ሣይሆን ራሱም የሞተበት ነበር። 99.6 ማምጣት ማለት ዘረፋና የለየለት አምባገነንነት ለመሆኑ አያከራክርም። ኢሕአዴግ አለ የሚለውን የዴሞክራሲ ጭላንጭል ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ የጣለው ለመሆኑ ከዚህ የበለጠ ማረጋገጫ ልናገኝ አንችልም።

ይኸነኑ የ2002 ምርጫን ለመገምገም በሚል ገዥውን ፓርቲ ጨምሮ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከፍተኛ አመራሮች ህዳር 22 እና 23 ቀናት 2003 ዓ.ም የሁለት ቀናት ወርክሾፕ ቢጤ አዳማ ከተማ ገልማ አባ ገዳ አዳራሽ በኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ተዘጋጅቶ ነበር። በዚህ ወቅት ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ከፍተኛ ያመራር አባላት ለመድረኩ መሪ ለፕሮፌሠር መርጊያ በቃና ስለተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋጋታ (ብዛት) ጥያቄ ተጠይቀው *"እናንተ በኛ አገር ስላሉት የፓርቲዎች ብዛት ልትደነቁ ትችላላችሁ። ደቡብ አፍሪካ ግን 150 ፓርቲዎች አሏት።"* በማለት ሲመልሱ ከተሣታፊዎቹ የተሰጣቸው መልስ:-

*"በርግጥ አፓርታይድ በነገሠባት አገር 150 ፓርቲዎች ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል። የሷ ተሞክሮ ግን ለኛ አገር በፍፁም አይሠራም። የዘረኝነትን ልምድ ለመቃረም ከሆነ ብቻ ነው ሊጠቅም የሚችለው"* የሚል ነበር።

እንደተባለው ደቡብ አፍሪካ 150 ፓርቲዎች ሊኖሯት ይችላሉ። ለምንና ለማን ማፈኛዎች እንደተቋቋሙ ግን ፕሮፌሰር መርጊያ አላብራሩም እንጂ ዓላማና ግባቸው ያነኑ ዘረኛ ፖሊሲ በሕይወት ለማቆየትና የጥቁሮችን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ለማኮላሸት መሆኑ ማንም አይስተውም። ይህም ሆኖ ግን አይቀሬውን ለውጥ ለማስቀረት ደቡብ አፍሪካ አልቻለችም። በተወሰነ መልኩም ቢሆን ዛሬ ደቡብ አፍሪካ አፓርታይድን ጨርሳ አጥፍታለች ባትባልም ባንፃራዊ መልኩ ስትታይ ሰላምና መረጋጋት የሚታይባት አገር ሆናለች። እያስመዘገበች ያለችው እድገትም የሚያመረቃን ነው። እኛም ኢሕአዴግ በሚቀድልን ቦይ መፍሰሳችንን አቁመን፣ የግል ዝናንና ጥቅምን ወደ ጎን ትተን አገራዊ ራእይ አንግበን ቢያንስ ባንድና በሁለት ተፎካካሪ ፓርቲዎች ታቅፈን ኢሕአዴግን መፎካከር ከቻልን በመልካም ስም የምንጠራበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም።

ለውጥ እናምጣ፣ እድገት እናስመዘግብ፣ ከምር እንታገል ካልንም ለዚች አገር ኢሕአዴግን ጨምሮ ሦስት አገር አቀፍ ፓርቲዎች ከበቂ በላይ ናቸው:: ከነዚህ በላይ የፓርቲ ጋጋታ ማብዛት ለማደናገሪያና በሕዝብ ስም ድርጎ ለመቀበል ነው:: ሕዝብም ከርቀት ሆኖ ተመልካች ከመሆን ወይንም የጉዳዩ ባለቤት መሆኑን አውቆ ለውጥ ለማምጣት የሚታገሉትንና ቀለብተኛ የፖለቲካ ድርጅቶችን ለይቶ በማወቅ ከኢህአዴግ የበለጠ ሊታገላቸውና ሊጠላቸው ይገባል:: በስሙ ሲነግዱበት ዝም ብሎ ሊመለከታቸው አይገባም:: በየእለቱ በሚፈለፈሉ የጎሳ ፖለቲካ ድርጅቶች ፀኩል ለውጥ ይመጣል ብሎ የሚያስብ ዜጋ ካለ ትልቅ ታሪካዊ ስህተት ነው::

እውነት እንነጋገር ከተባለም የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ከገዥው መደብ ሥልጣን የመረከብ ጉዳይ አይደለም:: ወይንም ያይዲኦሎጂ (የርእዮት ዓለም) ልዩነትም አይደለም:: አገርን ከከፋ አደጋ የመታደግ ጉዳይ ነው:: ልብ ብለን አጢነን ከሆነ ብሔራዊ አንድነታችን አደጋ ላይ ወድቋል:: በቂምና በበቀል ተቋጥሯል:: ይህንን የከፋት ቋጠሮ በጥሶ ለመጣል አንድ ከንድ፣ አንድ አመለካከትን ይጠይቃል:: አገር የምትናድበት የመሠረት ድንጋይ እየተነጠፈ ብሔራዊ አንድነታችን አስጊ ደረጃ ላይ መድረሱን እያየንና እያወቅን የየጎሳዎቻችን «ነፃ አውጭዎች ነን» እያልን መቀለዳችን ከዚህ ላይ መቆም አለበት:: በተለይም ምሁሮቻችን ከጎሳ ኩሬ ውስጥ መንቦጫረቃቸውን ማቆም አለባቸው:: 21 ዓመታት አየናቸው፤ ታዘብናቸው፤ በፍፁም አላማረባቸውም:: ቢያንስ እንደ ምሁርነታቸው አመለካከታቸው መስፋት አለበት:: የምሁር ጠባብና ጎሰኛ መሆን እጅግ አድርጎ ያሣፍራል:: ከጎሣቸው ውጭ ያለውን ሕዝብ እንደ ከፉ ጠላት ሊመለከቱት አይገባም:: የገዥዎች እንጂ የሕዝብ ከፉና ጨካኝ የለውም:: ሕዝብ ጨካኞችና ከፉዎች ካልበጠበጡት በስተቀር የረጋ እውቅያኖስ ነው:: ስለዚህ ይህ ወቅት የምሁሮቻችን የመፈተኛ ወቅት ነውና ፈተናውን በጥሩ ውጤት ያልፉ ዘንድ ለብሔራዊ መግባባት አእምሮአቸውን ከፍት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: ለማንኛውም «ከኔወዲያ ላሳር» ከሚልየተጠናወተ አስተሳሰብ በመጀመሪያ መላቀቅ አለባቸው::

<><><>





# “ከኔ ወዲያ ላሣር!”

ከዚህ ቀደም ባለው ምእራፍ <ፓርቲዎች ማደሪያዎች ወይንስ ማደናገሪያዎች?> በሚለው ርእስ ሥር 21 ዓመታት ተጉዘን ምንም ዓይነት ለውጥ አለማምጣታችንና ወደፊትም ገዥውን ፓርቲ ከማጀብ ያለፈ ፋይዳ እንደማይኖራቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቂ የሆነ ግንዛቤ አግኝቷል::

በ1966 ዓ.ም አብዮቱ እንደፈነዳ እንዲህ እንዳሁኑ የፖለቲካ ድርጅቶች እንደ እንጉዳይ ፈንድተው ነበር:: አንዳቸውም ግን ለውጤት ሣይበቁ ይችን አገር የወላድ መሀን አድርገዋት ቀርተዋል:: ለዚህም ነው ብቃት እንጂ የፓርቲዎች ጋጋታ ፋይዳ የለውም የምንለው:: በዚያን ጊዜ የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶችም መላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ወዛደር ሊግ (ወዝ ሊግ) አብዮታዊ ሰደድ (ሰደድ) ማርክሲስት ሌኒንስት ሬቮሊሽን ድርጅት (ማሌሬድ) የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል (ኢጭአት) የኢትዮጵያ ኮሚኒስቶች ፓርቲ (ኢኮፓ) ይህ ድርጅት አንድ ሰሞን ብቅ ብሎ የጠፋ ነው:: በሕዝብ ዘንዳ አይታወቅም:: በወቅቱም አንዳንዶች “የኮሚኮች ፓርቲ” ይሉት ነበር:: ከተጠቀሱት ሌላም የኢትዮጵያ ዴሞክራት ሕብረት (ኢዴሕ)፣ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)፣ ወያኔ ሕዝብ ሀርነት ትግራይ (ሕወሓት) እና ሻዕቢያ ነበሩ:: እንግዲህ እነዚህ ሁሉ የተለያዩ ዓላማዎችንና ተልዕኮዎችን ይዘው ኢትዮጵያን ለመቀራመት ሽሚያ የገጠሙበት ወቅት ነበር::

ሻዕቢያ፣ ሕወሓትና ኦነግ የመገንጠል መርህ ያነገቡ ሲሆን ኢዴሕ በበኩሉ “መሬት ለባለርስት፣ ቤት ለባለቤት!” የሚል መርህ ነድፎ ጉልታዊውን ሥርዓት መልሶ ለማቆም ነበር ይታገል የነበረው:: የቀሩት ግን ደርግን ጨምሮ ዓላማቸውና መርሃቸው አንድ ሆኖ ሶሻሊዝምን እውን ለማድረግ መታገል ነበር:: ዳሩ ግን በዓላማና በመርህ ሣይለያዩ ሥርዓተ ሶሻሊዝምን እኔ ነኝ የምተረጉመው በሚል በተለይም መኢሶንና ኢሕአፓ “ከኔ ወዲያ ላሣር” በማለታቸው እስበሳቸው እጅግ በሚያሣዝንና በሚያሣፍር መልኩ ተራርደው ውጤቱ ዜሮ ሆነ:: አገሪቱንም ዛሬ በተጨባጭ እንደምናያት ልትወጣው ወደ ማትችለው ቀውስ ውስጥ ገብታለች:: ከሞት የተረፉት የመኢሶንና የኢሕአፓ አባላትም በዓለም ዙሪያ ተበትነው የከፋ ሕይወት ይገፋሉ::

ለመሆኑ <አሣር> ማለት ምን ማለት ነወ? <አሣር> ማለት ፍዳ፣ መከራ፣ ችጋር፣ ሊወጡት የማይችሉት ማጥ ማለት ነው፡፡ ይህንን ማጥ፣ ይህንን ችጋር፣ እኔ ነኝ የምወጣው፤ ያለኔ አይሣካም” የሚሉ ደግሞ <ከኔ ወዲያ ላሣር> ባዮች ናቸው፡፡ <ከኔ ወዲያ ላሣር> የሚሉ ሰዎች ራሳቸውን ከማንም ከምንም በላይ አድርገው የሚኮፈሱና ከትሁትነት ሐስተሳሰብ በእጅጉ የራቁ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በራሳቸው የሚተማመኑና ልበ ሙሉዎች ግን <ከኔ ወዲያ ላሣር> አይሉም፡፡ የሰዎችን ምክር ይቀበላሉ፡፡ <ከኔ ወዲያ ላሣር> ባዮች ግን ከነሱ ወዲያ ላገሩ ተቆርቋሪ፣ ከነሱ ወዲያ ምሁር፣ ከነሱ ወዲያ ታጋይ. . . ላሣር ነው ብለው ስለሚያምኑ የሌሎቹን ሐሳብና ምክር አይቀበሉም፡፡ ስለሆነም በራሳቸው ስሜት በጭፍን ስለሚራመዱ በታሪክ እንደታየው ለውጤት አይበቁም፡፡ አልፎ አልፎ እንደ ሕወሐት ቢሳካላቸው እንኳን ጦርነት አምላኪዎችና ጀብደኞች በመሆናቸው የኋላ ኋላ መቋጫ ወደ ሌላው ማጥ ውስጥ ራሳቸውንም፣ አገርንም ይዘው መግባታቸው አይቀሬ ነው፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ኢሕአዴግ ራሱ ነው፡፡ ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ በጎሳ ከፋፍሎ የሚያምሰው አንሶ ጎረቤት አገር ሶማሊያ በመግባት የኢትዮጵያን የቆየ መልካም የጉርብትና ገጽታ አጥቁሯል፡፡

<ከኔ ወዲያ ላሣር> ባዮች ጎልተው ከሚታወቁበት ልዩ ባህሪያቸው ጀብደኝነት፣ ትምክህት፣ እብሪትና ማን አህሎኝነት ሲሆን ሌሎችን መናቅ፣ ማንጓጠጥ፣ ለሐሳባቸው ቦታ አለመስጠትና ችግሮችን በውይይትና በምክክር ከመፍታት ይልቅ በኃይልና በጉልበት ነው ለመቋጨት የሚጥሩት፡፡ ይህ በመሆኑም ውጤታቸው አያምርም፡፡

ከፍ ብዬ ለመግልጽ እንደሞከርኩት ሁሉም መርሀቸው ወይንም ርእዮት ዓላማቸው ሶሻሊዝም ሆኖ ሳለ “ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም” እንዲሉ መቻቻል' መመካከርና መደማመጥ ተሰኗቸው ሁሉም “ከኔ ወዲያ ሶሻሊዝምን ተርጓሚ፣ ሶሻሊዝምን ጠንቅቆ የሚያውቅ ላሣር ነው” በሚል በተለይም መኢሶንና ኢሕአፓ እስበሳቸው ትንቅንቅ በመግጠም የችግሩን ባለቤት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሣይቀር ከምንም ባለመቁጠር “እኛ እናውቅልሃለን” በማለት ደርግንም ምንም የማያውቅ ደንቆሮ ሠራዊት አድርገው በመገመት አንድ ሆነው ትኩሱን ለውጥ በሰከነ መልኩ ሕዝቡን አረጋግተው ሊያታግሉት ሲገባ ኢሕአፓ ከንቀቱ የተነሳ በትምክህተኝነትና በጀብደኝነት ታውሮ ወይንም ልቡ ተደፍኖ ገዳይ እስኳድ በከተማዎች በማሠማራት በሽጉጥ መትረየሶችና መድፎች፣ ታንኮችና የጦር ጀቶች የታጠቀን በዘመናዊ ውትድርና የሠለጠነን ሠራዊት ደረት ለደረት በመግጠም ልበሰሉ ቀንበጦችን በማስቀጠፍ እናቶች ‍ ‍ ‍ ‍ ‍ ‍ ‍ ል አልብሷል፡፡





ለውጥ መጣልን ብለው ከደርግ ጎን የተሠፉትን የቀን ሠራተኞች፣ ወዛደሮች፣ አብዮት ጠባቂዎችን፣ ተራ ወታደሮችን፣ መምህራንን . . . ወደ ሥራ ሲሄዱና ከሥራ ሲመለሱ ከመንገድ እየጠበቀ ግንባር ግንባራቸውን እያለ ደፋቸው፡፡ አብዮቱ በነዚህ ደም ቀለመ፡፡ ሕዝቡ <ዲሞን በዲሞትፈር አስታጥቁን አታስፈጁን!> ሲል ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰማ፡፡ ይህን ጊዜ ደርግ የመኢሶንና የኢሕአፓን ድርጊት በጥንቃቄ ይመለከት ነበርና “ለካ ምሁር ማለት እንደዚህ ነው? እኔ አንድ ዐይና ኢትዮጵያን በሥዕል ሥዬ ‹ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም!› ብዬ የተነሣሁት በሰላማዊ መንገድ ለውጥ የምናመጣ መስሎኝ እንጂ ለመግደሉማ የሰለጠንኩበት አይደል!” አለና ለጊዜው መኢሶንን ከጎኑ በማሰለፍ “ያንድ ታጋይ ደም በሺ አናርኪስቶች ደም ይመነዘራል!” በሚል መሪ መፈክር እጅግ በሚዘገንና በሚያሸማቅቅ መልኩ “ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር አፀፋው ይመለሳል!” በማለት አንድን ትውልድ በጅምላ በሌሊትና በቀን እየረሸነ እንደ ዉሻ ሬሣ በየጎዳናው ዳር ጣላቸው፡፡ የታደሉ እናቶች ከሁለት ልጆቻቸው መሀከል ቁመው አነቡ! ያልታደሉ እናቶች ግን ሬሣ በማገላበጥ ብቻ እስከ መጨረሻው ድረስ የልጆቻቸው ሬሣ የት እንደ ተጣለ ሣያውቁ ቀሩ፡፡

ከዚህ በኋላ ከደርግ መቅሠፍት የተረፈው ወይንም ያመለጠው የከተማ ፋኖ ከከተሞች በመውጣት ወደ ትግራይ ተራሮች (አሲንባ) ሄዶ መሸገ፡፡ ከዚያም አልቀናው በሕወሓት ተመቶ በዓለም ዙሪያ ተበተነ፡፡ የታደሉ ተማርከው ወይንም እጃቸውን ሠጥተው ዛሬ ገዥዎች ሆነዋል፡፡

ደርግ በደም ሠክሮ ነበርና ፊቱን ወደ መኢሶንና ወዝ ሊግ በማዞር ተራ በተራ ከመታቸው በኋላ እሱም ርቃኑን ቀረ፡፡ እንግዲህ ኢትዮጵያን ለመቧጨቅ እሠፍስፈው የነበሩት ሁሉ እስበሳቸው ተባልተው አገሪቱንም አደጋ ላይ ጣሏት፡፡ በመጨረሻም ደርግም <“ከኔ ወዲያ አገር ወዳድ ላሣር ነው> ባይ ነበርና በረባሶ ጫማ በተጫሙ፣ ጉርድ ከላሽንኮቭ ጠመንጃ በታጠቁ፣ ሸርጥ በጠመጠሙ፣ ባህያና በበቅሎ በተጫኑ ሥንቅ በሰሜን ኢትዮጵያ ልጆች ተንበርክኮ ጠመንጃውን፣ መትረየሱንና ታንኩን፣ መድፉንና የጦር ጀቱን፣ ሀገሪቱን ጭምር አስረክቦ ብትንትኑ ወጣ፡፡ <የከኔ ወዲያ ላሣር> ባዮች ውጤቱ ከዚህ ውጭ ሊሆን አይችልምና የሆነው ይኸው ነበር፡፡ ዛሬ እያስፈራን ያለውም ይህ እንዳይደገምና ቁናውን በቁና መስፈር እንዳይመጣ ነው፡፡ ከዚህ ውድቀት የምንማረው ቁምነገር ጀብደኝነት፣ ትምክህተኝነት፣ ከኔ ወዲያ ባይነት የትም እንደማያደርስ ነው፡፡ የኢሕአፓን ጀብደኝነትና እብጠት ልብ ብለን ስናጤነው ያስገርማል፡፡ በሽጉጥ ከታች

ያሉትን የኅብረተሰብ ክፍሎች ጭንቅላታቸውን ብሎ በመግደል ሥልጣን እይዛለሁ ብሎ ማሠቡ በራሱ ምን ያህል <ከኔ ወዲያ ላሣር> ባይነት እንደተጠናወተው መረዳት ይቻላል፡፡ ደርግ የሠለጠነ የሠራዊት ስብስብ ነው፡፡ በዚህ ላይ ከኋላው የሚመካበት የሀገሪቷ የመከላከያ ኃይል አለው፡፡ ለቆመለት ዓላማ ገና ያልተሰላቸ አፍለኛ ነው፡፡ የሚይዘውን የሚጨብጠውን አጥቶ እየተቅበዘበዘ የነበረበት ወቅት በመሆኑ እንዲህ በዋዛ በከተማ ነውጥና ሽብር ሥልጣኑን ይለቃል ተብሎ መታሰቡ የጀብደኞች እብጠት ነበር፡፡ ዓላማው ዜጎችን በፍርሃት አሸማቆ ወደ ደርግ እንዳይጠጉ ለማድረግ የተጠጉትን ቀድሞ መምታት ነበር፡፡ የሆነው ግን <አስታጥቄን አታስጨርሱን> የሚል ነበር፡፡ በመሆኑም ኢሕአፓ የታችኛውን የኅብረተሰብ ክፍል ጥግና ከለላ፣ እንዲሁም አለኝታነት በማጣቱ አሲንባ ተራራ ወጥቶ ለከፋ ችግርና ለመጨረሻ ውድቀቱ የበቃበት ምክንያት <ከኔ ወዲያ ላሣር> ባይነት ያመጣበት መዘዝ መሆኑን ዛሬ እኛ ልብ ልንል ይገባናል፡፡

እንግዲህ ያ ትውልድ ትምህርቱን ከዩኒቨርስቲ እያቋረጠ ኢትዮጵያን ከንጉሣውያን አገዛዝ ለማላቀቅ ቅን አስተሳሰብ ይዞ ቢነሣም ከልምድ እጥረት፣ ከችኩልነት፣ ሥልጣን ለመጨበጥ በመጓጓት፣ ያገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታና ታሪካዊ አመጣጧን በሚገባ ባለማጤን፣ በምዕራብውያን ሥርዓተ ትምህርት የተመረዙ <ከኔ ወዲያ ላሣር!> የሚሉ ጀብደኞች አመራር ላይ ወጡና መተኪያ የሌላቸውን ቀንበጦች የሳት እራት አደረጓቸው፡፡ ተርመጥምጠው ቀሩ፡፡ ለመሆኑ የዚህ አሣፋሪ ድርጊት በታሪክ ተጠያቂው ማነው? ደርግ? ኢሕአፓ? መኢሶን? ወይንስ ሁሉም? የዚህ መልሱ አስቸጋሪና አወዛጋቢ ነው፡፡ ብዙዎች ግን ደርግን ስህተተኛና ፋሽሽት እንደሆነ አድርገው በደፈናው ይኮንኑታል፡፡ ይህ ግን ሀቅን የተከተለ አይደለም፡፡ ይህንን የመሰለውን ጉዳይ ለታሪክ ሰዎች መተው የተሻለ ነው የሚሆነው፡፡ ከዚህ ይልቅ መነሳት ያለበት ጥያቄ አብዛኛዎቹ የኢሕአፓና የመኢሶን ከፍተኛ ያመራር አባላት የመጡት ከሠለጠነው ዓለም ካውሮፓ ነው፡፡ ታዲያ ከሠለጠነው ዓለም የተሻለ የትግል ስልትና ተመክሮ ይዘውልን ሊመጡ ሲገባቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በባህሉ፣ በወጉ፣ በልማዱ የሚያውቀውንና የሰለቸውን የስበስ በጭካኔ መገዳደልንና መተራረድን ለምን መረጡ? ዛሬም ቢሆን እንጠይቅ፡፡

እንደሚታወቀው በማይጨው ጦርነት ወቅት ኢጣሊያ በዘመናዊ የጦር መሣሪያ በመጠቀም በተለይም ያድዋን ሽንፈቷን በቀል የተወጣችው በመርዝ ጋዝ ሳይቀር በመጠቀም ነበር፡፡ ለመሸነፍ የበቃነውም በዚህ ምክንያት ነበር፡፡





እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያባቶቻችን ቁጭት <ሽንፈትና ውርደት የደረሰብን ዘመናዊ ትምህርት ባለመማራችን ነው> ብለው አመኑ፡፡ እውነትም ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ከድል በኋላ ወጣቶችን በገፍ ወደ ዘመናዊ ት/ቤቶች አስገብቶ ማስተማር ተጀመረ፡፡ በባዕዳን መምህራን፣ የባዕዳንን ጥበብ ለመቅሰም የህልም ሩጫ ተጀመረ፡፡ የጉም ሥር ለመጨበጥ . . .

እንግዲህ ያ ትውልድ ከታሪካችን፣ ከባህላችንና ከኑሯችን ጋር ያልተጣጣመና ያልተዋሀደ ውሃና ዘይት የሆነ ትምህርት በመጋቱና እንግሊዘኛ ቋንቋን በመናገሩ ብቻ ቁንጮ የሆነውን ያገርን ችግር ፈችውን ጥበብ የጨበጠ መስለውና አገሩንና ያገሩን አዛውንቶች የቁልቁል በንቀት ተመለከተ፡፡ እሱም የቁልቁል ማደጉን ሣያውቀው ዘቅዝቆ ወረደ፡፡ አባቶችም ልጆቻቸው እንግሊዘኛ ቋንቋ ሲናገሩ በመስማታቸው ተደስተው ያወቁ፣ የበቁና የነቁላቸው ስለመሰላቸው መሥመር ለቀው አየር ላይ ሲከንፉ እያዩ ከመምከርና ከመገሠፅ ይልቅ የበታችነታቸውን አምነው በመቀበል ልምዳቸውን፣ ተሞክሯቸውን፣ ባህልና ወጋቸውን ሣያወርሷቸው ለነሱ አጎበደዱ፡፡ እውነታው ግን የተማሩት ትምህርት ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌለው በባዶ ጉራ በመኮፈስ የጭካኔና እስበስ የሚያስተራርድ የውንብድና ትምህርት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ያ ትውልድ "የብሔር ጭቆና፣ እስከ መገንጠል . . ." በሚሉ አማላይ መርሆዎች ተመርዞና ጭንቅላቱ ዞሮ አንዱንም ሣይጨብጠው እስበሱ ተራርዶ ወላጆቹን አሳዝኖ፣ አገሩንም ጎዳ፣ ሆኖ ያለፈው ይኸ ነበር፡፡ ዛሬም አገሪቱን በሙት መንፈስ የሚያምሷት የዚያ ትውልድ ቅሪቶች ናቸው፡፡

በመሠረቱ እንግሊዘኛ ቋንቋ መናገር በራሱ ከፋት የለበትም፡፡ እንዲያውም የተለያዩ ቋንቋዎችን መጠቀም መቻል እንደ መታደል ይቆጠራል፡፡ ችግሩ እንግሊዘኛ ቋንቋን መናገር እንደ መሠረታዊ ዕውቀት ከመቆጠሩ ላይ ነው፡፡ የዚያ ትውልድ ችግር ይኸ ነበር፡፡ የሚከተለው ሀቅ ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል፡-

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ (ያሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ) በተማሪዎች አመፅ ይዘጋና የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ወደየትውልድ ቀያቸው ሲበተኑ የተማሪዎቹ የወቅቱ ፕሬዚዳንት የነበረው ጥላሁን ግዛውም ወደ ትውልድ ቀየው መምጣቱን የሰሙት ያውራጃው ገዥ አቶ ስዩም ያዕቆብ ትንሽ ተራማጅ ቢጤ ነበሩና ጥላሁን ግዛው ከቤታቸው ድረስ መጥቶ ስለወቅቱ ሁኔታ እንዲያነጋግራቸው ባማርኛ ቋንቋ ደብዳቤ ጽፈው በክብር ሲልኩበት ሄዶ ሊያነጋግራቸው ሲገባ ከሳቸው ጋር መነጋገር እንደማይፈልግ

በቃል መልሶ ይልከባቸዋል:: ይህ አይነቱ አብጠትም የዚያ ትውልድ ችግር ነበር:: ለውድቀት ያበቃውም ይኸ ትቢቱ ነበር::

ያውራጃው አሥተዳዳሪ ግን የትውልዱን አመለካከትና ሐስተሳሰብ ቀድመው የተረዱ ነበሩና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ጽፈው ለሁለተኛ ጊዜ ላኩበት:: በዚህ ወቅት ጥላሁን ግዛው ያላንዳች ማቅማማት ከቤታቸው ድረስ ሄዶ ያነጋገራቸው መሆኑን አስማማው ኃይሉ <ኢሕአሠ> በተባለው መጽሐፋቸው በገጽ 210 አስፍረውት ይገኛል:: በተመሣሣይ ያውራጃው ገዥ ለጥላሁን ግዛው የዘመኑ ትውልድ ከራሱ ቋንቋ ይልቅ ለእንግሊዘኛ ቋንቋ የበለጠ ክብርና ክብደት እንደሚሠጥ ትዝብታቸውን እንደገለፁለት አሥፍረዋል::

እንግሊዘኛ ቋንቋ ዛሬም ቢሆን የዕውቀት መለኪያ ተደርጎ ስለመቆጠሩና በእኛነታችን ላይ ስለሚፈጥረው ጫና የሚከተለው ማስረጃ ከበቂ በላይ ማረጋገጫ ይሆናል::

በነሐሴ ወር 1994 ዓ.ም በጠ/ሚንስትር መለስ ሰብሳቢነት የከፍተኛ ት/ቤቶች መምህራን ተሰብስበው በተወያዩበት ወቅት ያላንዳች ማጋነን ውይይቱ ተካሄዶ የነበረው እንግሊዘኛና አማርኛ ቋንቋን እኩል በኩል በመቀላቀል ነበር:: ይህንኑ ሂደት እውቁ ጋዜጠኛ ማዕረጉ በዛብህ እንዲህ ሲሉ በወቅቱ ተችተውት ነበር:-

*". . .እኛ ባሁኑ ወቅት የታዘብነው አማርኛና እንግሊዘኛ ቋንቋ መሣ በመሣ የተነገሩበት ጊዜ ነበር"* ካሉ በኋላ ምሁሩ ባማርኛ ቋንቋ በቀላሉ ሊገለፁ የሚችሉትን ሐሳቦች በእንግሊዘኛ ቀላቅለው የገለፅዋቸውን እንደሚከተለው አቅርበዋቸዋል:-

*"አንድ ሰው ዲሲሽን የሚወሰደው በኢንፎርሜሽን ቤዝድ ሆኖ ነው:: ስለዚህ የኢንፎርሜሽን አይቬለቢሊቲ ደግሞ ኢፖርታንት ነው:: በጉዳዩ ብዙ ዲሲሽን ቢደረግበትም ችግሩ ገና አድሬስድ አልሆነም:: ኢንፎርሜሽኑ አይቬለለቢል መሆኑ ደግሞ ሌላው ከሩሻል ጥያቄ ነው. . ."* ይህንን ጉራማይሌ ቋንቋ ምሁሩ እንደሚከተለው ተርጉመውታል:-

*"አንድ ሰው ውሳኔ የሚሰጠው ወይንም የሚያደርገው ባገኘው መረጃ ላይ በመመሥረት ነው:: ስለዚህ የመረጃው መኖርና ያንን መረጃ ማግኘት መቻሉ ደግሞ በጣም ወሳኝ ነው:: በጉዳዩ ላይ ብዙ ውይይት ቢደረግበትም ችግሩ በሚገባ አልታየም:: ወይንም በቂ ትንታኔ አልተደረገበትም:: የመረጃ መኖር እንደ ትልቅ ወሳኝ ነው:: መረጃው ሊገኝ መቻሉ ደግሞ የበለጠ*





*አብይ ጉዳይ ነው::"* ሲሉ ገልፀውታል:: *(ማዕረጉ በዛብህ ጦቢያ ጋዜጣ 9ኛ ዓመት ቁጥር 22 ነሐሴ 30 ቀን 1994 ዓ.ም)*

በዚህ ሁኔታ ከመልዕክቱ ተዳፍኖ መቅረት የበለጠ ጉራማይሌነቱ ሁለቱንም ቋንቋዎች ለዛ አሣጥቷቸዋል:: በዚህ ምክንያትም በባለ ሥልጣናቱና በምሁራኑ መካከል እንግሊዘኛ ቋንቋን ቀላቅሎ ለመናገር ይደረግ የነበረው ፉክክር የተሟላ መልእክትን ለሕዝብ ለማስተላለፍ ሣይሆን <የኔ እንግሊዘኛ ይበልጣል> የሚሉ ይመስሉ ነበር:: እንዲያውም በሚያስደንቅ ሁኔታ ዋናው የመነጋገሪያ አጀንዳ እንግሊዘኛ ቋንቋን ቀላቅሎ መናገር ይመስል ነበር:: ይህም <ከኔ ወዲያ እንግሊዘኛ ቋንቋን አዋቂ የለም!> የሚያስመስል ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም::

ዛሬ እንግሊዘኛ ቋንቋ የቤተ መንግሥት የመነጋገሪያ ቋንቋ ሆኗል ማለት ይቻላል:: በሌላ በኩልም ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደሞከርኩት እንግሊዘኛ ቋንቋ ቀላቅሎ መናገር ያዋቂነት ምልክት እየሆነም መጥቷል:: የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት እንደምንም ብለው ተቸግረውና ተጨንቀው በንግግራቸው መሀከል አንድ ሁለት እንግሊዘኛ ቋንቋን ሠንቅረው ወይንም ቀላቅለው መናገር ካልቻሉ ሐሳባቸው የሚደመጥና ተቀባይነት የሚያገኝ አይመስላቸውም:: ይህንን ሁሉ ልብ ብለን ስንመለከተው ሁለት ነገሮች ያስጨንቁን ወይንም የቆጨን ይመስለኛል:: እነሱም:-

1. *በእንግሊዝ ቅኝ ሣንገዛ በመቅረታችን የቆጨን የምንመስል ወይንም:-*
2. *በእንግሊዝ ቅኝ ስንገዛ ቆይተን በቅርብ ቀን ነፃ የወጣንና ቋንቋችንን በመፈለግ ላይ ያለንና ያለ እንግሊዘኛ ቋንቋ ድጋፍ ሐሳባችንን አሟልተን መግለጽ የማንችል የምንመስል የዋሆች::*

ለዚህ እውነተኛነት አሥረጅ የሚሆኑን ሌላውን ሁሉ ትተን ሦስት ተጨባጭ አማኞችን ማጤኑ ብቻ በቂ ነው::

አንደኛው ትውልድ ቀራጭ የሆኑት ት/ቤቶች ከሙዋዕለ ህፃናት እስከ ዩኒቬርስቲ ኮሌጅ ድረስ ያሉት የግል ት/ቤቶች የተሰየሙት በእንግሊዘኛ ቋንቋ ነው:: በያካባቢያችሁ አይታችሁ መፍረድ ትችላላችሁ:: አንዳንድ የት/ቤቶችን ባለቤቶች ለማነጋገር ሞክሬለሁ:: የሰጡኝ መልስ "ስያሜቸው በእንግሊዘኛ ቋንቋ ካልሆነ ወላጆች ወደ ት/ቤቶቻችን ልጆቻቸውን አይልኩም" የሚል ነው:: ይህ ምን ያህል እውነት ነው? ጠይቁ:: ዋናው ቁም ነገር ግን "ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ገበያተኛ አይቀበለውም" እንዲሉ

የራሳችንን አቅልለን የሌሎችን አክብደን ተሸካሚ መሆናችን የሚያሣዝን ነው::

ሁለተኛው ማስረጃችን ደግሞ የፖሊስ ሠራዊት ማዕረግ በእንግሊዝ ቅኝ ሣንገዛ በመቅረታችን የቆጨን ለመሆናችን በቂ ማረጋገጫ ነው:: <ኮንስታንብል፣ ረዳት ሣጅን፣ ዋና ሣጅን፣ ኢንስፔክተር፣ ዋና ኢንስፔክተር፣ ኮማንደር. . .> እያለ ይቀጥላል:: ኢሕአዴግ ሁሉን ነገር የመኮረጅ በሽታ ተጠናውቶት እንጂ ነባሩ የማዕረግ ስያሜ ኋላ ቀር ሆኖ አይደለም:: እንደማዕረጉ ስያሜ የእንግሊዝን ዘመናዊ የምርመራ ጥበቤ3ስ አብሮ አምጥቶልን ይሆን? በምርመራ ወቅት ዘቅዝቆ መግረፍ፣ ጥፍሮችን መንቀል፣ በኤሌክትሪክ ማቃጠል ቀርተው ይሆን? ጠይቁ:: ለማንኛውም <ሳይቸግር ጤፍ ብድር ጦም ለማደር!> ነውና ልናፍር ይገባናል::

ሦስተኛው እማኞችን ደግሞ በሚቀጥለው ምዕራፍ በስፋት እንደምንመለከተው "የብሔር ብሔረሰቦችና የባንዲራ ቀን" እየተባለ ከ97 ዓ.ም ወዲህ በያመቱ የሚደለቀው ኢትዮጵያ ልክ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ኢሕአዴግ ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ነፃ ሲያወጣቸው ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋቸውንና ባህላቸውን አጎናፀፍኳችሁ እንደሚላቸው ሁሉ ባንዲራቸውንም ደርግ "ጨርቅ" ብሎ ትቢያ ላይ የጣላትን አንስቶ በክብር የሚያውለበልባት በማስመሰል የሚያስጨፍረው በቂ ማሣያ ነው:: ይኸ ሁሉ ዞሮ ዞሮ <እኛ ነን ለዚች አገር ተቆርቋሪዎች! እኛ ነን ታላቆች! ከኛ ወዲያ ለዚች አገር ላሣር ነው!> ለማለት ነው:: የሌሎችን በኮረጅን ቁጥር ግን የኛን እያጣን መሄዳችን በቅጡ ሊጤን ይገባል::

<><><>





# ብሔር ብሔረሰቦችና የባንዲራ ቀን!

ወደየ ብሔር ብሔረሰቦች ቀን ከመግባቴ በፊት አንድ አዛውንት ያጫወቱኝን ቁምነገር ባስቀድም ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያለው ሆኖ አግኝቸዋለሁ:: እንዲህ ነው:-

ያነዬው ልዑል መኮንን ሆስፒታል ያሁኑ ጥቁር አንበሳ ሥራው ተጠናቆ አልቆ አገልግሎት መሥጠት ሲጀምር አብዮቱ ይፈነዳና ነጬ ሕንፃ <ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል> ተብሎ ይቀየራል:: እናም አንድ አዛውንት ይታመሙና ከመንዝ መጥተው ይተኛሉ:: ልጃቸው ሊጠይቃቸው ይመጣና ከሕክምናው ይልቅ የሕንፃው ዘመናዊነት ያስደንቀዋል:: በሱ እምነት ያንን ዘመናዊ ሆስፒታል ባጭር ጊዜ ውስጥ የገነባው ደርግ ነው ብሎ አምኗል:: ምክንያቱም በወቅቱ የንጉሠ ነገሥቱ አድሃሪነት፣ የሥርዓቱ ሰውበላነት በፕሮፓጋንዳ ይሰበክ ስለነበር ልጅ ላባቱ በመቆጨት ዓይነት:-

*"አባባ ይህ አድሃሪ ንጉሥ ያሠሩት ሆስፒታል ቢሆን ኖሮ ከዚህ ገብተህ አትታከምም ነበር:: ተራማጁ ደርግ ተኝተህ እንድትታከም አደረገ" ሲላቸው ተቆጥተው:-*

*"ዝምበል አንተ! የማታውቀውን አትወሽክት! አለሌ አህያ የሚያናፋው ጌታው ከሠራው ጋጥ ውስጥ ሆኖ ነው!" አሉት አሉ::*

በመሠረቱ ከዳር ያሉትን ወደ መሀል፣ የመሀሎቹን ወደ ዳር እያመጡና እየወሰዱ ባህል ከባህል፣ ወግን ከወግ፣ ቋንቋን ከቋንቋ ማስተዋወቅና የልምድ ልውውጥ እያንዳንዳቸው ማግኘት ብቻ ሣይሆን የጠበቀ መቀራረብንም መፍጠር እንደሚችሉ አይጠረጠርም:: ይህም ይበል የሚባል እንጂ የሚያስነቅፍ አይደለም:: የሚያስነቅፈውና የሚያስነውረው ስብሰቦ መርዝ ከመርጨቱ ላይ ነው::

ኢሕአዴግ በሕዝብ ስም አንድ ነገር ለማድረግ ሲፈልግ አስቀድሞ የፖለቲካውን ትርፍ በማስላት ነው:: የብሔር ብሔረሰቦችን ቀን ለማክበር የተገደደውም እድሜ ለ97 ዓ.ም ምርጫና ለአሪጅናሉ ቅንጅት ብዙ ለውጦችን ለማየት ችለናል:: ሌላው ቢቀር ኢሕአዴግ ከሕዝብ ጉያ ለመሸጎጥ ሲል "ጨርቅ" ይላት የነበረችውን ባንዲራ ከጣለበት አንስቶ፣ የብሔር ብሔረሰቦችን ቀን ለማክበር ተገዷል:: ይህ አንዱ ሕዝባዊ ድል ነው:: ይህ ባይሆንማ ኖሮ እንደሚታወቀው የኢሕአዴግ መርሁና ሥርዓቱ

በዘር ላይ ተመሥርቶ ዜጎችን በጎሣ ከፋፍሎ በማፋጠጥ ረግጦ መግዛት ነው፡፡ ኢሕአዴግ በ97 ዓ.ም ሕዝብ ታምር ስላሳየው "የብሔረሰቦች ቀን" በማለት ይሰበሰባል፡፡ "ድመት መንኩሣ አመሏን አትረሣ" እንዲሉ ስብሰባ ግን ስለ ሰላም አያወራም፤ በጎነትን አይሰብክም፡፡ "ባለፈው ሥርዓት ቋንቋችሁ ተንቋሾና ተንቆ፣ ባህላችሁ ተደፍጥጦ. . ." እያለ ተራ የፖለቲካ ርካሽነትን ለማትረፍ ሲል መልሶ መርዝ ይረጫል፡፡

ወገን ልብ እንበል፤ ቋንቋቸው ከተንቋሸሸ፣ ባህላቸው ከተረገጠና በባህላቸው እንዳይኮሩ ጫናና ተፅዕኖ ከነበረባቸው እንዴት እስከ ዛሬ ጠብቀው አቆዩት? ይህንን ጠይቁ፡፡ ኢሕአዴግ ከየት ቆፍሮ አገኛቸው? ወይንስ ከ1983ዓ.ም ወዲህ ነፃ ካወጣቸው በኋላ እያንዳንዳቸው ቋንቋቸውን መናገር ችለው ይሆን? ጠይቁ፡፡

በመሠረቱ ኢሕአዴግ ከእውነትና ከታሪክ ጋር አይዋደድም እንጅ ሀቁ አያቶቻችንና አባቶቻችን ከቅኝ ገዥዎች ጋር እየተናነቁ አሣፍረው በመመለሳቸውና ነፃ አገር እስከነ ሙሉ ክብሯ ሲያስረክቡን እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ፣ ጎሣና ነገድ ቋንቋው፣ ባህሉ፣ ወጉ ተጠብቆ ቆይቷል፡፡ ይህ ባይሆንማ ኖሮ እንደ አፍሪካውያን ወንድሞቻችን ምናልባትም ዛሬ እንግሊዘኛ ወይንም ፈረንሣይኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከሚባሉት አገሮች ተርታ እንመደብ ነበር፡፡ ወይንም ደግሞ ጣሊያንን አባቶቻችን ረግጠው ባያበርሯት ኖሮ ዛሬ ጣሊያንኛ ተናጋሪዎች እንሆን ነበር፡፡

አባት አርበኞቻችን ደማቸውን አፍሰሰው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው የእያንዳንዱን ብሔረሰብ ቋንቋና ባህል ካገር ሙሉ ክብር ጋር ባስረከቡ መሬት እንደ ዳቦ እየቆራረሱ በሚሸጡና የባሕር በር በዘጉ ከፉ ትውልዶች አጥንታቸው እንደ አውራ ጎዳና ጠጠር ይፈጫል፡፡ የመንዜው አዛውንት እንዳሉት ጌታው ከሠራው ጋጥ ውስጥ ሆኖ እንደሚያናፋው አለሌ ዓይነት ያንድም ጎሣና ነገድ ቋንቋና ባህል ሣይጠፋና ሣይበረዝ <ቋንቋችሁና ባህላችሁ ተረግጦ!> እየተባለ መርዝ ይዘራል፡፡ ሌላው ቀርቶ የሩቆቹን ያድዋን፣ የማይጨውን ትተን በ1969 ዓ.ም 300 ሺ. ሚሊሺያ ሠራዊት ታጠቅ ጦር ሠፈር ገብቶ ሲሠለጥን እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ፣ ጎሳና ነገድ ተወክሏል፡፡ በመወከሉም እንደ ልብሳቸው ዥጉርጉርነት ቋንቋቸውም፣ ባህላቸውም፣ ወጋቸውም፣ መልካቸውም ዓመላቸውም ዥጉርጉር ነበር፡፡ ዓላማና ግባቸው ግን አንድ ሆኖ ያገርን ዳር ድንበር አስከብሮ ለትውልድ ማስረከብ ነበር፡፡ ሀፍረት የለሹ ሕወሓት ግን ኤርትራን ተዋግቶ አስገንጥሎ፣ የባሕር በር ዘግቶና አዘግቶ <የብሔር ብሔረሰቦች ቀን> እያለ ከ97ዓ.ም





ወዲህ በያመቱ ሲያከብር ዐይኖቹን በጨው ታጠበ፡፡ ሌላው ድራማ የባንዲራ ቀን ነው፡፡

በጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ "ጨርቅ" ተብላ ገና ከማለዳው ተንቋሻ የነበረችው ባንዲራችንም እድሜ ለ97 ዓ.ም ምርጫ በያመቱ ትከበራለች፡፡ ወደ ውስጥ ከመግባቴ በፊት ግን <ባንዲራ> የሚለውን ቃል መፍታት የሚያስፈልግ ይመስለኛል፡፡

<ባንዲራ> የሚለው ቃል ጣሊያንኛ ሲሆን አማርኛን የተቀላቀለው ካድዋ ጦርነት በኋላ ነበር፡፡ በኛ ቋንቋ <ዓላማ> የምንለው ነው፡፡ ዓላማ የግዕዝ ቃል ሲሆን በጥሬ ፍችው ያንድ ነገር የመዳረሻ ግብ ማለት ሲሆን ጥልቀት ሲኖረው ደግሞ ምልክት፣ መለያ፣ መታወቂያ እንደ ማለት ነው፡፡ በዚህ ፍችው ስንሄድ አንዲት አገር ከሌሎቹ አገሮች ተለይታ የምትታወቅበት ደምና ሥጋ የተላበሰበት ዓላማ (ባንዲራ) ይኖራታል፡፡ ኢትዮጵያም ከሌሎቹ አገራት ተለይታ የምትታወቅበት መለያ ምልክቷ አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ ቀለማት ናቸው፡፡ ለመሆኑ ገዥው ፓርቲ "ብሔራዊ የባንዲራ ቀን መከበር አለበት" ሲል ከምን ዓላማና ግብ ተነስቶ ነው? ምንስ አስገዳጅ ሁኔታ ገጥሞት ነው ከ97ዓ.ም በኋላ "የባንዲራ ቀን" ለማለት የተገደደው? ማንስ ዓላማውን (ባንዲራውን) ጠላ? ማንስ አንጓጠጠ? የቱ ዜጋስ ጨውና ስኳር ቋጠረባት? እነዚህን ጥያቄዎች ከጠየቃችሁ በኋላ እድሜ ለ97 ዓ.ም ምርጫ ብላችሁ በድጋሚ አመስግኑ፡፡

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዓላማው ቀናዒ ነው፡፡ ቀናዒ ከመሆኑ የተነሣም በባንዲራው ላይ የመጣን ጠላት ከመተናነቅ ወደ ኋላ ብሎ አያውቅም፡፡ ይሁን እንጂ ኢሕአዴግ ከ97 ዓ.ም ወዲህ መፈክሩን ነጥቆ ወይንም ገልብጦ "የባንዲራ ቀን" እያለ ለማክበር ሞክሯል፡፡ ያከባበር ደንብም አውጥቷል፡፡

ኢሕአዴግ የ97 ዓ.ም ምርጫ ሕዝባዊ ማዕበል ከፉኛ ሲንጠው የሕዝብ ልጅ መስሎ ለመታየትና ሕዝብ የወደደውን የወደደ፣ ያከበረውን ያከበረ ለመምሰል ከወሰዳቸው ርምጃዎች መሀከል አንዱ ለባንዲራ ክብር መስጠት ነበር፡፡ ይህንንም ሲያደርግ "ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፎችን" እንዲሉ ጥቅሙንም ባለመርሳት ነው፡፡ በመሆኑም ሦስት መሠረታዊ ዓላማዎችን ሠንቆ ነው፡፡

አንደኛውና ዋናው ግቡ ከፍ ብዬ ለመግለፅ እንደሞከርኩት በ97 ዓ.ም ሕዝቡ ከፉ አሳሳት ስለሳተው በሱ አገላለፅ "ብጫ ካርድ አሣይቶኛል፤ ቀይ

ካርድ ሣያሣየኝ ወደ ሕዝቡ መሸንጥ አለብኝ” የሚል ነው:: ወደ ሕዝብ ለመሸንጥ ደግሞ ሕወሓት ፋኖ በነበረበት ጊዜ “ስኳርና ጨው ይቋጥርባት ነበር” የተባለችውን ባንዲራ ከጣለበት አንስቶ የሕዝብ ልጆች አሲዞ ከሕዝብ ፊት አስቁሞ እያውለበለበ ማዘመር ነው::

ሁለተኛው ግቡ ከባንዲራው ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ ታሳቢ ያደረገ ነው:: የዚህ ገቢ ደግሞ በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: ለነገሩ ትንሽም ብትሆን ኢሕአዴግ ገንዘብና ነገርን አይንቅም:: በመሆኑም ጠ/ሚንስትር መለስ “ጨርቅ” እንዳሏት ኢሕአዴግ እንደጨርቅ ባይነት እየቀደደና እየቆራረጠ በያመቱ ይቸበችባል:: የታክሲ ሹፌሮችና ባለሎንቺናዎች ሁሉ ቅጥባጣ መልኩ መሪ ጨብጠው፣ ልክ እንደ ሀገር መሪ እያውለበለቡ ሲከንፉ ማየት የተለመደ ሆኗል:: በልማዱ መሪዎች ብቻ ነበሩ ባንዲራ እያውለበለቡ የሚሄዱት:: አምባሳደሮችም በተመደቡበት አገር ከመኪናቸው ፊት ለፊት ሰቅለው ከቦታ ወደ ቦታ ሲዘዋወሩ ባንዲራ እያውለበለቡ እንዲሄዱ የፕሮቶኮሉ ሕግ ይፈቅድላቸዋል:: የባንዲራ ቀን መከበር ከተጀመረ ወዲህ ግን ሹፌሩ ሁሉ ያገር መሪ ሆኗል::

በመሠረቱ መቸገር ሆኖ እንጂ ሕወሓት/ኢሕአዴግ በምንም መመዘኛ የኢትዮጵያን ሕዝብ ስለባንዲራ ፍቅርና ክብር ሊያስተምር አይችልም:: የሞራል ብቃትም የለውም:: ካንጀቱ ከሆነም በመጀመሪያ በስህተቱ ተፀፅቶ ሕዝብን ይቅርታ መጠየቅ ነበረበት:: ይህ በሌለበት ሁኔታ ግን በደፈናው “የባንዲራ ቀን ላክብር” ማለት የድብብቆሽ ጨዋታ ነው የሚሆነው::

የኢሕአዴግ ሦስተኛው ግቡ ከባንዲራው ላይ ያለውን በሰማያዊ መደብ ብጫ ቀለም ያለበትን የኮከብ ምልክት አርማውን በሕዝቡ አእምሮ ውስጥ ለማስረፅ ነው:: ይህ ከምሩ የሚታገልለት ነው:: ያለመታደል ጉዳይ ሆኖ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቋሚ የሆነ ብሔራዊ አርማና መዝሙር የለውም:: የዚህ ምክንያቱ በሕዝብ ያልተመረጡና ውክልና የሌላቸው አምባገነን መሪዎች በጉልበታቸው ከላዩ ላይ ስለሚቀመጡበትና ከሕዝብ ስሜትና ፍላጎት ውጭ የራሳቸውን አምባገነንነት የሚያንፀባርቅ በዘፈቀደ ስለሚያስቀምጡ ነው:: በመሆኑም አርማዎቻቸውም ሆኑ መዝሙሮቻቸው ዘመን ተሻጋሪዎች አይደሉም:: ከነሱ ውድቀት ጋር አብረው ይወድቃሉ:: የቀዳማዊ ኃይለሥላሴና የደርግን አስታውሶ ማለፉ በቂ ነው:: የኢሕአዴግ አርማና መዝሙር ነገ ስላለመፍረሱ ምንም ዓይነት ዋስትና የለም:: የሚገርመው ግን ክቡር ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ “ጨርቅ” እንዳሏት በሷው ተጠቅልለው ወደ መቃብር መውረዳቸው ነው:: ይህ አስገራሚ ግጥምጥሞሽ ነው::





# “ልማታዊ መንግሥት!”

ከ97 ዓ.ም ወዲህ የኢሕአዴግ አንዱ ሽመንሙን ቋንቋ “ልማታዊ መንግሥት ነኝ” በማለት ራሱን በራሱ ማንቆላጰሱ ነው::

በመሠረቱ አንዲት አገር ለማች ወይንም አደገች የምትባለው በቃላት ሽንገላ ወይንም ኩሸት ሣይሆን ተጨባጩ እውነታ ወደ አገር ውስጥ የምታስገባቸው ሸቀጦች ወደ ውጭ ከምታስወጣቸው ከእጥፍ በታች ያነሱ እንደሆነ ነው:: ከዚህ ሀቅ ስንነሳ ኢትዮጵያ የዚህ ግልባጩን ነች:: ወደ ውስጥ የምታስገባቸው ሸቀጦች ቢያንስ ዘጠና ፐርሰንት ናቸው ማለት ይቻላል:: ወደ ውጭ የምትልካቸው ሸቀጦች የቆዳ ውጤቶች፣ ቡና የቅባት እህሎች እንዲሁም ጥራጥሬ የመሣሰሉት ዋንኞቹ ሲሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ሚዛን ባይደፋም በከፍተኛ ደረጃ የሚጮህለት ያበባ ምርት ነው::

ይህንን ያበባ ምርት ሕዝቡ “የኢሕአዴግ ኢንዱስትሪ?” በማለት ያሽሟጥጠዋል:: ይህ ያበባ ምርትም የጥቂቶች መንደላቀቂያ ሆኖ እንደሆነ እንጂ እንደሚጮህለት የውጭ ምንዛሪን የሚቀርፍ ወይንም የሚያቃልል አይደለም:: እንዲያውም ገበሬውን ከርሻ መሬቱና የከብቶቹን መዋያ ሜዳዎች ያሣጣና ያፈናቀለ፣ መሬቱንም ላንድኛው በኬሚካል ሊያመክን እንደሚችል የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ:: ስለዚህ ኢሕአዴግ “ልማታዊ መንግሥት ነኝ” እያለ ራሱን መካቡ ከምን የመነጨ ነው? ብለን ብንጠይቅ አንድ አባት ለልጃቸው ያወጡላት ስም ዓይነት ይሆንብናል::

አንድ አዛውንት የልጃቸው ጥቁረት የምጣድ ቂጥ ትመስላለች:: ስሟን ግን <ብርቱካን> አሏት:: “መልከ ጥፉን በስም ይከሱ” እንዲሉ መሆኑ ነው:: እናም ሰው በልጅቷ ጥቁረትና በስሟ መካከል ያለውን ልዩነት በማጤን አዛውንቱን “የብርቱካንን ቀለም ወይንም መልክ አያውቁም” በማለት ይተቿቸዋል:: ኢሕአዴግም ራሱን በራሱ “ልማታዊ መንግሥት ነኝ” ሲል የልማትን ትሩፋት ምን ያህል ያውቃል? የሚል ጥያቄን ያስነሳል:: በጠኔ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በያመቱ በሚረግፉባት አገር “ልማታዊ መንግሥት ነኝ” ብሎ ራስን ማሞካሸት እንደ መቀለድም ይቆጠራል::

ርግጥ ነው ኢሕአዴግ “ልማታዊ መንግሥት ነኝ” ሲል በገጠር የልማቱን ጋጋታ በቴሌቪዥን እያሣየ ገበሬው “ሚሊየነር” እየተባለ አረንጓዴ ቆብ ከራሱ ላይ እያስቀመጠ (እያስደፋ) በጅምላ ሲሸልም ያሳያል:: በከተማ

ደግሞ የመንገዶችን መሠራት፣ የፎቆችን ግንባታ፣ ዜጎች የኮንደሚኒየም ቤት ባለቤት መሆናቸውን፣ የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ግንባታው በብዙሃን መገናኛዎች ያዥጎደጉዱታል:: "ሺ ቢታለብ ያው ከገሌ" እንዳለችው ድመት ከችጋር ግን መላቀቅ አልቻልንም:: በፕሮፓጋንዳ ብቻ ጠግበን እናድራለን::

ዜጎች ከዚሁ አዲስ አበባ "ቁምሣ" (ቁርስና ምሳ) ካንድ ላይ ባምስት ሰዓት እየተመገቡ ባሉበት ሁኔታና ይህም አላዋጣቸው ብሎ "ቁምራ" (ቁርስ፣ ምሣና ራት) በቀን አንድ ጊዜ የሦስቱን ጊዜያት መመዝቢያ አቀራርበው ከሚበሉበት ጊዜ ላይ ደርሰው ባይናችን እያየን አንዳንዶቻችንም የችግሩ ቀጥታ ተካፋይ ሆነን እያለን በምን አይነት ሚዛን ነው ኢሕአዴግ "ልማታዊ መንግሥት ነኝ" ሊል የሚችለው? ራሱ ጠግቦ ስላደረ? ጠይቁ::

ሁልጊዜ የኢሕአዴግ መንግሥት "ልማታዊ መንግሥት ነኝ" ሲል ወይንም በሌላ ምክንያትም ቢሆን ራሱን የሚያነፃፅረው ወደ ኋላ ብዙ ዓመታት ተመልሶ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ከደርግ አገዛዝ ጋር በማነፃፀር ነው:: ካምና ዘንድሮ የተሻለ መሆን እንዳለበት እንኳን የሚገነዘብ መንግሥት አይደለም:: የመልኳ ጥቁረትና የስሟ ብጫነት ዓይነት ነው::

ቷናንት ከቅኝ ግዛት የተላቀቀችው ጎረቤታችን ኬንያ ዛሬ የትና የት ጥላን ሄዳለች:: ሌላው ቀርቶ የምንበላው ማጣታችን ብቻ ሣይሆን ብሶታችንና መራባችንን እንኳን እንዳንተነፍስ በመታፈናችን የኢትዮጵያ ስደተኞች ኬንያን ሲያጣብቡ የኬንያ ስደተኞች ግን ከኛ አገር ስለመኖራቸው አናውቅም::

መንግሥት "ልማታዊ" ከሆነ ሕዝብ ጠግቧል፣ አገር ለምታለች ማለት ነው:: አገር ከለማችና ካደገች ደግሞ ሥራ ተትረፍርፏል ማለት ነው:: የምናየው ግን የተገላቢጦሹን ነው:: ወጣቱ፣ ጎልማሳው፣ አዛውንቱ፣ ሴት ወንዱ ሥራና ቁራሽ ፍለጋ ወደ ባዕዳን አገራት የሚጎርፈው ለምንድ ነው? ይህንን ሀቅስ መካድ ይቻላል? አገር እጅግ ኃላፊነት በጎደላቸው ሙሰኞች እጅ ላይ ወድቃ ሕዝብ የቁም ስቃይ እያየ መንግሥት በዚህ ተግባሩ ሊያፍርና ራሱን ሊፈትሽ ሲገባው ለችግሩ ሰለባ ለሆነው ሕዝብ መልሶ "ልማታዊ ነኝ" ማለት ከንቀት በስተቀር ሌላ ምን ፍች ሊሠጠው ይችላል?

ኢሕአዴግ በመንግሥትነቱ መንገድ መሥራትና አንዳንድ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መዘርጋት እንዳለበት እንኳን በቅጡ የተገነዘበ አይመስልም:: አንዳንድ ነገሮችን በሠራ ቁጥር እንደ ህፃን ልጅ አላፊ አግዳሚው "ኢሕአዴግዬ!" እያለ እንዲያሞካሸው ይፈልጋል::





## ንፅፅር

የኢህአዴግ መንግሥት 21 ዓመታት ተጉዞ ያልተላቀቀው ነገር ቢኖር ራሱን ከተራ ኩሹት ማላቀቅ አለመቻሉ ነው:: ራሱን ከፍ ከፍ ባደረገ ቁጥርም ወደ ኋላ ተራምዶ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴንና የደርግን ሥርዓቶች ከመኮነን ጀምሮ ቅንጣት ሥራ እንዳልተሠራ አድርጎ ዜሮ ላይ ያስቀምጣል:: ራሱን ግን «ልማታዊ መንግሥት ነኝ » ሲል ይከባል:: ለማንኛውም ከሁለቱ ያለፉ መንግስታት መብለጡን ወይንም ልማታዊ መንግስት መሆኑን በንፅፅር እያየን ሕሊናዊ ፍርድ መስጠት እንድንችል እነሆ:-

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በ43 ዓመታት ያገዛዝ ዘመናቸው ከውጭ ብርና ርዳታ ያገኙት የገንዘብ መጠን 250 ሚሊዮን ያሜሪካን ዶላር ሲሆን ባመት 625 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ብቻ ነበር:: የደርግ መንግሥት በበኩሉ በ17 ዓመታት የግዛት ዘመኑ ከውጭ ያገኘው የብድርና የርዳታ መጠን 4 ቢሊዮን ዶላር ወይንም 8.2 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ነበር:: ይህ በመሆኑም በንጉሠ ነገሥቱም ሆነ በደርግ ጊዜ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የመሠረተ ልማት አውታሮች ተዘርግተዋል፤ ይህንን ሀቅ ግን ኢሕአዴግ አይቀበልም::

ባንፃሩ የኢሕአዴግ መንግሥት በነዚህ 21 ዓመታት ውስጥ ከውጭ ብድርና ርዳታ ያገኘው የገንዘብ መጠን 50 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን በኢትዮጵያ ብር ስንመነዝረው 3 ትሪሊዮን 250 ቢሊዮን 500 ሚሊዮን ገደማ ይሆናል:: የዓመት ፈሰሱ 162 ቢሊዮን 500 ሚሊዮን ብር ነው:: ይኼ ሁሉ ገንዘብ ከሥራ ላይ ውሏል አልዋለም? ሌላ ጥያቄ ሆኖ ልናተኩርበት የሚገባን ቁምነገር ግን በውጭ አገር ወይንም ባበዳሪ አገራት ተጽዕኖ ሥር የወደቅን መሆናችንን ነው:: እንግዲህ ኢህአዴግ «ልማታዊ መንግስት ነኝ» የሚለን 3 ትሪሊዮን ብር ዕዳ ተሸክሞ ነው::

በሌላ በኩልም በግብር አሰባሰብ ስንሄድ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴም ሆነ በደርግ ያገዛዝ ዘመን ዜጎች የሚጠበቅባቸውን ግብር ከመክፈል ውጭ ሌላ እዳ እንዲከፍሉ አይገደዱም ነበር:: ይህንን በተመለከተ ባንድ ወቅት ያዲስ አበባ ነጋዴዎች <ግብር በዛብን ይቀነስልን> በሚል ሱቆቻቸውንና ሆቴሎቻቸውን ላንድ ቀን ዘግተው ሰላማዊ ጩኸት ባሰሙበት ወቅት ስለዚሁ ጉዳይ ጠ/ሚንስትር መለስ ተጠይቀው ሲመልሱ:-

«ያዲስ አበባ ሕዝብ እስከ ዛሬ ድረስ ግብር ከፍሎ አያውቅም» ሲሉ ስላቅ ዓይነት መልስ ሰጥተው ነበር:: በዚህ ውጤት አራት ኪሎ ሸረጋ

ሆቴልን ጨምሮ ሌሎች በርካታ የንግድ ተቋማት ከንግዱ ዓለም እንደ ተሰናበቱ ቀርተዋል፡፡ ይህም የኢሕአዴግ መንግሥት የዜጎችን አቤቱታና ጥያቄ ባግባቡ አዳምጦ የመመለስ ወይንም የማስተናገድ ብቃት የሌለው መሆኑን ያሳያል፡፡ ኢሕአዴግ ሁልጊዜ ችግሮችን የሚፈታው በጉልበት ነው፡፡ ዛሬም ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጋር ለረጅም ጊዜ ያፋጠጠው ይኸው በጉልበቱ የማምለክ ባህሪው ነው፡፡

እንግዲህ ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት በንጉሡም ሆነ በደርግ ጊዜ ዜጎች ግብር በሚከፍሉበት ጉዳይ ብቻ ይከፍሉ ነበር እንጂ በተረፈ ነፃ ነበሩ፡፡ ባንፃሩ «በዴሞክራቱ መንግሥት» የግብሩ ዓይነትና ያሰባሰቡ ስልት ተዘርዝሮ አያልቅም፡፡ ዛሬ በንጉሡ ጊዜ ማዘጋጃ ቤት ያሠራቸው የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች በነፃ ሽንትን ከፍሎ መውጣት አይቻልም፡፡ በቅድሚያ ካርኒ መቁረጥ የግድ ነው፡፡ በዚህ ላይ ተሰልፎ ወረፋ መጠበቁ እፍኛን ያፈነዳል፡፡ በያካባቢው አዳዲስ መፀዳጃ ቤቶች ባለመሠራታቸውም ዜጎች ከብራቸውን ጥለው በየጥጋጥጉ በመፀዳዳታቸው ከተማዋ እንደ ዋና መዲናነቷ ልታገኝ የሚገባትን ፅዳትና ውበት ማጣቷ ልንደብቀው የማንችለው ሀቅ ነው፡፡

አንድ ሰሞን አበራ ሞላ (ስለሺ መኩሪያ) ሠርቶ ማሳያዎችን በመሥራት ብዙ ጥረቶችን አድርጎ ነበር፡፡ ከ97 ዓ.ም ወዲህ ግን የት እንደገባ በግሌ አላውቅም፡፡ ያም ሆነ ይህ መንግሥታችን በፕሮፓጋንዳ «ጽዱ አዲስ አበባ!» እያለ ይኳሽናል፡፡ ጽዳቷንና ውበቷን ግን በያካባቢያችን እያየን መፍረድ እንችላለን፡፡

በዘመነ ኢሕአዴግ የ10 ሣንቲም ሻሂ በብርና በሁለት ብር ጠጥቶ መውጣት አይቻልም፡፡ ካሽ ሬጅስትር አጥምዶ ወይንም አስቀምጦ የሻሂውን ዋጋ 15 ከመቶ (ቫት) ጨምሮ መክፈል የግድ ነው፡፡ ሻሂ ቅጠልና ስኳር በገፍ የምታመርት አገር ካንድ ብርጭቆ ወይንም ስኒ ላይ የካሽ ሬጅስተር አጥምዶ ቫት የሚቆርጥን መንግስት በቃላት ለመግለጽ ቃል ያጥራል፡፡

የኢሕአዴግን የግብር አሰባሰብ ስግብግብነት በተመለከተ አንዳንድ አዛውንቶች በምፀት ሲገልፁ «ኢሕአዴግ ወደፊት ባልና ሚስት ግብረሥጋ በፈፀሙ ቁጥር ቫት ለመቅረጥ እንዲያመቸው መዝግቦ የሚያቆየው ካሽ ሬጅስተር ከራስጌያቸው ማስቀመጥ እንዲችል ለተወካዮች ም/ቤት አቅርቦ ሕግ ሳያስረቅቅ አይቀርም» ሲሉ ሥጋታቸውን በቁም ነገር ይገልፃሉ፡፡ አዛውንቶቹ ይህንን ሥጋታቸውን ሲገልፁም ከባዶ ተነስተው አይደለም፡፡ ተጨባጭ መረጃዎችን ይዘው ወይንም ጨብጠው ነው፡፡ እንዲህ ነው፡-





በ2003 ዓ.ም ድንገቴ የግብር አሰባሰብ ደንብ በማውጣት እግረኞች በዜብራ መንገድ ማቋረጥ ካልቻሉ፣ በሌላ አነጋገር እግረኞች ተንደርድረው ወይንም ተሽከርክረው መኪናን ገጭተው ከጠረመሱ ወይንም በሹፌሩ ላይ ጉዳት ካደረሱ 60 ብር እንዲቀጡ የሚል በተወካዮች ምክር ቤት ባንድ አርፋጃ አስቀርቦ በማፀደቅ ሥራ ላይ በማዋል ዜጎችን በምክንያት የሚቀርጥ መንግስት ነው ኢሕአዴግ፡፡ እኔ ራሴ የዚህ ቅጣት ሰለባ ነኝ፡፡ የዜብራ መንገድ አላቋረጥከም ተብዬ ካሣንቺስ ፖሊስ ጣቢያ ተወስጄ ስልክ ደውዬ ብሩ እስከሚመጣልኝ ድረስ ለ2 ሰዓት ያህል የትራፊክ ደንብ ከጣሱ ሚኒባሶች ጋር ታግቼ ቆይቼ 60 ብሩን ከፍዬ ልለቀቅ ችያለሁ፡፡ እንደኔው ታግተው ይንጫጩ የነበሩ ዜጎችን አይቻለሁ፡፡ ይህ የእግረኞች ቅጣት ዛሬ የቆመ የመሰለው 22 ማዞሪያ ያለው የትራፊክ ፖሊስ ሕንፃ ተሠርቶ በማለቁ ይመስለኛል፡፡

እንግዲህ የኢሕአዴግ መንግሥት ከውጭ በብድርና በርዳታ ከሚያገኘው ሌላ ከፍ ብዬ ለመግለፅ እንደሞከርኩት በመጠንም ሆነ ባይነት ከገጠር እስከ ከተማ እጅግ ግዙፍ የሆነ ግብር አሰባሰብ ስልት ቀይሶ ከመንገድ ዳር ተቀምጣ በፀሐይ እየተቃጠለች ቲማቲምና ሽንኩርት ከምትቸረችረዋ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የንግድ ተቋማት ድረስ ታክስ እያግበሰበሰ አንዳንድ የማስመሰያ ፈሰስ ወይንም በትርፍራው መንገዶችንና በዓመቱ መጨረሻ የሚሰነጣጠቁ ሕንፃዎችን ቢሠራ ምንድን ነው ሊያስፎክረው የሚችለው? ከዚህ ላይ ሌላም ጥያቄ ማንሳት ይቻላል፡፡ ለመሆኑ መንገዶቹን፣ድልድዮቹንና ግድቦቹን የነማን ኩባንያዎች ናቸው የሚሠሯቸው? ይህንን አጥብቃችሁ ጠይቁ፡፡

በከተማም ሆነ በገጠር የሚገነቡትን ግንባታዎች የሚሠሩት ሰባ ከመቶውን የኢሕአዴግ ኩባንያዎች መሆናቸው ያደባባይ ሚስጢር ነው፡፡ ስለዚህ በብድርም ሆነ በርዳታ የሚገኘው ገንዘብ እንዲሁም ከሕዝብ በግብር መልክ የሚሰበሰበው ገንዘብ ከቀኝ ኪስ ወደ ግራ ኪስ የሚገባ መሆኑን ጣታቸውን የሚጠቡ ህፃናት ሳይቀሩ ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ ቀሪዎቹን ሰላሳ ከመቶውንም ቢሆን ያለጨረታ በቻይና ኩባንያዎች የሚሠሩ ናቸው፡፡ እነዚህም ጭንብሎች እንጂ ከኢሕአዴግ ከንድ ነፃ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩልም የሲሚንቶ፣ የፌሮ (ባጠቃላይ የግንባታ ዕቃዎች) በነዚህ 21 ዓመታት ለምንድን ነው ዋጋቸው አይነኬ የሆኑት? ብሎ መጠየቅም ተገቢ ነው፡፡ የዚህ ምስጢሩ የግንባታ እቃዎች አስመጭና አከፋፋዮች የኢሕአዴግ ወኪሎች ወይንም ኢሕአዴግ ራሱ የንግዱ ክፍል ኢኮኖሚ ዋና ተዋናይ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚሁ የዋጋ ንረት ጋር በተያያዘም ጤፍ የምታመርት አገር ጤፍስ ለምን ተወደደ? ብሎ መጠየቅም ተገቢ ነው፡፡

በ83 ዓ.ም መቶ ኪሎ ጤፍ ከ 40 - 50 ብር ይሸጥ የነበረው ዛሬ ከ1300 -1800 ብር ደርሷል። ኪሎ ሥጋ በ83 ዓ.ም ከ3 - 5 ብር ይሸጥ የነበረው ዛሬ ከ140 - 160 ብር ደርሷል። ለምን? ጠይቁ። የዚህ ሚስጢርም ጂዳ፣ ሮም፣ ለንደን፣ ቶሮንቶ፣ ዋሽንግተን ዲሲና ኒዮርክ የተከፈቱት ግዙፍ ግዙፍ ሬስቶራንቶች የነማን እንደሆኑ ጠይቆ ሀቁን ማወቅ ይቻላል። እንግዲህ ይህንን ሁሉ ጉድ ሕዝብ አያውቅም ብሎ «ልማታዊ መንግስት ነኝ»እያሉ ማሽሟጠጥ ሕዝብን ዝቅ አድርጎ እንደ መመልከት ይቆጠራል። ሕዝብ ያያል፣ሕዝብ ይሰማል፣ሕዝብ ጠንቅቆ ያውቃል። ያንድ መልካም ሕዝባዊ መንግሥት ዐይንና ጆሮው ሕዝብ ነበር። ይህ ግን ዛሬ የተገላቢጦሽ ሆኗል።

"ኢሕአዴግ 21 ዓመታት ተጉዞ አንዳንድ ያረጁ መንገዶችን መጠገኑንና አዲያዲስ መሥመሮችን መዘርጋቱን፣ እንዲሁም ባዲስ አበባና በክልል ዋና ዋና ከተሞች ፎቆችን ማቆሙን እንደ ትልቅ ነገር በመቁጠር በፕሮፓጋንዳ <ትልቅ መንግሥት> ለመባል ይታትራል። ከሠራና አገር ብልጽጋ፣ ሕዝብ ራሱን ችሎ ሲያድር ሥራው በራሱ ትልቅ መንግሥት እንደሚያስብለው እንኳን ግንዛቤ የለውም። በጩጬትና በማስመሰል የተለከፈ ጉደኛ መንግሥት ነው። ለመሆኑ በመንግሥትነቱ ምን ሊሠራ ኖሯል? ያንድ መንግሥትስ ኃላፊነቱና ተግባሩ ምን ሊሆን ነው? መንገድ መሥራቱ፣ ፎቅ መገንባቱ፣ የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ግድቦችን መገደቡ አፋኝነቱንና ፀረ-ሰላምነቱንስ ያካክስለታል? በየቀኑ የተራበ አውሬ ይብላኝ እያለ አገሩን እየጣለ የሚሰደደው ወጣት አገሩን ጠልቶ አይደለምኮ። የሥርዓቱ ከጨካኝነት በድህነት እንኳን እንዲኖር ስላላስቻለው ነው።

በመሠረቱ ኢሕአዴግ አንዳንድ ግንባታዎችን በመገንባቱ "ልማታዊ መንግሥት" የሚያስብለው ከሆነና በዚህ ተግባሩም እንዲሞካሽ ፍላጎቱ ከሆነ ኢጣሊያምኮ የሊማሊሙን ገደል ደረማምሳ ትውልድ ሊገነባው ቀርቶ ሊያስበው የማይችለውን መንገድ ሠርታልናለች። ከዚህ አዲስ አበባ በቅርብ ርቀት የሚገኘውን የጣርማ በርን ተራራ ቦርቡራ በመብሳት የውስጥ ለውስጥ መንገድ ገንብታልናለች። ጥቂት የማይባሉ ሕንፃዎችንም በዋና ዋና ከተሞች ገንብታለች። እሷም ታዲያ "ልማታዊ መንግሥት" ተብላ ስትገዛን መኖር ነበረባት? አያቶቻችንና አባቶቻችን እሷን ወግተው ማባረራቸው ስህተት ነበር? ይህንን በተመለከተ ያንድነት ፓርቲ የሥራ አስፈፃሚ አባልና የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊ አቶ ተክሌ በቀለ እንዲህ ሲል ሀቁን አስቀምጦታል:-

*"ሕዝብ በዳቦ ነፃነቱን የሚቀይር ቢሆን ኖሮ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን መግዛት በቻለች ነበር . . ." (ፍኖተ ነፃነት ቅፅ 2 ቁጥር 16 ማክሰኞ ህዳር 5 ቀን 2004 ዓ.ም)*







*አቶ ተክሌ በቀለ*

*ያንድነት ፓርቲ የሥራ አስፈፃሚ አባልና የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊ*

የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ቁሣዊ ልማትና መንፈሣዊ ልማት የማይነጣጠሉ መሆናቸውን በቅጡ የተገነዘቡት አይመስሉም። ቁሣዊ ልማት ብቻውን ልማት ሊሆን አይችልም። በሌላ አባባል ፎቅ ቢገተር፣ መንገድ ቢሠራ ያለ አእምሮ ነፃነት ወይንም መንፈሳዊ ልማት ፋይዳ የለውም። ዋናውና ወሳኙ ኃይል የአእምሮ ነፃነት ነው። ሕዝብ እንዳይናገር፣ ስለመብቱ እንዳይጠይቅ፣ ስግብግብና ኃላፊነት የጎደላቸው ባለሥልጣናት ካንድም ሁለት ሦስት ፎቆችን እየገነቡ ባንፃሩ የድሃ ጎጆዎችን ባፍራሽ ግብረ ኃይል እያፈረሱና ዜጎችን እያሰደዱ <ፎቅ እየሠራሁላችሁ ነኝ፤ ኮንዶሚኒየም እየገነባሁላችሁ ነኝ፤ ዓባይን እየገደብኩላችሁ ነኝ፤>ማለት በጭራሽ የትም አያደርስም። በመጀመሪያ መቅደም ያለበት ወይንም አብሮ መሄድ ያለበት ዋነኛውና ፈጣሪው ኃይል አእምሮ ስለሆነ አእምሮ ነፃ መሆን አለበት። አእምሮ ነፃ እስካልሆነ ድረስ ግን የተገነባው ሁሉ ይፈርሳል፤ ይናዳል።

የጥንት ባሪያኮ ጌታው የሚያሠራው ሆዱን እየሞላ ነው። ነፃነት ግን የለውም። ምናልባትም በቤት ውስጥ ካሉት እንስሳት መሀከል እንደ አንዱ ነው የሚቆጠረው። ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብም በገመድ ተቆራኝተው ለሽያጭ ወደ ገበያ እንደሚነዱ በጎች ወይንም ፍየሎች አንድ ላምስት ተጠርንፎ ነፃነቱን ተገፎ አምጣ ያሉትን ከልጆቹ አፍ እየመነጨቀ እየሰጠ፣ ሁን ያሉትን



አቶ ተከሌ በቀለ

እየሆነ፣ ባል ሚስቱን፣ ሚስት ባሏን እስበሳቸው የሚመራረጁበት ክፉ ሥርዓት ውስጥ ገብተን እየዛቀጥን ባለንበት ወቅት ኢሕአዴግ "ልማታዊ መንግሥት ነኝ፣ ዴሞክራት ነኝ!" ሲል ዐይኑን በናጫ አሸ፡፡

ወደ ከተማ ስንመጣ ደግሞ <ስቪል ሠረባንቱን >ኢሕአዴግ "ያይኑ ቀለም አላማረኝም" ባለ ጊዜ ጥፋት ፈልጎ ወይንም ፈጥሮ ከሥራው ያባርረዋል፡፡ ወይንም ደግሞ የመሥራት ሞራሉን በሚገል መልኩ ከደረጃ ዝቅ ያደርገዋል፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ጡረታን አሥከብሮ ጡረታ መውጣት እንደ መታደል የሚቆጠርባት አገር ሆናለች፡፡

በመሠረቱ ያረጁ መንገዶችን መጠገንና አዲስ አበባ ውስጥ አንድ ቀለበት መንገድ መሥራትና ትላልቅ ፎቆችን መገንባት ከሌሎቹ አገራት ጋር ስናነፃፅረው በመንግሥት ደረጃ ሊያመፃድቅና ሊያኩራራ ባልተገባ ነበር፡፡ ለዚያውምኮ የሚገነቡት ፎቆች የነማናቸው? በየመንገዱ የሚፈነጩት ኮብራዎችና ላንድ ክሩዘሮች የነማን እንደሆኑ ሕዝቡ ጠንቅቆ ያውቃቸዋል፡፡ ተጎታቾቹ፣ ቡቴዎቹ፣ በዋና ዋና ከተሞች የሚፏልሉት አይሲዞዎችና ሀይገር ባሶች፣ እንዲሁም በሌሊት ጨለማን እየሠነጠቁ የሚበሩት ዘመናዊ እስካይ ባሶችና ሰላም ባሶች የነማናቸው? መንገዶቹ ለነዚህ ተሽከርካሪዎች ደህንነት ሲባል ቢሠሩና ቢጠገኑ ምን ያስደንቃል? የሚያስደንቀውና የሚያስገርመው ለቅኝ ገዥዎች ያልተንበረከከ ጀግና ሕዝብ በምርኮኞች እጅ ላይ ወድቆ፣ ነፃነቱንና መብቱን እንደ ቆዳ ተገፎ ለዘመናዊ ባርነት መጋለጡ ነው፡፡

"መንግሥታችን ልማታዊ" ከሆነ ለምን እንራባለን? ለምንስ ዜጎች አገራቸውን እየጣሉ በጅምላ ይሰደዳሉ? ለምንስ እጅግ ተዋርደው ያረቦች ገረድ ለመሆን ይመርጣሉ? እነዚህን ጥያቄዎች ጠይቁ፡፡

ባንድ ወቅት በደቡብ ኢትዮጵያ ጠኔ ገብቶ ከኢትዮጵያ አልፎ የዓለም የመገናኛ ብዙሃን መነጋገሪያ ሆኖ በነበረበት ወቅት የኢሕአዴግ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጠ/ሚንስትር መለስን ጨምሮ "ድርቅ እንጂ ርሃብ አልገባም" እያሉ ያስተባብሉ ነበር፡፡ ይህንን በተመለከተና ስለርሃብና ስለ ጠኔ ልዩነት እንዲያስረዱኝ ዶ/ር ኃይሉ አርአያን ጠይቄቸው የሰጡኝ መልስ፡-

*"ይኽ መንግሥት አንድም ጊዜ ስለሚሠራው ስህተት አምኖ አያውቅም፡፡ ‹ድርቅ እንጂ ርሃብ የለም› ሲል ‹ድርቅ የተፈጥሮ ክስተት በመሆኑ እኔን አያስጠይቀኝም› ለማለት ነው፡፡ ድርቅም ቢሆን ባግባቡ መፍታት ካልቻለ ወይንም በወቅቱ ለተጎዱት ወገኖች ካልተደረሰላቸው ሊያስጠይቅ ይችላል፡፡ በፍፁም ከተጠያቂነት ማምለጥ አይቻልም"* ካሉኝ በኋላ ቀጠል አድርገው፡-





*"ርሃብ (Hunger) ስንል ማንኛውም ሰው የሚመገበው ሳያጣ በሆነ ምክንያት ወይንም በሥራ ተጠምዶ የመመገቢያ ጊዜ አጥቶ ሊሆን ይችላል፤ ሲቆይ ወይንም ሲውል የሚሰማው ስሜት ርሃብ ይባላል፡፡*

*"ጠኔ (Famine) ማለት ግን ከርሃብ በፍፁም የተለየ ነው፡፡ የሚላስ የሚቀመስ ጨርሶ የሌለበት ሁኔታ ሲፈጠርና ቅጠሎችና ሳሮች ሳይቀሩ በድርቅ ሳቢያ ሲየሩ በዚህ ወቅት ጠኔ ይከሰታል፡፡ ጠኔ ባገራችን ብዙ ጊዜ ተከስቷል፡፡ ብዙ ሕዝብም ፈጅቷል፡፡ ጠኔ የሰውነትን ቅርፅ ሳይቀር ያዛባል፡፡ ጠኔ ሰዎችን ብቻ ሳይሆን እንስሳትንም አጥንታቸውን አስቀርቶ የሚፈጅ ነው"* ሲሉ ምሁሩ ተርከውልኛል።

እንግዲህ ሀቁ ይኸ ሆኖ እያለ፤ የኢሕአዴግ መሬትን እንደጣቃ እየቀደደ እየሸጠ "ልማታዊ መንግሥት ነኝ" ሲል ከምን አንፃር ይሆን? ጠይቁ፡፡



*አንጋፋው ምሁር ዶ/ር ኃይሉ አርአየ*

## የመሬት ቅርምት

የዘመኑን የመሬት ቅርመት በተመለከተ አቶ ስንታየሁ በቀለ የተባሉ ምሁር <አዲሱ የቅኝ ግዛት ጅማሬ> በሚል ርእስ እንዲህ ይገልፁታል፡-

". . .ኢሕአዴግ ሀገርን አይደለም 5 ሚሊዮን የፓርቲውን አባላት በፓርቲው አባልነት የሚያቆይ አቅም ሊኖረው እንደማይችል እሙን ነው፡፡ አሁን ያሉት አምባገነኖች በምዕራባውያን <ስፖንሰርነት> በሕዝብ ላይ



አንጋፋው ምሁር ዶ/ር ኃይሉ አርአያ

የተጫኑ መርጎች ናቸው. . .” ይሏቸዋል፡፡ አቶ ስንታየሁ በቀለ ጽሑፋቸውን በመቀጠል “የኢሕአዴግ ‹የመሬት ስጦታ› ለምን?” በማለት ይጠይቁና አያይዘው “ከ97 ዓ.ም በኋላ በኢሕአዴ ከተተገበሩት አስከፊ ፖሊሲዎች አንዱ ሰፋፊ የርሻ መሬቶችን ለውጭ ባለሀብቶች ማከፋፈል ነው፡፡ በቅርቡ የዓለም ባንክ ይፋ የሆነ የጥናት ውጤት እንዳሣየው ከሆነ በኢትዮጵያ ከ1996-1999 ዓ.ም መካከል 1.2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ ለኢንቬስተሮች ተሠጥቷል” ይሉናል፡፡ አሁንም ጽሐፋቸውን በመቀጠል፡-

“ኢሕአዴግ የሕዝብ ውክልና ሣይኖረው ኤርትራን አሳልፎ ሠጥቷል፡፡ አገራችን በዓለም ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላት ግን ደግሞ ወደብ የሌላት ሀገር አድርጓታል፡፡ ይግባኝ በሌለው ፍ/ቤት በኢትዮጵያና በኤርትራ ደንበር ሠፋፊ የኢትዮጵያ መሬቶች ለኤርትራ እንዲሠጡ ፈቅዷል፡፡ በጎንደር በኩል ለሱዳኖች አስረክቧል፡፡ አሁን ደግሞ ለ99 ዓመት ለኢንቬስትሜንት በውል ስምምነት ጋምቤላን የሚያክል ክልል እንዳናጣ ያሰጋል?” ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡

*(ፍኖተ ነፃነት ቅፅ 1 ቁጥር 5 ረቡእ ነሐሴ 25 ቀን 2003 ዓ.ም)*

የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪው መምህር ደረጀ መላኩ በበኩላቸው <የኢትዮጵያ ገበሬዎች እጣ ፈንታና የመሬት ቅርምቱ!> በሚል ጥንታዊ ጽሑፋቸው “ኢትዮጵያን በባንቱ ስታይዜሽን ያገዛዝ ዘይቤ ጣሯን ያበዛባት ሥርዓት አሁን አለ፡፡ ለብዙ ሺ ዓመታት የባሕር በር የነበራትን ታላቅ አገር መግቢያና መውጫዋ እንዲዘጋ ዋናውን ሚና የተጫወተው የለየለት አምባገነን መንግሥት ዛሬ ደግሞ ፍፁም አስደንጋጭና ህልውናችንን የሚፈታተን ነገር ሠርቷል፡፡ ድንግል መሬቷን በዓለም እጅግ ርካሽ በሆነ ዋጋ ለተቀራማቾች አስረክቧል!” ካሉን በኋላ ተቀራማቾቹ ምን ያህል ሄክታር መሬት እንደ ተቀራመቱ በሠንጠረዥ አስደግፈው አቅርበዋል፡፡ እነሆ፡-

| አገዛዙ ለደንበር ዘለልና ለኢትዮጵያውያን የሠጠው የመሬት መጠን | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የባለ ሀብቱ ስም | የመጣበት ሀገር | የመሬት ቅርምት የተካሄደበት ክልል | የሚያለማው የሰብል ዓይነት | የመሬት ስፋት በሄክታር | ምር መራ |
| 1 | ካራቱሪ የርሻ ኩባንያ | ሕንድ | ጋምቤላ | ፓል አይልና ጥራጥሬ | 100,000 | |
| 2 | ሺፓርጂፓሎንጂ | ሕንድ | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | ለነዳጅ የሚያገለግል | 50,000 | |





| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ተክልና የምግብ ዘይት | | |
| 3 | ቢ ኤች አ (BHO) | ሕንድ | ጋምቤላ | የፓል ዘይት ጥራጥሬ | 27,000 | |
| 4 | ሩች ያኩሪ አተር ኢንዱስትሪ | ሕንድ | ጋምቤላ | አኩሪ አት | 25,000 | |
| 5 | ሲ ኤል ሲ (CLC) ስፔንቴክስ ኢንዱስትሪ | ሕንድ | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | ጥጥ | 25,000 | |
| 6 | ሁናን ዲፋንቶያን የርሻ ካምፓኒ | ቻይና | ጋምቤላ | የሸንኮራ አገዳ | 25,000 | |
| 7 | አዳማ | ሕንድ | ደ. ኢትዮጵያ | ጥጥ | 18,516 | |
| 8 | ኋይት ፊልድ | ሕንድ | ደ. ኢትዮጵያ | ጥጥ | 10,000 | |
| 9 | ሳውዲ የርሻ ኮከብ | ሣውዲ አረቢያ | አልዊሮ ጋምቤላ | ስንዴ በቆሎ ሩዝ | 10,000 | |
| 10 | ዳንኤል የርሻ ልማት ድርጅት | ትውልደ ኢትዮጵያዊ | ደ. ኢትዮጵያ | ጥጥና ጥራጥሬ | 5,000 | |
| 11 | ሜላ የርሻ ልማት | ኢትዮጵያ | ደ. ኢትዮጵያ | የጥጥ ተክል | 5,000 | |
| 12 | አከሰስ ካፒታል ሰርቪስ | ኢትዮጵያ | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | የአጣን ዛፍና ጥራጥሬ | 5,000 | |
| 13 | ትራኮን የንግድ ድርጅት | ኢትዮጵያ | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | የጥጥ ተክል | 5,000 | |
| 14 | ዶ/ር ታሚ ህደጉ | ትውልደ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዊ | ደ. ኢትዮጵያ | የጥጥ ተክል ሲድ | 5,000 | |
| 15 | ብሩ ሆይድ (buoyed) | ኢትዮጵያ | ቤኒሻንጉል ጉምዝ | የጥጥ ተክልና አኩሪ አተር | 5,000 | |
| 16 | ሲሲ. የርሻ ልማት ድርጅት | ኢትዮጵያ | ደቡብ | የጥጥ ተክል | 4,003 | |
| 17 | ቤንዲታ ሀርቨስት የግል ኩባንያ | ሕንድ | ጋምቤላ | ሻይ ቅጠልና የነዳጅ ተክል | 3,012 | |
| 18 | ራህዋ (Rahwa) | ኢትዮጵያ | ደ. ኢትዮጵያ | ጥጥ፣ ጥራጥሬ | 3000 | |
| 19 | Asky (የርሻ ልማት) | ኢትዮጵያ | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | ጥጥ | 3000 | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2<br>0 | ፀጋዬ ደምዝ | ትውለደ ኢትዮጵያዊ | ደ ኢትዮጵያ | ጥጥ | 1000 | |
| 21 | ፊታ (key stone) | ትውልደ ኢትዮጵያዊ | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | Horticultral crop | 431 | |

ጠቅላላ ድምር = 347,099 ሄክታር

እንግዲህ ይህ 347,099 ሄክታር መሬት ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉልና ደቡብ ክልል ከፊሉን ያህል ነው:: ባማራ፣ በኦሮሚያና የአሞን ሽለቆ ተከትሎ የተሠጠውን የመሬት መጠን አይጨምርም:: እንደገና ባዲስ አበባ ዙሪያና አቅራቢያ ላበባ ምርት የተሰጠውን ሁሉ ሲካተት ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው 1.2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በባዕዳን እጅ ገብቷል ማለት እንችላለን:: ምን ቀረን ታዲያ ወገን? ጠይቁ::

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ በሕዝብ ብዛት ካፍሪካ የሦስተኛ ደረጃን ከግብፅና ከናይጀሪያ ቀጥላ ትይዛለች:: ታዲያ ይህን ያህል የሕዝብ ቁጥር የሠፈረባት አገር፣ የሥራ አጡ ቁጥር ከእለት ወደ እለት እያደገ ባለበት ሁኔታና ያለ ዘመናዊ የወሊድ መቆጣጠሪያ የሚወለዱ ህፃናት ባሉባት አገር ያላንዳች መቆርቆርና ኃላፊነት በጎደለው ሁኔታ ድንግል መሬቷን ለባዕዳን ቱጃሮች በነፃ የመሥጠት ያህል ማደል በምን ቃል መግለጽ ይቻላል? ለ99 ዓመት ውል እየገቡ እጅግ በተጣደፈና በሽሚያ ዜጎችን ከመኗሪያ ቀያቸው እያፈናቀሉ ባዕዳንን ማስፈር ምን ዓይነት የከፋት ልክ ማጣት ነው? መልስ ሰጭ ባታገኙም ጠይቁ::

## "ያልጠረጠረ ተመነጠረ!"

"ያልጠረጠረ ተመነጠረ" እንዲሉ አቶ ግራማ ካሣ የተባሉ ሌላው ምሁር በበኩላቸው ስጋታቸውን እንደሚከተለው ይገልፃሉ:-

"ሱልጣን ኢብራሂም አሠብን ለኢጣሊያኖች እንደ ሸጠ ሁሉ አገራችንን እኛ በማናውቀው መንገድ ለውጭ አገር ዜጎች እየተቸበቸበ ይሆን?" በማለት ይጠይቁና "ካመታት በኋላ ኢትዮጵያ የሕንዶችና የቻይናዎች አገር ትሆን ይሆን?" ሲሉ በስጋት እንደገና ይጠይቃሉ:: እውነትም ያሰጋል:: ኢሕአዴግ እንደ ሱልጣን ኢብራሂም ለሕንዶችና ለቻይናውያን በጋምቤላና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ከሕዝብ እውቅናና ውክልና ውጭ የመሠረት ድንጋይ እያስቀመጠላቸው ይሆን? ጠይቁ::





እንደሚታወቀው እነዚህ አገሮች የዓለምን ሕዝብ ቢያንስ 1/4ኛውን ቁጥር የሚሸፍኑ ናቸው:: እድሜ ለኢሕአዴግ የራሱን ዜጎች እያሰደደ ከተጨናነቀ ኑሮ እየገላገላቸው ነው::

አቶ ግርማ ካሣ ለባዕዳን ኢንቬስተሮች የተቸረውን የመሬት መጠን በንፅፅር እንዲህ ይገልፁታል "ወደ 4 ሚሊዮን ሕዝብ የሚኖርባት ያዲስ አበባ ከተማ ስፋት 54,000 ሄክታር አካባቢ ይሆናል:: በሌላ አባባል ያዲስ አበባን አምስት ጊዜ የሚያህል መሬት ለውጭ አገር ዜጎች ተሠጥቷል ማለት ነው" በማለት ቁጭታቸውን ከገለፁ በኋላ ቀጥለው "በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን በከንቱ ያለቀባት የባድመ ይገባኛል ጦርነት ነው:: የባድመ ከተማ ከዳር እስከ ዳር ካንድ ኪሎ ሜትር አትበልጥም:: በመሆኑም ስፋቷ ከ100 ሄክታር ያነሰ ነው ማለት ይቻላል::ታዲያ ከ100 ሄክታር ላነሰ መሬት ያን ሁሉ ንብረትና እልቂት የተከሰከሰው፣ ያ ሁሉደምየፈሰሰው ለውጭ አገር ዜጎች የተሠጠው 2,500,000 ሄክታር መሬት በስፋቱ 2,500 ባድማዎች እንደተሰጡ የሚያስቆጥር ነው:: ላንድ ባድማ ያን ያህል መስዋእትነት ሲከፈል2,500 ባድማዎች በቀላሉ ሲሰጡ ማየት እጅግ በጣም የሚያሳዝን ነው" በማለት ቁጭታቸውንበምሬት ገልፀዋል:: *(ፍኖተ ነፃነት ቅፅ 2 ቁጥር 10 ማክሰኞ መስከረም 16 ቀን 2004 ዓ.ም)*

እንግዲህ ኢሕአዴግ አውቆም ይሁን ሣያውቅ ይህንን የመሰለ ስህተት እየሠራ ነው "ልማታዊ መንግሥት ነኝ" በማለት ራሱን በራሱ የሚከበው:: ምናልባት የሕንዶቹንና የቻይናዎችን ልማት ተስፋ ሠንቆ ይሆን? ዋነው ነገር ወደፊት ምን መደረግ አለበት? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ መልስ ማግኘት የሚገባው ጉዳይ ነው::

ኢሕአዴግ ይህን የመሠለ ትውልድን የሚጎዳ ጥፋት ሲፈፅም ዜጎች እያዩና እያወቁ ወይንም እየሰሙ በቸልታ የመመልከታቸው ጉዳይ ከኢሕአዴግ ጥፋት የበለጠ አሣሣቢና አነጋጋሪ እየሆነ መጥቷል:: በተለይ የምሁራን ገለልተኛ መሆን ኢሕአዴግን በጭፍኑ እንዲጓዝና ሕዝብን እንዲንቅ አስችሎታል:: ይህን የኢሕአዴግ የጭፍንና የእብሪት ጉዞ ለመግታት ወይንም ጨርሶ ለማስወገድ ተቀራርቦ መወቃቀስ ተገቢና አስፈላጊ በመሆኑ ለይደር የሚተው ጉዳይ አይደለም:: ተቀራርቦ ለመወቃቀስ ደግሞ አስቀድሞ ብሔራዊ መግባባት መፍጠርና ባገር ጉዳይ ዙሪያ ለመነጋገር ቅድሚያ ከምሁራን የሚጠበቅ ተግባር ነው:: የምሁራን ችላ ባይነት ባገርና በሕዝብ ላይ በደል መፈፀም ነውና ከወቀሣ ማምለጥ አይቻልም::

<><><>

# ኑ - እንወቃቀስ!

*የባሩድ ጪስ ሲያሸት የኖረ ፋኖ የሰላም አየር እንደ በርበሬ ያስነጥሰዋል! (ይከነክነዋል!)*

## ብሔራዊ ርቅ

ርቅ አረቀ፣ የተወላገደውን እንዳይሠበር አድርጎ አቃና፣ አስተካከለ ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲሆን በማህበረሰቡ ፍች ስንሄድ ደግሞ ርቅ ያወቃቅሳል፣ ያስማማል፣ እውነት ያናግራል። በመሆኑም የሰላም ሥንቅ ነው።

ብሔራዊ ርቅ ስንልስ ምን ማለታችን ነው? አገር አቀፍ ሰላም ይሰፈን ማለታችን ነው። ከፍ ብዬ ለመጠቆም እንደሞከርኩት ርቅ ያወቃቅሳል፤ ያበጡ ቁስሎችን ያፈርጣል፤ ወይንም ያፈነዳል። ብጉንጁ ከፋ የጉያ ወይንም የብብት እባጭ ነው። ፈርጦ መግሉ ካልወጣ በስተቀር የሰላም እንቅልፍ አያስተኛም። ስቃዩ ከፋ ነው። የማህበረሰብ ቁስል ደግሞ ከዚህ የከፋ ነው። አንዱ ጎሳ ወይንም ብሔረሰብ በሌላው ብሔረሰብ አኩርፏል። ከዚህም በከፋ መልኩ አመርቅዟል። ይህ በየጉያው ያበጠ ብጉንጅ ፈርጦ ሊሽር የሚችለው ብሔራዊ መግባባት በመጀመሪያ ተፈጥሮ በመጨረሻ ተወቃቅሶ ብሔራዊ ርቅ ማውረድ ሲቻል ብቻ ነው።

ብሔራዊ ርቅ ያስፈልጋል ስንልም ከባዶ ተነስተን አይደለም። በነዚህ 21 ዓመታት ውስጥ ብቻ ዜጎች እስበሳቸው ተጋለዋል፤ ተዳምተዋል፤ ተቆሳስለዋል . . . በዘመነ ደርግም በነጭ ሽብርና በቀይ ሽብር ከወዲህም ሆነ ከወዲያ ያለቀው ወጣት ያንዲት እናት ልጆች በመሆናቸው የወገኖቻቸው ቁስል ፈርጦ ሊሽር የሚችለው ላንዱ ወገን የሰማዕታት ሙዚየም በመሥራት ሣይሆን ተቀራርቦ በመወቃቀስ ቁስልን ማፍረጥ ሲቻል ብቻ ነው።

ደርግ ካገር መከላከሉ ሌላ በተለያዩ ምክንያቶች ወይንም "በፀረ - አብዮተኞች ስም" መጠነ ሠፊ ደም አፍስሷል። የሕዝብ ያልሆነ የባዕድ ሥርዓት አምጥቶ በመጫን ንብረት በመውረስ ከሕዝብ ጋር ተቋስሏል። የብዙዎቹን ተስፋ አጨልሟል።

የሕወሓት ፋኖዎች ኢሕአፓን ከትግራይ ተራሮች ጨፍጭፈው አባረዋል። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ልክ እንደ ደርግ ሁሉ





አብረዋቸው የተሰለፉትንም በልተዋል። "አማራ ገዳይ!" እያሉ ፋኖ ነበሩበት ብቻ ሣይሆን መንግሥት ከሆኑ በኋላ እንኳን ያማራ ዜጎችን ነጥለው ባልተቋረጠ መልኩ መኗሪያ በማሳጣት አጥቅተዋል፤ እያጠቁም ናቸው። እንደ ብሥራት አማረ የተጠናወታቸው ደግሞ ወደ ኋላ እጅግ ርቀው ነገሥታቱን በተለይም አፄ ምኒልክን እያንቋሸሹ አፅማቸውን ዘልፈዋል። እነዚህ ሁሉ ክፉ የብብት እባጮች ናቸው። ተወቃቅሰን ካልፈረጡ በስተቀር የትውልድ ጠንቆች ናቸው። አንዱ ዘር ወርቅ ሌላው ዘር ጨርቅና ልፍስፍስ እየተባለ እንዴት አብሮ መኖር ይቻላል? እንወቃቀስ።

ኦነግ የኦሮሞን ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጥሎ እገነጥላለሁ በሚል መጠነ ሠፊ ደም አፍስሷል። የኦሮሞ ልጆችንም አስቀጥፏል። ዛሬም ቢሆን "ያህያ ባል ከጅብ አያድን" እንዲሉ የኦሮሞ ልጆችን ኑሮ እያጨለመ ይገኛል።

በመኤሶንና በኢሕአፓ መሀከል ብዙ ደም ፈሷል፤ ሕይወትም ጠፍቷል፤ በኦጋዴን አካባቢ በሚንቀሳቀሰው (ኦብነግ) ምክንያት የሶማሌ ዜጎቻችን እጅግ በከፋ መልኩ ሰለባ ሆነዋል። በነዚህ ሁሉ ሳቢያ የፈሰሰው ደም እንዲደርቅ ከተፈለገ መወቃቀስ ያስፈልገናል።

ኦነግና የኦሮሞ ምሁራን ባማራ ላይ ጥቅል የሆነ ጥላቻና የቆየ ቁርሾ እንዳላቸው በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲገልፁ ቆይተዋል። መግለፅ ብቻ ሳይሆን መጠነ ሰፊ ደምም አፍስሰዋል። ባፄ ምኒልክ ጊዜ ግፍ ተፈፅሞብናል በሚል ተራ ብቀላ ውስጥ መግባታቸውን መደበቅም ሆነ መካድ አይቻልም። ይህ እባጫቸው እንዲፈርጥ በቅድሚያ ብሔራዊ መግባባት ተፈጥሮ ከዚያም በመቀራረብ መነጋገርና እውነቱን ነቅሶ በማውጣት መወቃቀስ የግድ ይላል። መናናቅና በጥላቻ የጎሪጥ መተያየቱ ለቀጣይ ትውልድ ሕይወት የሚበጅ አይሆንም።

አማራው ከሚፈፀምበት ሁለንተናዊ ግፍ የተነሳ በትግሬኛ ተናጋሪ ወገኖቻችን ላይ ሕወሓት በሚረጨው ያልተቋረጠ ፕሮፓጋንዳ የተነሣ አመርቅዟል። ይህንን ሀቅ መሸፋፈን አይቻልም። የተጋዳላይ ብሥራትን መጽሐፍ ያነበበ ሰው በፍፁም እንቅልፍ አይተኛም። የጄኔራል ሳሞራ የኑስና ያቆ መለስ በየጊዜው ያስተላለፏቸው መርዛማ ንግግሮች በቸልታ የሚታለፉ አይደሉም። የሚያነጋግሩና የሚያወቃቅሱ ናቸው።

እውነት እንነጋገር ካልን የሕወሓት ተጋዳላዮች በተለይም ተጋዳላይ ብሥራት አማረ "በፍኖተ-ገድል" መጽሐፉ እንደሚነግረን ከሆነ

ትምህርታቸውን እያቋረጡ በረሃ የገቡት ዘውዳዊውን ፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት ለመጣል ብቻ ሣይሆን አማራን ለማጥፋት ጭምር እንደሆነ በማያሻማ መልኩ አስቀምጦታል:: ለማስታወስ ያህል በድጋሚ እጠቅሰዋለሁ::

*"ታላቁ የትግራይ ብሔራዊ ንቅናቄ ተፀንሶ የተወለደው ብልሹ በሆነው ያማራዊነት ፍልስፍና ተግባር ምክንያት እንደሆነ ርግጠኛ መሆን እንችላለን:: ለትግራይ ሕዝብ ትግል ዋናው ምክንያት ኢትዮጵያን ባማራዊነት ለመጥመቅ የተደረገው ጥረት ማስረጃ ነበር . . ." (ፍኖተ ገድል ገጽ 31)*

ወገን፤ የሕወሐት ተጋዳላዮች አማራን ለማጥፋት መንቀሳቀሳቸውና በረሃ መግባታቸው ከዚህ የበለጠ ማስረጃና ማረጋገጫ ፍለጋ ቁፋሮ መግባት አይጠበቅብንም:: ይህንን የብሥራት አማረን የተጠናወተ ሐስተሳሰብም ከትንሽ እስከ ትልቅ የሕወሐት አባላት መቶ በመቶ የሚጋሩት ነው:: አቶ መለስ ዜናዊና ጄኔራል ሳሞራ የኑስ የተናገሯቸውን መለስ ብሎ ማጤን ተገቢ ነው::

ሌላው አበበ ተሰማ የተባለ ተጋዳላይ ኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ ያለ ስለዚሁ ብሥራት አማረ ስለጻፈው መጽሐፍ በጀርባ ገጽ አድናቆቱን ሲገልፅ እንዲህ ይለናል:-

*"በትግራይ ሕዝብ ዘመናዊ ትግል ከነበሩ አንጋፋ ታጋዮች አንዱ በመሆኔ ብሥራት አማረ ወቅታዊና ታሪካዊ መጽሐፍ ላይ አስተያየት ለመሥጠት እንድችል ያደረገኛል . . ."* ይላል:: ይህ ማለትም የብሥራት አማረን መርዛማ ሐስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ የሚጋራ መሆኑን ነው የምንረዳው:: የሆነ ሆኖ እነዚህ እባጮች ሁሉ በወቅቱ ተቀራርቦ በመወቃቀስ መፍረጥ አለባቸው:: ለነገ የሚተውና መቆየት የሌለባቸው ናቸው::

የሩቁን ትተን እንኳን ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ ባገሪቱ ውስጥ ሰላም አልሰፈነም:: በጋምቤላ፣ በሲዳሞ፣ በቦረና፣ በጉጂ፣ ባፋር፣ በኦሮሚያ የተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች፣ ባሰሳ . . . ደም እንደ ጅረት ፈሷል፤ መንደሮች ጋይተዋል፤ እህል በሌለባት አገር ክምሮች ተቃጥለዋል፤ ቤተክርስቲያናትና መስጊዶች ነደዋል፤ እንስሳት ታርደዋል፤ ተዘርፈዋል፤ ከሞትና ከመቁሰል የተረፉ ዜጎች አገር ጥለው ተሰደዋል፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በግንቦት ሰባት ስም ዜጎች እየታደኑ የእስር ሰለባ እየሆኑ ናቸው:: የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ጋዜጠኞች "ባሸባሪነት ስም" የእድሜ ልክ እስራት እየተሜነባቸው ናቸው:: እነዚህን ቁስሎች ሁሉ ይዞ አብሮ በሰላም መዓዝ እንዴት ይቻላል?





እባጮቹ ሁሉ ተወቃቅሰን ማፍረጥ ካልቻልን መዘዙ ለትውልድ ጠንቅ ነው:: በመሆኑም ኢሕአዴጋውያን ኑ እንወቃቀስ!

የርቁ ፋይዳ ኢሕአዴግን ጭምር ነፃ ለማውጣት ነው:: አንዱን አስደስቶ ሌላውን ለማስከፋት ወይንም የከፋት እዳ ተሸካሚ ለማድረግ አይደለም:: እንዳደጉት አገራት ለማደግ ከፈለግን ተወቃቅሰን ብሔራዊ ርቅ ማውረድ የግድ ይለናል:: ትልቁ ካሳም ተቀራርቦ ተወያይቶና ተወቃቅሶ እውነት ከመጨበጡ ላይ ነው:: ከእውነት የበለጠ ደግሞ ያበጠ ቁስልን የሚያፈርጥ የለም:: ቢያንስ ለብሔራዊ ርቅ መንገድ ለመጥረግ ጊዜ ሳይሰጠው ብሔራዊ መግባባት መፍጠር የግድ ነው:: በዚህ በኩል ምሁራን ሰፊ ድርሻ አላቸው:: ከታሪክ ተወቃሽነት ለመዳን የሚችሉት ሁሉ የማድረግ ታሪካዊ ኃላፊነት አለባቸው::

ላንጋፋው ምሁር ለዶ/ር ኃይሉ አርአያ ብሔራዊ ርቅን በተመለከተ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ሰፋ ያለ መልስ ሰጥተውኛል:-

*"በርካታ ብሔረሰቦች በሚገኙባት ኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ባለፈ ታሪካቸው ተከባብረው የመኖራቸውን ያህል ግጭቶችም ነበሩ:: በግጭቶቹ ሂደት ያንዳንድ ብሔረሰቦች አባላት በሌሎች ብሔረሰቦች አባላት ላይ በደል ተፈፅሞብናል ባዮች ናቸው :: ይህ በመሆኑም ባሁኑ ጊዜ ያንዳንድ ብሔረሰቦች አባላት በታሪክ ወደ ኋላ በመመለስ፣ ‹አባቶቻችሁ ባባቶቻችን ላይ ይህን በደል አደረሱ፣ ያን ግፍ ፈፀሙ› በመባባል ቂምና በቀል የመቀስቀስ ጤናማ ባልሆነ ዐይን የመተያየትና ልብ ለልብ ያለመቀራረብ ምልክቶች እየታዩ ናቸው:: እነዚህ ምልክቶችም ለሕዝቡ አንድነት መላላት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ሥጋት አለ:: ይህ ሥጋት ጊዜ ሳይሰጠው መወገድ ይኖርበታል:: ባለፈ ትውልድ አባላት የተፈፀሙ በደሎችና ግፎች ለዛሬ ትውልድ አባላት አብሮና ተባብሮ ለመኖር እንቅፋት መሆን የለበትም::*

*"በርግጥ ባለፉት ትውልዶች የተፈፀሙ በደሎችና ግፎች የታሪካችን አካሎች ናቸውና እንዳልነበሩ መካድ ወይንም ተሸፋፍነው መታለፍ የለባቸውም:: እውነተኛ ባህሪያቸው ታውቆ ተመዝግበውና ተተንትነው ለታሪክ መቀመጥ አለባቸው:: ከዚያ በኋላ በግልጽና በሰላማዊ ውይይት በበደሎቹና በግፎቹ ላይ መግባባት ከተደረሰ በኋላ ብሔራዊ ርቀሰላም ማውረድ ይቻላል::*

*"በመሠረቱ በብሔረሰቦች መሀከል ግጭት መፈጠሩና መጎዳዳቱ በኢትዮጵያ ብቻ የተከሰተ አዲስ ነገር አይደለም:: ብዙ ብሔረሰቦችን*

*በውስጣቸው በያዙ በርካታ የዓለማችን ሀገሮች ውስጥ ብዙ ፍጭት ተካሂዶ፣ ብዙ በደልና ጉዳት ደርሶ፣ በመጨረሻ ግን አንድነት ፈጥረው፣ ብሔራዊ ርቀሰላም አውርደውና የዴሞክራሲ ሥርዓት ገንብተው አገራቸውን የዕድገትና የብልጽግና ተምሳሌቶች እንደሆኑ ከታሪክ እንረዳለን:: ስለዚህ ከራሳችንም ሆነ ከቀረው ዓለም ሕዝብ መልካም ልምድና ተሞክሮ ወስደን ባዲስ መንፈስ ተባብሮ በመሥራት ራሳችንን ከጋራ ድህነትና ኋላ ቀርነት ማላቀቅና የራሳችንን ሕይወት አስተካክለን ለመጭው ትውልድ ጤናማ ኅብረተሰብ ማስረከብ ነው::"* የጥቁሱ መጨረሻ:: ሌሎቻችሁስ ምን ትላላችሁ? ጠይቁ::

ብሔራዊ መግባባትንና ብሔራዊ ርቅን በተመለከተ ከምሁሮቻችን ብዙ ቁምነገሮች ይጠበቃሉና ያስተማራችሁን ሕዝብ ስቃይ እኩል የመካፈል ግዴታ አላባችሁ:: እኔን ምን አገባኝ በሚል የዋህነት በችልታ የሚታለፍበት ወቅት ላይ አይደለም ያለነው::

ቀደም ባሉት ጊዜያት ስለብሔራዊ ርቅ ሲነሳ አቶ መለስ "ማንና ማን ተጣልተዋል?" እያሉ ያፌዙ ነበር:: የደርጉ ቁንጮ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምም ስለርቅ ሲጠየቁ "ይህ የባልና ሚስት ጠብ አይደለም" እያሉ ይመልሱ ነበር:: ርቅ እንዴት ይጠላል? ስለምስ ይፈራል? ጠይቁ::

ርቅና ሰላም የሚፈሩና የሚጠሉ የባሩድ ጪስ ሲያሸቱ የኖሩ ፋኖዎች ብቻ ናቸው:: የሰላም አየር እንደ በርበሬ ይከነክናቸዋል፣ ያስነጥሳቸዋል::

ስለብሔራዊ ርቅ ጉዳይ አንስተን ካንድ አዛውንት ጋር ስናወጋ "ርቅ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: ርቅን የሚፈሩ የዲያቢሎስ አጋፋሪዎች ብቻ ናቸው" ነበር ያሉኝ:: ይህ እውነት ነው:: ከፋት የተጠናወታቸው ካልሆኑ በስተቀር ርቅ አውርዶ ሰላም አስፍኖ ወደ ልማት መግባት እንዴት ሊፈራና ሊጠላ ይችላል? ርቅን ፈርቶ በሙት መንፈስ አገር ማመስስ እንዴት ይቻላል? ጠይቁ:: የሙት ራእይስ እንዴት መውረስ ይቻላል?

በመሠረቱ ኢሕአዴግ በሙት መንፈስ አገር ማመሱንና የከፋት ታሪክ መደለዙን አቁሞ ለብሔራዊ መግባባትና ብሎም ለብሔራዊ ርቀሰላም እጆቹን ዘርግቶ ያዲስ ታሪክ ባለቤት መሆን አለበት:: በሕዝቦች ደም ስሚንቶ እያቦካና አጥንታቸውን አርማታ እያደረገ ፎቅ መገንባቱ የትም እንደማያደርሰው ልብ ሊል ይገባዋል::

በቅርቡ ጠ/ሚንስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ እንደገለጹት ከሆነ አቶ መለስ ከ50 ጊዜ በላይ ኤርትራን ለመታረቅ ወይንም ይቅር እንባባል ለማለት





ጠይቀዋል:: በመሠረተ ሐሳቡ ስለርቅ ማሰባቸው አይነቀፉም:: የሚነቀፉት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሆን ግን አንድም ጊዜ ስለሰላም ሲናገሩ ተደምጠው አይታወቁም:: የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደናቁ ወደ ማይቀረው ዓለም መሄዳቸው በእጅጉ ያሣዝናል::

አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝም ያቶ መለስን ራእይ እንዳለ ሳይሸራረፍ ለማስቀጠል ቃለ መሀላ የፈፀሙ ስለሆነ ከኤርትራ ጋር አቶ መለስ ጀምረውት የነበረውን ድርድር እንደሚቀጥሉበትም ነግረውናል:: በሚመሩት ሕዝብ መሀል ግን ብሶት እንደ እሳተ ገሞራ እየተንተከተከ ያለ መሆኑን የተረዱትም፣ ያወቁትም አይመስሉም::

ኢሕአዴግ ዛሬ እንዳይመሽበት ይጨነቃል እንጂ የነገው ትውልድ ድቅድቅ ጨለማ ቢውጠው ጉዳዩ አይደለም:: ስለዚህ በዓለም ዙሪያ የተበተናችሁ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ለብሔራዊ ርቀሰላም ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ጩሁ! ኑ እንወቃቀስ! ኢሕአዴግ በሙት መንፈስ አገር ሲያምስ ዝም ብለን ማየት የለብንም::

የፖለቲካ ሰዎችም በየማግስቱ ሁለት ሦስት እየሆናችሁ የፖለቲካ ድርጅት በማቋቋም በትንሽ ፍርፋሪ ኢሕአዴግን ከማጀብ ይልቅ አንድ ሆናችሁ ለብሔራዊ ርቅ በትጋት ብትሠሩ የታሪክ ባለቤት እንደምትሆኑ አትጠራጠሩ:: መቸም ቢሆን ዘጠና ዘጠኝ የፖለቲካ ድርጅቶች ዘጠና ዘጠኝ ጠ/ሚንስትር ወይንም ፕሬዚዳንት መሆን አይችሉም:: የሚቻለውና በጎው ነገር የሕዝብ ልጅ መሆን ነው:: እንዲያው ለመሆኑ ኢትዮጵያ የማነች? ጠይቁ:: ይች አገር የሁላችንም እንድትሆን ከተፈለገ ብሔራዊ ርቅ የውዴታም የግዴታም ነው:: በማንኛውም መመዘኛ ኢሕአዴግ በሙት መንፈስ ቃለ መሀላ እያስገባ ሊገዛን አይገባውም:: እድልም ልንሰጠው አይገባንም::

ብሔራዊ ርቅ ሳንፈጥር ቀርተን እባጮቻችን አጉል ቦታና ጊዜ ላይ ይፈርጡና ትውልድ ሊወጣው ከማይችለው ቀውስ ውስጥ ቢገባ እያንዳንዳችን ከታሪክ ተወቃሽነት ማምለጥ አንችልም:: የዚህ እዳም መራራ ነው:: ለማንኛውም ምሳሌ ትሆነን እንደሆነ በሚል ካንዲት ትንሽ ፍጡር ጋር ያለንን ተመሣሣይነት ቀጥየ ለማሣየት እሞክራለሁ::

# ዳሞትራ

ዳሞትራ የሸረሪት ዘር ስትሆን መጠኗ ግን ከሸረሪት በጣም ትተልቃለች:: ዳሞትራ ባንዳንድ አካባቢ ናዚራ ይሏታል:: ዳሞትራ የምትኖረው በድንጋያማ አካባቢ ወይንም ቀያቴማ አፈር ያለበት በመጠኑ ዱር ውስጥ ከተቦረቦረ መሬት ውስጥ ነው:: አየር ፀባዩ ቆላና የበለጠም በረሃማ አካባቢ ይስማማታል::

ዳሞትራ ሰውን ጨምሮ እሷን የሚተናኮል ባደፈጠችበት አቅራቢያ ስታይ እግሮቿን በማንጨፍረር ልክ እንደ ተቆጣች ድመት በመንኮርፈፍ ፋ! ፋ-! የሚል ድምፅ ታሰማለች:: በዳሞትራ የተነደፈ ሰው በፍፁም አይተርፍም:: ተነፋፍቶና አባብጦ ነው ተሰቃይቶ የሚሞተው:: ከእባብ የበለጠ መርዝ አላት::




ዳሞትራ





ዳሞትራ ልክ እንደ ሸረሪት እንቁላል ጣይ ናት:: የምትጥለውም አንድ እንቁላል ብቻ ነው:: ካንዱ እንቁላል ውስጥ ግን በመቶዎች የሚቆጠሩ ዳሞትራዎችን ትፈለፍላለች:: ዳሞትራ እንደ እንቁላል ጣዮች ሁሉ ልጆቿን ጭራ አትመግባቸውም:: በምትኩ ራሷን አሳልፋ ለልጆቿ ትሰጣለች:: ይህ የተፈጥሮ ግዴታዋ ነው::

ልጆቿ ከላይዋላይ ሥፍረው በመጀመሪያ ይልሷታል:: ቀጥለው ደግሞ ቀስ እያሉ ይግጧታል:: በመጨረሻም እየተሻሙ ይቆረጣጥሟታል:፤ እሷን በልተው ከጨረሱ በኋላ እስበሳቸው መበላለት ይጀምራሉ:: ሁለት ሦስት ይሆኑና አንዷን አንቀው ይበላሉ:: እንዲህ እየሆኑ ተበላልተው አንድ ወይንም ሁለት ተቃራኒ ፆታዎች ለዘር ይተርፋሉ:: እንዲህ እየሆኑ ባይጨርሱ ኖሮ አገራችን የዳሞተራዎች አገር ትሆን ነበር:: እንግሀ ልብ ብለን አጢነን ከሆነ ኢትዮጵያም ዳሞትራ እናት ነች:: ልጆቿ እሷን እየተሻሙ ይበሏታል:: መልሰውም እስበሳቸው ይበላላሉ:: አስደናቂ ፍጡር ነች:: ካንዷ እንቁላል ውስጥ የተፈለፈሉት ዳሞትራዎች እናታቸውን በልተው ከጨረሱ በኋላ እስበሳቸውም ተበላልተው ይጨራረሳሉ:: የኢትዮጵያ ልጆችም ካንድ ማህፀን ውስጥ ወጥተው እስበሳቸው ይገዳደላሉ:: ይህ አስገራሚ ተመሣሣይነት ነው:: ኢትዮጵያም ዳሞትራ እናት ከመሆን፣ ዜጎቿም የዳሞትራ ልጆች ከመባል እንድንድን ብሔራዊ ርቅ ያስፈልገናል:: ስለርቅ አእምሯችንን ከፍት አድርገን እጆቻችንን እንዘርጋ!! ኑ- እንወቃቀስ!!



ዳሞትራ

# ማጠቃለያ

ውድ አንባቢያን እስካሁን እንዳነበባችሁትና ለ21 ዓመታት ተጉዘን እንዳየነውና እንዳረጋገጥ ነው ከሆነ ሕወሓት/ኢሕአዴግ የተጓዘበት መንገድና ወደ ፊትም የሚሄድበት መንገድ የመዳረሻ ግቡ ኢትዮጵያን መበታተን ነው:: ይህንን የምትጠራጠሩ ካላችሁ የዋሆች ብቻ ናችሁ:: ስለዚህ ከዚህ አስፈሪ መቅሰፍት ለመዳን መፍትሄው ተቀራርቦ በመወቃቀስ ብሔራዊ ርቅ ማውረድ ሲቻል ብቻ ነው:: ርግጥ ነው ርቅን ኢሕአዴግ ተሸማቅ ይፈራል:: ርቅን የሚፈራበት ምክንያት ደግሞ:-

1ኛ. መጠነ ሠፊ ደም በማፍሰሱ ምክንያትና የሀገሪቱን እንጡራ ሀብት ከወርቅ ማዕድን ጀምሮ እስከ ድንግል መሬቷ ድረስ ከውጭ አገር ቱጃሮች ጋር እየተቀራመተ ያካበተውን ሀብት የት ሆኖ እንደ ሚበላው ጨንቆታል:: በሕዝብ ላይ እምነት የለውም እንጂ የርቁ ፋይዳ ያካበተውን ሀብት ተረጋግቶ ያለ ሥጋት መብላትና ለልጅ ልጆቹ ማውረስ የሚችለው ርቅ ሲወርድ ብቻ ነው:: ከርቅ በኋላ የሚወረወር የከፋት ፍላፃ አይኖርምና::

2ኛው የኢሕአዴግ ሥጋት ርቅ ከወረደ ሥልጣኔን እለቃለሁ የሚል ነው:: ይህ ፍርሃቱ መቸም ቢሆን የሚለቀው አይደለም:: እውነት እንነጋገር ካልንም መቸም ይሁን መች ኢሕአዴግ አስገዳጅ ሁኔታ ካልገጠመው በስተቀር ለብሔራዊ ርቅ እጆቹን ይዘረጋል ተብሎም አይታሰብም:: ለኢሕአዴግ አስገዳጅ ሁኔታና አስፈሪ ፈንጅ የሕዝቦች መቀራረብና አንድ መሆን ነው:: ስለዚህ እኛ ደግሞ ይህንን ኢሕአዴግ የሚፈራውን አንድ እንዳንሆን ጋሬጣ የሆነንን ጎሰኝነት አስወግደን ከመበታተን ወደ አንድነት፣ ከመራራቅ ወደ መቀራረብ ከመጣን የሚበግረን አንዳችም ኃይል አይኖርም:: ወደ አንድነት ለመምጣት ግን የግድ ልብ ለልብ እንድንገናኝ መወቃቀስ አለብን:: ከተወቃቀስን ደግሞ ቁስሎቻችን ፈርጠው ይሽራሉ:: በመጨረሻም ኢሕአዴግ የሙት ራእይ ወርሶ በሙት መንፈስ አገር እያመሰ ረግጦ ሊገዛን ፈፅሞ አይገባውም:: በምንም መመዘኛ አቶ መለስ ካለፉ በኋላ በሙት መንፈሳቸውና በሙት ራዕያቸው ሊገዙን ከቶ አይቻላቸውም!! እስከ መቼስ የራሱ የሆነ ራዕይ በሌለው መሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይመራል? ይህንን ጠይቁ::

ፈጣሪ ኢትዮጵያን ትርሳት!!

ተፈፀ





# ዋቢዎች


- ❖ 80 አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ
- ❖ ዴቪድ ላምብ ተርጓሚ ኑብዩ እያሱ አፍሪካና አምባገነን መሪዎቿ (1985 ዓ.ም)
- ❖ ዶ/ር ላጲሶ ጌ.ዴሌቦ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ታሪክ አ.አ ንግድ ማተሚያ ቤት (1982 ዓ.ም)
- ❖ አንዳርጋቸው ጽጌ ነፃነትን የማያውቅ ነፃ አውጭ (1997 ዓ.ም)
- ❖ ጆንሐዘወይ ስፔንሰር ተርጓሚዎች መንግሥቱ ኃይለማርያምና መዝገቡ ምትኬ ጥርስ የገባች አገር (1986 ዓ.ም)
- ❖ የቴሌኮሙንኬሽን አገልግሎት 100ኛ ዓመት መጽሔት (1994 ዓ.ም)
- ❖ ኮሎኔል አሥናቀ እንግዳ ሽከም የማይከብደው ሕዝብ
- ❖ ተክለጻድቅ መኩሪያ የግራኝ ወረራ (1966 ዓ.ም)
  _ አፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት (ኩራዝ አሣታሚ ድርጅት 1981 ዓ.ም)
  _ አፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት (ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት 1982 ዓ.ም)
  _ አፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት (ኩራዝ አሣታሚ ድርጅት 1983 ዓም)
- ❖ ዶ/ር ሔነሪ ብላንክ ትርጉም ዳኘው ወ/ሥላሴ የሥራት ዘመን በአበሻ አገር (ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት 1962 ዓ.ም)
- ❖ ደስታ ተክለወልድ አዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት
- ❖ ገሪማ ታፈረ ጎንደሬ በጋሻው (1949 ዓ.ም)
- ❖ ስየ አብርሃ ነፃነትና ዳኝነት በኢትዮጵያ (2004 ዓ.ም)
- ❖ ፅናት ጋዜጣ ቅፅ1 ቁጥር 8 መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም
- ❖ አስማማው ኃይሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢ.ሕ.አ.ሠ) (2003 ዓ.ም)
- ❖ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ቅፅ 2 የተለያዩ ቁጥሮች (2004 ዓ.ም)
- ❖ ትኩእ ባሕታ መለስ ከልጅነት እስከ እውቀት (2005 ዓ.ም)
- ❖ ዳንኤል ተፈራ የነጋሶ መንገድ (2003 ዓ.ም)

- ብሥራት አማረ ፍኖተ ገድል (ሜጋ ማተሚያ ቤት 2004 ዓ.ም)
- ሪቻርድ ፓንክረስት (The Ethiopian Royal Chronicles)
- ጳሐፊ ትዕዛዝ ገ/ሥላሴ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ (1959 ዓ.ም)
- ተስፋዬ ገብረአብ የቡርቃ ዝምታ (1992 ዓ.ም)
- መለስ ዜናዊ የኤርትራ ሕዝብ ትግል ከየት ወደ የት?
- Advance dictionary
- ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም አሰብ የማናት? (2003 ዓ.ም)
- የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ (1995 ዓ.ም)






# የደራሲው ቀደምት ሥራዎች

1. ዳር እስከ ዳር (ረጅም ልቦለድ)
2. ጥቁር ደም (ረጅም ልቦለድ)
3. ጥልፍልፍ (ረጅም ልቦለድ)
4. ቅሌት (ታሪክ ቀመስ ልቦለድ)
5. ደም በደም (ታሪካዊ ልቦለድ)
6. ሁለገብ አማርኛ ሰዋሰው ፩ መጽሐፍ
7. 7. ዶ/ር ጥንቸል (መድብል የልጆች)
8. ልበወርቅ (መድብል የልጆች)
9. የቀበሮ ባህታዊ (መድብል የልጆች)
10. ይኸው ራሱ በሙት መንፈስ አገር ሲታመስ



አበዳሪ አገሮች ለጥቃቅኗ ነገሮች ለኢሕአዴግ መንግሥት ብር የሚያስታቅፉት ዓባይን የሚያህል ወንዝ ሲደፈር ለምን ብድር ከለከሉ? ይህ ሕዝብ ሊያውቀው የሚገባ ጉዳይ ነበር፡፡ ከሁኔታዎች መረዳት እንደሚቻለው ግን ያባይ ግድብ ጉዳይ ድንገተኛና ጥድፊያ የሆነበት አቶ መለስ የሚያውቁት ሕዝብ የማያውቀው አንድ የተደበቀ ምስጢር ይኖራል፡፡ የሚስጥሩ ቋጠሮ ያለውም ከዚህ ላይ ነው፡፡ በተረፈ አቶ መለስ እንኳንስ ዓባይን የኢትዮጵያን ሕዝብ የደፈሩ ጀግና ናቸው፡፡ ታሪኩን በሙዩ ዓመት የቋጬ፤ ክቡር ባንዲራውን "ጨርቅ" ብለው ያንቋሸሹ ናቸው፡፡

★ ★ ★

ሕወሓት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየፈፀመ ያለው ግፍ እንቅልፍ አያስተኛውም፡፡ ሊተኛም አይችልም፡፡ ፈንጅ ላይ የተቀመጠ ድርጅት ነው፡፡ ከፉና እኩይ በሆነው ተግባሩ ከሕዝብ ጋር ሊያስማማው የሚችል አንዳችም በጎ ሥንቅ የለውም፡፡ በተለይም ባማራ ሕዝብ ላይ የሚያዘንበው የከፋት ፕሮፓጋንዳና የዘር ማፅዳት ዘመቻ ከምን የመነጨ ነው? ኦርቶዶክስን ማጥፋት ወይንም ማዳከም የሚቻለው በመጀመሪያ የእምነቱ ተከታይ የሆነው አማራ ሲመታ ነው በሚል ይመስላል በነዚህ 21 ዓመታት ውስጥ እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ የመስቀልና የጥምቀት ዋዜማዎች እየተጠበቁ ታርዷል፡፡ በጅማ፣ ባርካ፣ ባሰቦት፣ የዋልድባ ገዳም ሣይቀር ወደ ስኳር ኢንዱስትሪነት እንዲቀየር የተበየነበት የዚህ ሃይማኖቱን የመገዝገዝ ቀመር ነው፡፡

ሌላው ሴራ ከሙስሊም ወገኖቻችን ጋር ለማዳማትና እስከ መጨረሻው ድረስ ለማቆራረጥ የኢሕአዴግ ሹሞች ሲፈፅሙ ቆይተዋል፡፡ ከቤተክርስቲያን አጠገብ መስጊድ እንዲሠራ ወይንም ካልጠፉ ቦታ ጥምቀተ ባህር የሚከበርባቸው ቦታዎች ለመስጊድ መሥሪያ እየተፈቀዱ ቦታና ጊዜ እየተመረጠ መጠነ ሠፊ ደም ፈሷል፡፡ እነዚህን ሁሉ የሚቆስቁሷቸው የዘመኑ ካድሬዎች ናቸው፡፡

የሕወሓት ሰዎች ምን እየሠሩና ምን እየቀበሩ እንዳሉ ደግማችሁ ደጋግማችሁ ጠይቁ፡፡ ይህንን እኩይ ተግባር ለመሞገት ወጣቱ ትውልድ ሰንፏል፡፡ ወይንም አገራዊ ደባውን በቅጡ የተገነዘበው አይመስልም፡፡ ላባቱ ጉዳይ እናቱን የሚድር ልጅ እየተወለደ ነው...

ከመጽሐፉ ውስጥ ገፆች የተወሰዱ

የሽፋን ምስልና ቅንብር -
ከአዲስ ታይምስ መጽሔት የተወሰደ

ዋ $ 26.99